በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን::

የተከፋፈለ ልብ

ትዕይንት ፩

ጠበብ ብሎ በተከፈተው መጋረጃ ዮሴፍ ቁጭ ብሎ እንደ ትዝታ ሆኖ የአባቱ የአደራ ቃል ይመጣበታል:: የሞቱ አባቱን ፎቶ ከተሰቀለበት እያስተዋለ ያስባል::

ድምፅ:- በፍፁም አላዝንም:: ተስፋዬም ባንተ ነው:: ሩጦ ማምለጥ ጨብጦ መያዝ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ተናግሮ የሚያሳምን ፍሬዬን አንተን ይጠብቅልኝ እንጂ ከእንግዲህ መዳከሜ አንዳች ቁጭትን በውስጤ አያኖርም:: ልጄ ዮሴፍ የያዕቆብ አሥር ልጆች ወንድማቸውን እጅግ በተቃወሙት ጊዜና ቅናታቸውም አይሎ ወደ ግብፅ በሸጡት ጊዜ በባዕድ ሀገር በስደቱም ወቅት ከወህኒ በግፍ ተጥሎ ብቸኝነት በተጫነበት ሰዓት ሁለ የእግዚአብሔር ጥበቃ ላፍታ እንኳ አልተለየውም:: ዛሬም ጸሎቴ ለዘወትር የዮሴፍ አምላክ ጥበቃ እንዳይርቅህ ነው:: የወጣትነትህን ብርታት ለጸም፣ ለጸሎትና ለስግደት ከማዋል እንዳትቦዝን ተስፋ አደርጋለሁ:: ልጄ ዮሴፍ እህትህን ሳራን ሶፍያ ከተባለችበት ከባዕድ ሀገር በአንዳች ምክንያት አውጥተህ የሚገባትን ምህረት ከአምላኳ ታገኝ ዘንድ እርዳት:: ታዬንም የመጨረሻ ትዕግስትህን ተጠቅመህ ርኩሳን መናፍስቱ ይርቅለት ዘንድ፣ ዳንኤልንም ከገባበት የምንፍቅና ሕይወት ትመልሳቸው ዘንድ ህያውነት በተሞላው ፍቅርህ አስባቸው:: ስለ ኢያሱ መቼም ብዙ አላውቅም:: እንደምታውቀው ደብዳቤ መጻፍ እንኳ ካቆመ ከራርሟል::

ዮሴፍ በዚህ ሁለ ጥረትህ መሃል እራስክን ከመደገፍ ላፍታ እንዳትቦዝን ይህ አደራዬ ፅኑ ነው:: ምሬት ፈጥሮብህ እንዳያስጨንቅህ ባልሻም ከአምላካችን ታገኝ ው ዘንድ የፀሎት ማቅረቢያ ርዕስ ይሆንልሀልና አጥብቀህ ያዘው::

መጋረጃው በስፊው ይከፈታል:: ዮሴፍ በሀዘን እንደተደመመ ይናገራል::

ዮሴፍ:- አባዬ ቃልህ በህሊናዬ ድምፅ አውጥቶ መጮህ ከጀመረ ከራረመ:: ሞትህ ምክንያት ሆኖ ሳራን ከውጭ አመጣት:: ኢያሱም ቀጥሎ መጣ:: ታዲያ ዛሬ ልጆችህ ሁለ ተሰባስበው ሁሉም በየግላቸው መንገድ እየተጓዙ ብትመለከት ይህች ቤትህ የአንድ አንተንና እማማን ህያው ነፍሳት በእምነትና በአስተሳሰብ ከፋፍላ ይዛ ብታይ ምን ይሠማህ ይሆን? አንድ የሚያደርጋቸው አንተ የተማመንክበትን ዓይነት ብርቱ የመንፈስ ቅዱስ ዕቃ ጠፍቶ ብታይ ምን ትል ነበር? የኢያሱ የሱስ ምስክርነት፣ የታዬና የሜላት የደራ የጥንቆላ ሥራ፣ የሳራ የባዕድ ሀገር ናፍቆት፣ የዳንኤል የምንፍቅና ሁሉም ከልክ አልፎ የአንዲቷ የእማማ ሀዘን እጅግ ፀንቶ ብታይ ምን ይሰማህ ነበር?

/ኢያሱ ይገባል፣ ሪቫን ግንባሩ ላይ አስሯል አለባበሱ ለየት ያለ ነው በዘመናዊነቱ/

ኢያሱ:- ሰላም ቁሱ ዮሴፍ!! ለዚህ ቤት ቀዳሽ ባራክ ትሆን ዘንድ በአላክህ የተቀባህ

ዮሴፍ፡- **/እያማተበ/** ኢያሱዬ ምነው ይህችን ደካማ ልቤን እታበይባት ዘንድ ባትፈትናት? ትንሽነቴን ምናምንቴነቴን እንዴት ብዬ ልግለፅልህ?

ኢያሱ፡- Oh! It is incrdible!! ይህ ራሱ እኮ የትልቅነትህ ምስክር ነው። የአንተን ግዙፍ መንፈሣዊ ልብ ከዳንኤል ተልካሻ ልብ ጋር ላነፃፅር የተጠቀምኩበት መንገድ እንደጠበቅሁት ሆኖ ተሣካልኝ። ዳንኤል ምን እንዳለኝ ታውቃለህ? የኢየሱስ ወታደር ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል በአየር ላይ ተንሣፎ የሚበር መሲህ፣ የሃይማኖት ርግብ፣ ንጹህና ቅዱስ መሆኑን እያብራራ ነገረኝ አንተ ግን.....ድንቅ ንጽጽር By the way ማም የት ናት?

ዮሴፍ፡- ወደ ውስጥ ሣትሆን አትቀርም። የት ልትሄድ አስበሀል? አሁን የምሣ ሰዓት ስለሆነ ልጆቹን ጠርተህ አንተም ብትቀመጥ ጥሩ ነው።

ኢያሱ፡- የመጥራት ትዕዛዙን ተቀብያለሁ። ለመብላቱ ግን አልገደድም። **/ያፋጫል/** «ሃሎ! ሃሎ! የምግብ ጦር ምስጦች ሁሉ፤ የምትበሉበት ስዓት በመድረሱ በመብያው መድረክ ትሰበሰቡ ዘንድ ታዛችኃል።» **/ዮሴፍ ያየዋል/** ምነው? አዲሱ የአጠራር ስልት አልጣመህም?

ዮሴፍ፡- ኢያሱዬ ይህማ ስርዓት አይደለም። በአምሳለ ስላሴ የተፈጠረን የእጁ ስራዎች ምድር ውስጥ ከሚኖሩ ምስጦች ጋር እንዴት ታነፃፅራለህ.....ደግሞም...../**ያቋርጠዋል/**

ኢያሱ፡- ተወው ተወው ሄጂ ታዬን ፣ ከጥንቆላው፣ዳንኢልንም ከአርቲ ቡርቲ የስንፍና ስራው፣ሶፊያንም ከመቆጠሪያ ቆጠራዋ እጠራቸዋለሁ። የዋህዋ ርግብ ማም ደግሞ ከማጀቷ ገበታዋን ተሸክማ ከች!

ዮሴፍ፡-/**ግራ እንደተጋባ/** መቼ ይሆን ይህ ሁሉ አብቅቶ መኖር የሚጀመረው? ሁላችንም እንደ አንደነታችን በአንድነት ይምንዘምረው? **/ሜላት ትገባለች/**

ሜላት፡-ዮሴፍ እንደምን ውለሀል?

ዮሴፍ፡-እግዚአብሔር ይመስገን ሜላት ደህና ውለሻል? ምነው ያዘንሽ ትመስያለሽ? እጮኛሽ ወንድም አለም የስቀየመሽ እንዴ?

ሜላት፡- ኧረ ደህና ነኝ እንዲያው የሆነ መፅሀፍ እያነበብኩ ስለነበር ነው። **/ሳራ/ሶፊያ/፣ ታዬ፣ ዳንኤል ይገባሉ። ከዮሴፍም ጋር ሠላም ይባባላሉ/**

ታዬ፡- ወሬያቸሁን አናቋርጥ ዘንድ ቸኩለን እንዳልገባን ተስፋ እናደርጋለን።

ዮሴፍ፡- ኧረ በፍፁም ወንድም አለም። እንዲያውም ሠላም እየተባባልን ነው የገባችሁት ደግሞም እኮ በምሣ ሰዓት ያን ያህል ጠንክር ያለ ወግ መያዝ ያስቸግራል።

ታዬ፡- አንዳንዴ ጠጠር ያለ ቁምነገር ሲያጋጥም የት ይቀር ብለህ? በል እስቲ በቶሎ እማዬን ምሣ በላት / **ዮሴፍ ይገባል**/ .....ዳንኤል እስከዛ ጸሎትህን ብትጀምር ምን ይመስልሀል? አይደል እንዴ ልጆች?

ሶፊያ፡- ከወዲሁ የመጠበቅ ትዕግስት እንደሌለህ ለመግለጽ ነው አይደል ታዬ? **/እያወጉ እያለ እናት ምሳ ይዘው ይገባሉ/፡፡** ልጆቹንም ሰላም እያሉ ያቀራርባሉ፡፡ ለሶፊያ ለበቻዋ ይሠጧታል፡፡ ከዚያም ወደፊት ጠጋ ብለው ደጃፉ ላይ ይቀመጣሉ፡፡ ዳንኤል ለጸሎት ያቀረቅራል፡፡ ሜላትና ታዬ ይመገባሉ፡፡ ኢያሱ ይገባል፡፡

ኢያሱ፡- ምነው ማም እንደየኔ ቢጤ በር ላይ ኩርምት ብለሽ ተቀመጥሽ? ውጪ! ከእኛ ጋር አትበይም አሉሽ? አብስለሽ አዘጋጅተሽ ለምስጦቹ ተውሺላቸው? ነይ እስቲ ባይሆን ለኔና ላንቺ አቅርቡ እኔ አባላሻለሁ፡፡

እናት፡- ኢያሱዬ ወቅቱን ረሣኸው መሠል?

ኢያሱ፡- አሃ! ለካ የምን ጾም ነው ገብቷል ብለሽኛል፡፡ ለማንኛውም እኔ በጠዋት ጥሩ ክትፎዬን ልፊያለሁ፡፡

ሜላት፡- ከእኛ ጋር ጥቂት ብትጨምር ለቁንጣን የሚዳርግህ አይመስለኝም፡፡

ኢያሱ፡- ኧረ! ኧረ! ተይ እንጂ ሜላት እኔ ከእናንተ ጋር ቁጭ ብዬ ማዕድ ልቁረስ? የሁለት ዓለም ሰዎች መሆናችንን ረሣሽ?

ታዬ፡- እውን አንተ አሁን ዮሴፍ ሲተው አይተህ ነው እንጂ የተውከው ከእኛ ጋር እንዳትበላ የሚያደርግህ ምን ተጨባጭ ምክንያት ኖሮህ ነው?

ኢያሱ፡- ታላቂ! መጀመሪያ ብሎና ምክንያቴን አንድ በአንድ እዘረዝርልሃለሁ፡፡ **/ዳንኤል ጸሎት ጨርሶ ቀና ይላል እንጀራው ሊያልቅ ነው፡፡/**

ዳንኤል፡- ሰው በእግዚአብሔር ቃል እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም፡፡ ኢያሱዬ ምን ጊዜ ገባህ?

ኢያሱ፡-አንተ ስትበር፣ሰማየ ሰማያት ሰንጥቀህ ኢዮርና ራማን ሁሉ አልፈህ ጽርሃ አርያም ልትገባ ጥቂት ሲቀርህ መጣሁ ደግነቱ አንተም አልደረስክ ተከሰከስክ! መጥፎ አወዳደቅ No food!

ዳንኤል፡- አንተ እንዳልከው ግን አይደለም ኢየሱሴ ይባረክ ደርሼ ነበር የተመለስኩት የዘወትር ጉዞዬን ባማረ ሁኔታ ፈጽሜ ስመለስ ካገኘሁት ደስታ አንጻር ያጣሁት እንጀራ ምንም ነው፡፡

ሜላት፡- ይህቺን ብላ ትበቃሃለች፡፡

ታዬ፡- አይ ሜላት! ዳኒ በዚህ ብቻ ይመለሳል ብለሽ ነው? ለማንኛውም ይቅመሣት

ኢያሱ፡- ኧረ ይህቺስ በሰፊው ተያይዛዋለች አግዙኝ አትያቸውም እንዴ **/በፌዝ/**

ሶፊያ፡- አጉል እየኮሩ መቼ እሺ ይላሉ ብለህ ነው? ዳኒ.....ና ብላ፡፡

ዳንኤል፡- ጌታ ይባርክሽ እህት ዓለም በቃኝ **/ኢያሱ ከሶፊያ ጋር ጥቂት ይቀማምጣል፡፡ ታዬ ተነስቶ ወደ እናቱ እየተጠጋ/**

ታዬ፡- እናቴ ሃና ለምን አንድ ቀን ቤተሰባዊ ስብሰባ አናካሂድም?

ኢያሱ፡- /በጉንተላ/ ሰሞኑን የጥንቆላው ገቢ ቅንሳልኗ.....

ታዬ፡- አዎ አየሽ ማድረጉ አይከፋም የአባታችንን ንብረት አሰባስቦ ስርዓት ማስያዙ የአጠቃላይ የቤተሰቡ ኃላፊነት ቢሆንም ይበልጥ እኔና አንቺን ይመለከታል።

እናት፡- እንዳልክ ልጄ ታዬ እኔ ምኑን አውቄው ብለህ? ግን እንዲያው ተዚህ ሁሉ በፊት መቅደም ያለበት አንተም ጥንቆላህን ትተህ፣ ይህቺ እህትህም ይህን አንጉል ቅብጠቷን እርግፍ ብታደርግ፣ ይህም ሙትቻ ጌታ ይክበር የሚለውን ባዶ ፉከራ ቢያስወግድ ነበር የሚበጀው

ሶፊያ፡- እማምዬ ደግሞ መቅደም ያለበትን አዟዟርሽው ብር እኮ ብዙ ነገር ይለውጣል።

ኢያሱ፡- ቪዛ የምታስመቺበት እጅ እንዳጠረሽ ግልጽ ነው። ለማንኛውም ሶፊ ስትሄጂ እንዳትረሺኝ።

እናት፡- ልቤን አቁስላ እንደኖረች አንድም ቀን ከኔ ጋር ለመቆየት የማትሻ ድንጋይ ልጅ ቢዛ ቢዛ ብላ ልትሞት ነው።

ታዬ፡- እማዬ ልንጫናት አይገባም። ለመኖር ገንዘብ ያስፈልጋታልና ሄዳ የምትሻውን ገንዘብ ለማግኘት ልንረዳት ይገባል። ለማንኛውም ይህ አያስጨንቅም ዋናው ቁም ነገር ግን የአባታችንን ሀብት ስርዓት አስይዞ አስፈላጊውን ማድረጉ ላይ ነው።

ኢያሱ፡- እኔም ካንተ ከታላቁ ጥቂት ኃላፊነት ብመጸወት አሳፋሪ ባለስልጣን የምሆን አይመስለኝም።

ሜላት፡- ኢያሱ ደግሞ በሁሉ ነገር መቀለድ ይወዳል።.....እንሂድ ታዬ /ተያይዘው ይወጣሉ ዳንኤል ቀለል ሲለው ያስታውቃል/

ኢያሱ፡- እማም ነይ ግቢ እባክሽ እነታዬ ሲወጡ እንኳን እኔን ዳኒን ቀለል ብሎታል። /እናቱን ይዞ ይገባል/

ዳንኤል፡- አዎ ልክ ነህ አንድ ቀን ጌታ ሲፈቅድ እናንተ ኢየሱሴን እንደምትቀበሉ እርግጠኛ ስለሆንኩ ከእናንተ ጋር ስሆን ይቀለኛል እነሱ ግን ክፉ ዲያብሎስ ሰፍሮባቸው ፍጹም ስለተማረኩ መቼም የሚመለሱ አይመስለኝም

እናት፡- ኤድያ! አንተስ ላይ ሰፍሮ የሚያስለፈልፍህ ምን ሆነና ነው? ዮሴፍዬ ሲያስተምረኝ «በራስህ ዓይን ውስጥ ያለን ምሰሶ ሳትመለከት የሌላውን ጥቂት የአይን ጉድፍ ለማውጣት አትማክር» የሚል ጥሁፍ አንብቦልኛ ል።

ዳንኤል፡- ልክ ነው የጌታ የኢየሱስ ቃል ነው፡፡ ይህኮ ታዲያ ዮሴፍዬ እኔን ሊመክር ሲቃጣው መጠቀስ የሚገባው ጥቅስ ነው፡፡

ኢያሱ፡- በይ እስቲ ሶፊያ አንቺም አይደለም መጠቀስ ያለበት አንተና ኢያሱ እኔን ለማሣመን ስትሞክሩ ነው አትይም? ምን አይነት ደካማ ተጫዋቶች አጋጠሙኝ እባካችሁ? ተንቀሣቀሽ በዚህ ውስብስብ የህይወት ጨዋታ ውስጥ ማንነትሽን አጉይው፡፡

ሶፊያ፡- አንተ እየተናገርክልኝ እኔ ምኑን ተጫወትኩት?

ኢያሱ፡- አይ እኔ ላስታውስሽ ነው እንጂ አንቺን ወክዬ መጫወት አልችልም እኔ ጆከር ነኝ እንጂ በጨዋታው ውስጥ ውሱን የሆነ ማንነት የለኝም ገባሽ?

ዳንኤል፡- መች እንዲገባ አድርገህ ትናገርና ይገባታል? ለማንኛውም ኢያሱዬ መንገድህን ልታስተካክል ይገባሃል ህይወትህን ለጌታ ስጥ እሱም ትክክለኛ ውን ያመለክትሀል፡፡

ኢያሱ፡- ኤድያ! እንኳን እኔ ተጨምሬ አንተም መንገድህን ያገኘህ አይመስለኝም ምናልባት ከጊዜ ብዛት መንገድህን ካገኘህ ብታስታውሰኝ አይከፋም ባልከተልህም ላንተ የሚሆን ምክር አላጣም፡፡

እናት፡- ጎሽ የኔ ልጅ እንዲህ ልክ ልኩን ንገርልኝ /**ሶፊያ ልትሄድ ትነሣለች**/

ሶፊያ፡- እማዬ ስልክ ከፈለገኝ ጋደኛዬ ጋር ደውሉልኝ በያቸው

ኢያሱ፡- ጓደኞችሽ ጋር እየሄድሽ ነው ማለት ነው፡፡ ለማንኛውም እግር አታብዥር ራስሽን ጠብቂ ህይወትሽ ራሷ ሚዛኗዊ ባልሆነ ርካብ ላይ ነውና የረገጠችው ጥቂት ብታጋድይ አወዳደቅሽ የከፋ ነው፡፡ መሰልሽን እስከምታገኚ የማትመስልሽን ጓደኛ አትያዥ ሰው ባንዴ እውነተኛ ጓደኛ የማግኘት እድሉ በጣም የጠበበ ነው፡፡ የአሁኗ ጓደኛሽ መሰልሽ ትመስልሽ ይሆናል፡፡ አውቃለሁ ፎዚያን ከስሟ ብንጀምር አትሆንሽም፡፡ ተያት! ወይ እንደኔ በልብሽ ገዳም መንነሽ ብቸኛ ሁኚ.....ቻው! /**ሶፊያ ትወጣለች**/

ዳንኤል፡- ስትናገር ልብ ትነካለህ ግን አንዳንዴ ትሳሳታለህ

ኢያሱ፡- አንተ ነህ የተሳሳትከው፡፡ አየህ ማንኛውም ንግግር እያሾፉ ካልሆነ በቀር ለተናገረው ትክክል ነው፡፡ ለሰማው ግን ትክክለኛነቱ እንደ ጆሮውና እንደ ህሊናው ነው፡፡

ዳንኤል፡- ጥሩ ምክር መክረሃታል

ኢያሱ፡- አንተም ስትሄድ ብታስተውሰኝ የምልህ አላጣም

ዳንኤል፡- አብረን እንሂድ ብልህስ?

ኢያሱ፡- እሺ እንደማልልህ ስለምታውቅ አትቀብጥም /**ዳንኤል ሰዓቱን ያይና ሊሄድ ይነሳል**/

ዳንኤል፡- ለካ ሰዓቱ ደርሷል፡፡ ዛሬ የጸሎት ኘሮግራም አለን፡፡

ኢያሱ፡- /ጥቂት አሰብ ያደርግና/ ታላቁ ስለሆንክ የምልህን አጣሁ ለማንኛውም ራስህን እንደራስህ ጠብቅ

ዳንኤል፡- የጌታ ሰላም ይብዛላችሁ ደህና ዋሉ

ኢያሱ፡- አሜን፡፡ ወንድም አለም አሜን! Oh No! No! አያገባህም

ዋሽንት

/አናት በስዕለ ማርያም ፊት ይንበረከካሉ፡፡ ኢያሱ በአትክሮት ይመለከታቸዋል ሲጨርሱ/

ኢያሱ፡- ደስ ይላይ፡፡ ማም

እናት፡- እኔ ስደሰት አይተህ እንጂ አንተማ ምኑን አውቀኸው? የእኔንና የአባትህን እምነት ብትከተል ይበልጥ ትደሰት ነበር፡፡

ኢያሱ፡- አይ.....እማም አልተዘጋጀሁም.....የጸሎት ሰዓትሽን አስረፈድኩብሽ አይደል? አትነግሪኝም ነበር?

እናት፡- ምን ያደርጋል? ዮሴፍ ሰርቪሱን እነታዬ ሲይዙበት ጊዜ እመቤቴን ይዞ ወደዚህ መጣ ታዲያ ሰው መጣ አልመጣ እያልኩ ተዚችው የአቅሜን አነበንባለሁ፡፡

ኢያሱ፡- ፐ! እዚህ ቤት ውስጥ ታዬ ነግሶበታል፡፡ ሳሎኑን ለጥንቆላ፣ ሰርቪሱን ለጉልምትና ወደፊት ደግሞ የአስጠንቋዩ ደንበኞች ቁጥር ሲጨምር ይህንንም ልቀቁ ማለቱ አይቀርም እማም አንቺና ዮሴፍ ለምን ዋልድባ አትወርዱም?

እናት፡- እግዚአብሔር ሳይፈቅድ መች ይሆናል ልጄ? ደግሞስ ካሰቡበት ቤትም ገዳም ነው፡፡ ነገር ዓለሙ ድብልቅል ብሎ ግራ አጋባኝ እንጂ በቤትም መመነን ይቻላል እኮ ኢያሱዬ

ኢያሱ፡- አይ! አይመስለኝም እማም መሰልሽ በሌለበት? የታዬ የጥንቆላው እጣን ጢስ እየቦነነብሽ፣ የሶፊያ የመቁጠሪያ ቅጭልጭል እያደነቆረሽ፣ የዳንኤል አርቲ ቡርቲ ልፍለፋ እያሰለቸሽ፡፡.....እኔ ደግሞ ቀን ስቅም እውልና ማታ ደግሞ የጨብሲ ተወግቼ ስመጣ በመግነዛዊ ትንፋሼ እያወድኩሽ እዚህ ቤት ውስጥ ልመንኩስ ትያለሽ? እኔ እንጃ አምላካችሁም ይለመንሻል ብዬ አልገምትም

እናት፡- አምላካችን በል እንጂ ልጄ?

ኢያሱ፡- አይ እማም እኔ ያመኑበትንም ያላመኑበትንም ዝም ብሎ መቀባጠር አልወድም፡፡ አብደሀል ብለው ከምወዳት ዳላስ ገነቱ በአሮጌ አውሮኘላን ጭነው ካባረሩኝ ወዲህ በእምነት በኩል አንዳች ተጨባጭ ነገር አላገኘ ሁም አባታችን ከመሞቱ በፊት ጥቂት ቀደም አድርገው አሳብደውኝ በነበርና እውነቱን ከርሱ በተረዳሁት መልካም ነበር፡፡

እናት፡- እኔስ ልጄ? እኔስ እናትህን ለምን አትሰማኝም? ዮሴፍስ? የአባቱን የአደራ ቃል ተሸክሞ ሌት ተቀን የሚለፋ ወንድምህን ለምን አትሰማውም? በርሱ ያለ የአምላክ ፍቅር ለምን ባንተ ውስጥ አንዲኖር አትፈቅድም? ኧረ ተው ልጄ ተው

ኢያሱ፡- እማም ምን ላድርግ? ዳንኤልም ይለኛል፡፡ እሱም የለብላቢት ቀንበጥ እንደበላች ፍየል ኢየሱስን ተቀበል እያለ ምዕራፍና ቁጥር እያጣቀሰ ብትንትን ቋንቋውን ገጣጥም ሊያሳምነኝ ይሞክራል፡፡ እማም ቀና ብለሽ ስሚኝ፡፡ ይልቅ አንቺ ገዳም ግቢ ከምናምንቴዎች ጋር ኑሮ ይቅርብሽ፡፡

እናት፡- አይ ልጄ እስቲ ተወኝ ይልቅስ አንተ ሰው ሁንልኝ በቃ እነዚህን ሱሶችህን እርግፍ አድረገህ ተዋቸው፡፡ እኔ እናትህን ዛሬ በእርጅናዬ ዘመን ደስ አሰኘኝ ሌት ተቀን እኮ የምጨነቀው ላንተ ነው፡፡ ልጄ እስቲ እሺ በለኝ

ኢያሱ፡- እሺ እማም ሁሌም አንቺ እሺ እንደምትይኝ እኔም እሺ እንዳልሁ ነኝ..... ማም ዛሬ ደግሞ ኪሴ ባዶ ነው፡፡ እናም...../**እናት ብሮች ይሰጡታል/** thank you ማም ኧረ! በቃ ዋልድባም ይቅር ኑሪልኝ አቦ /**ይዞ ሲወጣ መብራት ይጠፋል/**

ትዕይንት ፪

ከመጋረጃ ጀርባ ዋሽንት ይከፈታል መጋረጃው ሲከፈት ዳንኤልና ሜላት ይታያሉ ተከራርፈዋል። የጥቂት ጊዜውን ዝምታ ሜላት ጥሣው ትናገራለች በምሬት

ሜላት፡- ሴትነቴን ፈትነህ ከሰው በታች አደረግኸኝ። ስስ ልቤን አማለህ ከማልወጣው ስቃይ ውስጥ ጨመርከኝ። ህይወቴን የሴትነት ሃብቴን ክብሬን ነጠቅኸኝ። ዳንኤል የወንድምህ ታዬን ሰይጣናዊ ቁጣ ቀስቅሰህ ነፍሴ በጭብጡ እንዳለች ፍሬ ምናምንቴ እንድትሆን አረካት። እርሱም በጭካኔ ሊያፈርጣት ሲጥ ሊያደርጋት ነው።

ዳንኢል፡- ጌታ ይመስገን ሜላት ጌታ ይክበር አንዳች የለብሽም ለመሆኑ እንዴት አወቀ?

ሜላት፡- ዘወትር የማታዘዙኝ ጭፍሮቼ እነ አዳልሞቴ ሹክ አሉኝ ክብር አልባ መሆንሽን በውስጥሽ የሚላወስ ፍሬ መያዝሽን ጠቆሙኝ አለች።

ዳንኤል፡- ፑፍ.....ሀሰት ጌታ ይክበር ውሸቱን ነው። ለአንዱ አውርተሽ ወይንም ደግሞ ላንዷ ስታማክሪ ሰምቶ አልያም በህልምሽ ቀባጥረሽለት ይሆናል እንጂ የሱ አዳልሞቴ በጌታ የተያዘን ሚስጥር በፍፁም ሊገልፅለት አይችልም።።።

ሜላት፡- አይ ዳንኤል! ከነዚህ ከዘረዘርካቸው የተለየ አዳልሞቴ ከየት ሊመጣ ብለህ? ሰይጣን በሰዎች አድሮ እንጂ የሚሰራው ራሱ በግዙፍ አካል አይገለጽ።.....ታዲያ ዳኒ ታዬ የማይታጠፍ ፍርዱን ፈረደብኝ። «ሉሩሃማ» ነሽ ምስሽ ሞት ነው ሲል ማታ ቁርጥ ውሣኔውን ገለፀልኝ...ነገር ግን ሞት የሚገባት የኔ ነፍስ ብቻ ሣትሆን የደፈረኝም ሰው ነፍስ መሆኗንም አሁንም ከብረት በጠነከረ ቃሉ ገለጾልኛል። **/ዳንኤል ይርዳል/**

ዳንኤል፡- በጌታ ስም! ታዲያ እኔን የኢየሱስ ወታደር ለሞት አሣልፈሽ ልትሰጪ ስሜን ገለጽሽለት?

ሜላት፡- እጅግ አስጨነቀኝ..... እጅግ ወተወተኝ .....ግን.....

ዳንኤል፡-እናስ? ውትወታውና ጭቅጨቃው የልብሽን ፍቅር ለኔ ለኢየሱስ ወታደር ያለሽን ታላቅ አክብሮት ፈትቶ ወደቅሽ? ስሜን፣ እኔነቴን ገለጽሽለት?

ሜላት፡- መሣሪያ አውጥቶ ቢያስፈራራኝ፤ የቃላት ውርጅብኝ እያወረደ ቢያርደኝ

ዳንኤል፡- በጌታ ስም! ወደቅሽ? ፍርሃት አንደባሎ ጣለሽ?

ሜላት፡- ኧረ በፍፁም!

ዳንኤል፡- ጌታ ይክበር! እልል...../**እናት እልልታውን ሰምተው ከውስጥ ይወጣሉ/**

እናት፡- ምን ተገኘ ደግሞ ነው ነካ አደረገህ?

ዳንኤል፡- ጌታ ይክበር እማዬ እኔስ ደህና ነኝ እንዲያው በተደረገልኝ ቸርነት ደስታዬ እጥፍ ድርብ ሲሆንብኝ ጊዜ መቆጣጠር አቅቶኝ ጌታዬን ላከብር አልል አልኩኝ

እናት፡- ኤዲያ! አክብረኸው ሞተሃል እቴ! ምን እንዳው ለዛ ያጣ ነገር ነው የምታሰሚኝ እመቤቴ! ኤጭ! ኧረ ተው አንተ እንከፍ ተው ወደልብህ ተመለስ ዘወትር በምሬት እንድኖር ባታደርገኝ ምናለ?

ዳንኢል፡- ...../**የሚለውን መዝሙር ይዘምራል**/ .....አይ እማዬ! ለኔ የበራ ብርሃን ለእናንተ ሁሉ ተገልጾ አብረን ደስ ቢለን ምን ነበረበት? አሁን ሁላችንም የኢየሱስ ወታደር ለመሆን ብንታደል?...ሜሊ መቼም አንድ ቀን ጌታን እንደምትቀበይ እርግጠኛ ነኝ

ሜላት፡- ትንሽ ልጅ! የማትረባ! በሰው ሞት ለጌታህ ክብር የምትሰጥ ከንቱ ኃጥያት መጽውተህ ፃድቅ ልሁን ባይ የነሃስ ጩኸት የምታቃጥል.....

እናት፡- ጎሽ እንዲያው አፊ ቁርጥ ይበልልሽ በደንብ ንገሪው፡፡ ይኼ ትንሽ ልጅ ኤድያ!

ዳንኤል፡- ጌታ ይክበር ኢየሱሴም ተገርፎ ተሰቅሏል ምራቅም ተፍተውበታል ዛሬ አኔን ነጻ ሊያወጣኝ፡፡፡ የእናንተ ስድብ ምንም ነው /**በፉጨት ይዘምራል፡፡ ኢያሱ ይገባል፡፡**/

ኢያሱ፡- የስርቆሽ ፍቅራችሁን እየተወጣችሁ ሣለ ርግቧ እማዬ ገብታ ነገሩን ሁሉ ብልሽትሽት /**ይስቃል**/

ዳንኤል፡- ሂድ.....ሂድ.....በጌታ ስም! ውሸታም! ቀጣፊ! ሰይጣን! /**እንደ ማባረር ይላል**/

ኢያሱ፡- እሺ.....እሺ.....በቃ ዝም! ምስጢር አላወጣም /**ሜላትን ያያታል**/ ምስኪን! አስከፍተሃታል ዛሬ የኢየሱስ ወታደር ክላሽንኮቭ ጠበመንጃውን ደግኖብሽ ነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢሽን ሲያስቆጥርሽ ያረፈድሽ ትመስያለሽ፡፡ እማዬ እንዴት ነው ግብግቡ ላይ አልደረስሽም?

እናት፡- ምን እባክህ መላ ቅጡ የጠፋ እልል እያለ ቤቱን ቢደባልቀው ዛሬ ምን ሲሳይ ቤቴ ገባ ብዬ ብዘልቅ የኔው እብድ ተገትሮ «ጌታ ይክበር» ይለኛል

ኢያሱ፡- ብራቮ! እኔ እብድ አለመሆኔን አወቅሽ አይደል? ጨርቁን የጣለው ይኸው! /**ወደ ዳንኤል እየጠቆመ**/.....እማም መቀነትሽን ካልዳበስሽልኝ መሞቴ ነው /**ጸጉሩን ያሻሻል**/

እናት፡- ኧረ ቁምልኝ ልጄ እኔ እናትህ እያለሁ?! ...../**ብሮች ፍለጋ መቀነታቸውን ሲዳብሱ ያጣሉ**/ ኢያሱዬ አልያዝኩም፡፡ እ.....ወደ ውስጥ እንግባና እሰጥሃለሁ /**ይዘውት ይወጣሉ**/

ዳንኤል፡- ጌታ ይባርክሽ ሚላት!

ሚላት፡- እግዚኦ ያንተ ጌታ! እግዚኦ ያንተ ኢየሱስ!

ዳንኤል፡- ተይ እንጂ ሚላቴ እንዲህ አይነቱን ቆሻሻ ነገር ስሠራ እኮ ጌታን አልተቀበለኩትም ነበር፡፡ ብርሃን የበራልኝ የማታ ማታ ነው፡፡ ታዲያ የትላንት ታሪኬ ከዛሬው ብሩህ የድህነት ኑሮ ጋር ቁርኝት የለውም፡፡

ሚላት፡- ተው እንጂ ዳንኤል እንደዚህ አትበል በኔ ውስጥ ያተምከው የዘለዓለም ምልክትስ የትላንት አንተነትህ አሻራ መሠረታዊ ቅርስ! ይህንንስ ምን ልታደርገው ነው? ታሪክ ነው ህይወትና አካል ያለው ፍጡር! ተው ዳንኤል የትናንት ማንነትህና የዛሬ አንተነትህን አገናኝ ድልድይ ህያው ታሪክ እንደሌለ ሁሉ አጉል አትመጻደቅ ኤዲያ!

ዳንኤል፡- ጌታ ይክበር ትናንት የተረሣ ነው፡፡ በተለይ ለኔ ትላንት ጨለማ ነበር ዛሬ ብርሃን ነው የኔን ከሌሎች የሚለየው ይህ ነው፡፡ በአንጻሩ ደግመ ዛሬም በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ የሚኖሩ አሉ፡፡ ስለዚህ.....ስለዚህ ሚላት እኔን ብርሃናዊውን የኢየሱስ ወታደር ነጻ ማውጣት አለብሽ

ሚላት፡- **/እጅግ በቁጣ እንባዋ እየተናነቃት/** እንዴት? እኮ እንዴት ተደርጐ?

ዳንኤል፡- የጨለማን ፍሬ ለጨለማ ግዞተኞች በመስጠት! ጌታ ይክበር!

ሚላት፡- ኧረ! ጀብደኛው የኢየሱስ ወታደር! እስኪ ከጨለማው ግዞተኞች አንዱን ለምሣሌ ጥቀስልኝ

ዳንኤል፡- ከህልቅ መሣፍርት መሃል አንዱን ጥቀስልኝ በማለትሽ ደስ አለኝ፡፡ ጌታ ይክበር! የጨለማውን ግዞተኞች በሙሉ ግለጽልኝ በማለት የማይመች ጥያቄ ብትጠይቂኝ ኖሮ ግን ለጌታ ክብር ሰጥቼ ስቂ ዝም! እል ነበር ለማንኛውም ታዋቂውና አንጋፋው ምሣሌ ዮሴፍ አለልሽ

ሚላት፡- እግዚኦ ውሽት! እግዚኦ ቅጥፈት!

ዳንኤል፡-ሃቁ ግን ይሄ ነው አንቺን ባይመስልሽም አስቢበት! እመለሣለሁ፡፡**/ይወጣል/**

ሚላት፡- እንግዲህ ምን ይዋጠኝ? ምንስ ልሁን? ሞት ቀረበችኝ አሁንስ እኔ ምንድ ነኝ? ሰብአዊ! የእውነተኛ ፍቅር መስዋዕት? ወይስ ጨካኝ ከዳተኛ?.....ዳሩ ማንነቴ ምን ፋይዳ አለው? የታዬን ሰይጣናዊ ቁጣውን አብርዶ የሞት ፍርዱን ላያሣጥፈው.....ግን ከዚህ የሞት ፍርድ የምድንበት አንዳች መላ የለም? ምንም? ህሊናዬ ባክህን መላ ፍጠር! በፍጥነት የምድንበትን መላ ቀይስልኝ **/ዮሴፍ ይገባል/**

ዮሴፍ፡- እንደምን ውለሻል ሚላት?

ሚላት፡- ደህና ነኝ፡፡ አንተ ደህና ውለሃል?

ዮሴፍ፡ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ፡፡.....ልክ ጭንቀትሽን ሳይ ምን ትዝ እንዳለኝ ታውቂያለሽ? አንድ የአምላክ ቃል በህሊናዬ አቃጨለ፡፡ «እናንት ሸክማችሁ የከበደ ወደኔ ኑ፡፡ እኔም አሣርፋችኃለሁ» የሚለው፡፡ ሜላት ልዩ ጥሪ አይደለም? ፍቅራዊ መስህቡ አልተሠማሽም?

ሜላት፡- በፍፁም! ምን እንደሆነ ባላውቅም ላም አለኝ በሠማይ አይነት የተስፋ ጥበቃ አንገቴን ወደላይ በማቅናት መጓጓት አልሻም፡፡ አሁንና እዚህ በሚሆን መፍትሄ ፍፁም እምነት አለኝ፡፡

ዮሴፍ፡- አሃ ሜላት! አምላካችን አሁንና እዚህ የሚታይን መፍትሄ መስጠት የሚሣነው ይመስልሻል? ዛሬ እኔና አንቺ እዚህ እንነጋገር ዘንድ የፈቀደ ያደረገም ማን ይመስልሻል?

ሜላት፡-ተው ዮሴፍ የማይመስል ነገር መስማት ሰልችቶኛል፡፡ አሁንና እዚህ ዛሬ ክህደትና ቅጥፈት ሲነገር የፈቀደ አምላክ ነበራ?! ዛሬ እዚህ የሞት ኑዛዜን ያናዘዝ ዘንድ ሃይልን ለአናዛዥ ምስኪንነትን ለተናዛዥ የቸረም አምላክ ነበራ?! አይ ተው.....ተው..... ዮሴፍ **/ክፍት ይላታል/**

ዮሴፍ፡- ሌላ ማንም ይሆናል ብለሽ አትገምቺ፡፡ ለእግዚአብሔር አምላክ አንገዛ ብለነው ስናምጽ ከህጉ ርቀን በስሜታችን ስንመራ የክፋት አባት ይሰለጥንብናል፡፡ ነገር ግን ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ይሆናል፡፡ ፊታችንን ወደርሱ መልሰን በጸጸት ተመትተን የተማጸነው እንደሆነም የሰለጠነብንን ርኩስ መንፈስ፤ ከአለት ይልቅ የከበደውን የልቦናችንንም ትካዜ ሊያርቅልን እርሱ የታመነ ነው፡፡.....የሆነስ ሆነና ሜላት ስለምን የሞት ፍርድ ነው የምታወሪው?

ሜላት፡- ስለምንም የሞት ፍርድ! **/ታዬ ይገባል፡፡ ፊቱን አኮሣትሮ ግራ በተጋባ ሁኔታ ያስተውላቸዋል/**

ታዬ፡- ምንድን ነው? ዛሬ ስብሰባ እንዳለ ተነግሯችሁ አልነበረም? ሰዎቹ ሁሉ የት ገቡ?

ዮሴፍ፡- የምን ስብሰባ ነው ወንድም አለም?

ታዬ፡- ስለአባታችን ንብረት ለመወያየት ለዛሬ ቀጠሮ ቆርጠን ነበር፡፡ ለማንኛውም ቶሎ እንዲሰበሰቡ ግባና ንገራቸው፡፡ ሁሉም ያሉ ይመስልሃል **/ዮሴፍ ወደ ውስጥ ይገባል/**

ታዬ፡- **/ሜላትን በጥላቻ አይን እየተመለከታት/** እስቲ ተነሽና ወደ ውስጥ ግቢ **/ትነሣለች/** እየውልሽ ወደያውም ኑዛዜሽን ብትጨርሺ መልካም ይመስለኛ ል፡፡

ሜላት፡- **/እጅግ በፍርሃት/** ታይዬ የምህረት ፊትህ ላይቀየር እውን ጨክንክ? እኔ ግን በፍጹም እውን አልመስልሽ ብሎኛል፡፡

ታዬ፡- ስማሽ? ውቃቢዬ የአጋርሽን ማንነት ቢገልጽልኝ ኖሮ እስከዛሬ እንኳ የመቆየት ዕድልሽ የመነመነ ነበር፡፡ ምን ይሆናል ሁሉን ገልጸልኝ ይህን ምስጢር ነግኝ ፡፡ በአፋጣኝ ልትነግሪኝ ፈቃደኛ ባልሆንሽ መጠን የአሚሚትሽ አይነት እጅግ እየከፋ ይሄዳል እንጂ የሙትነትሽን ውሣኔ የማያሣጥፍ ታምር እንማይፈጠር እርግጠኛ ነኝ፡፡ ደንበኞቼ በኔ ላይ ያላቸው እምነት ይላላ ዘንድ አንቺን በመማር ተልካሻ ስህተት አልፈጽምም ውሣኔዬ አይታጠፍም አሁን ውጪልኝ **/ትክዝ እንዳለች ትወጣለች- ሜላት በወጣችበት በር ሶፊያ ትገባለች/**

ሶፊያ፡- **/ዞር ብላ ወደገባችበት በር እያየች/** ታዬ ምን ብለሀት ነው ሜሊ እንዲህ ክፍት ያላት?

ታዬ፡- ውቃቤ ርቋት ነው፡፡ እሺ አንቺ ትንሽ ልጅ ጉዞሽ እንደት እየሆነልሽ ነው?

ሶፊያ፡- አቦ ነጂስ ሆኖብኛል፡፡ ነገሩ ሁሉ በብር እጥረት መላው ጥፍት እያለ ነው፡፡ ታዬ እኔ አሁንስ የማደርገው ጠፍቶኛል፡፡ ለሠኣታት እንኳን እዚህ ሀገር መቆየት አልሻም፡፡ ይህን ፍላጐቴን የምትረዳልኝ አንተ ነህ እንጂ ወላ እማዬ፣ ወላ ዮሴፍ ሁሉም እንቅፋቶች ሆነውብኛል፡፡ እስቲ የእማዬ ክፋት ደግሞ ምን የሚሉት ነው? በሞላው ሃድራዋ ምናለ ባትጨክን? እኔን መሰል ሃምሣ ልጆች ወደፈለጉበት የሚያጓጉዝ ብር አላት ግን.....

ታዬ፡- ቆይ አትበሣጪ ሶፊ ምናልባት በዛሬው ስብሰባ አንድ ውሳኔ ላይ ከደረስን ተስፋ ይኖርሻል፡፡ የእኔንና የአነቺን ድርሻ ተጠቅመሽ ትሄጃለሽ ባይሆን ከሄድሽ በኃላ ትከፍይኛለሽ፡፡

ሶፊያ፡- ሃሣብህ በጣም ጥሩ ነበር ግን የሚሣካልህ ይመስልሃል?

ታዬ፡- ምን የሚያግደን ነገር አለ ብለሽ ትገምቻለሽ?

ሶፊያ፡- ኢያሱ.....ኢያሱ ኮ የሃብቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚ ነው፡፡ እናም ደግሞ እሱ አላህ ሲፈጥረው ለብጥበጣ ነው

ታዬ፡- ይህ እንኳ ባይሣካ የጥንቆላ ገቢዬ ቀላል አይደለም አንቺ ብቻ ጥቂት ቀናት ረዳቴ መሆን ሊኖርብሽ ነው፡፡

ሶፊያ፡- ኧረ ምንም ችግር የለም፡፡ ከዚህ ነጂስ ሃገር አውጥቶ ከዚያ ጀነቴ ለመግባት ያብቃኝ እንጂ እኔ እህትህ በደንብ እረዳሃለሁ፡፡.....የኢያሱን አፍ ግን በብር ያሠርክ መስሎህ እንዳትታለል፡፡

ታዬ፡- ሶፊ ሁሌም ክፉ ማሰብ ደግ አይደለም፡፡ ህሊናሽን ቀናውን መመኘት ልታስለምጂው ይገባል፡፡ ይልቅ እስቲ ግቢና ቶሎ በሉ በያቸው፡፡ ሰዎቹ በጣም ዘገዩ **/ሶፊያ ትወጣለች/**

/ታዬ ሣምሶናይቱን ከፍቶ ወረቀቶች ያገላብጣል፡፡ ያስባል፡፡ ከዚያም ዘግቶ ቁጭ ሲያደርግ ይገባሉ ከሜላትና ከኢያሱ በስተቀር/.....

ታዬ፡- ዛሬ በዚች ቦታ ስለግል ጉዳያችን እንድንነጋገር መልካም ፈቃዳችሁ ሆኖ በመሠባሠባችሁ ደስ ብለኛል፡፡ አባታችን በሞት ከተለየን ልክ ዛሬ ስድስት ወሩን አስቆጠረ፡፡ የአመት ግማሽ በመሆኑ ቀላል ጊዜ አይደለም፡፡ ውቃቢያችሁ አይደንግጥና አባታችን አስቀድሞ ምንም አይነት የውርስ ድልድል ሳያደርግ በአጋጣሚ ነው ያለፈው ታዲያ ዛሬ የተሰበሰብነው በሚዛናዊ ህሊና ተዳኝተን በእናታችን ምርቃት ማንም ምንም ሣይበደል ክፍፍሉን እንፈጽም ዘንድ ነው፡፡ እናቴ ሃና ምን ይመስልሻል?

እናት፡- እንዴ እኔ ምኑን አውቅ ብለህ? ዮሴፍዬ በል እንጂ ተናገር እንዴት ነው ነገሩ?

ዮሴፍ፡- እማዬ ምነው እንደሚያውቅ አድርገሽ ጠየቅሽኝ? እኔም ለነገሩ እንግዳ ነኝ

ታዬ፡- ተው እንጂ ዮሴፍ ደጋግሜ ስብሰባ እንዳለን ስለፈልፍ ትሰማ አልነበር እንዴ?

ዮሴፍ፡- ወንድም አለም ስለሃብት ክፍፍል መሆኑን በጭራሽ አላውቅም ነበር

ሶፊያ፡- አሁን ሆነም አልሆነም ተገቢውን ነገር ተማምኖ ማካሄዱ ላይ ነው ቁምነገሩ፡፡ ታዬ የተናገረው ነገር መቼም ግልጽና ግልጽ ነው፡፡

እናት፡- ዋና አስተባባሪዋ ለካ አንቺ ነሽ ይህ የተጠናወተሽ ጋኔን እስካለቀቀሽ ድረስ መቼም ቀና ለማሰብ በፍጡም አትችይም **/ኢያሱ ድንገት ይገባል/**

ኢያሱ፡- ፐ! እንዴት ያለ ክቡር ስብሰባ ነው? **/በጣቱ እየተራመደ ሄዶ ይቀመጣል/**

ሶፊያ፡- ኧረ ስብሰባውን .....ኤዲያ በጠበጠው!

ኢያሱ፡- **/በሶፊያ ድምጽ/** «ኧረ ስብሰባውን»....ይሄኮ በፖሊስ የሚጠበቅ የስብሰባ አዳራሽ አይደለም፡፡ የግል ጉዳይን በጋራ ለመነጋገር ይህን ያህል የሚያሠቅቅ ስብሰባ አይባልም፡፡

ታዬ፡- **/ኢያሱን ይገላምጥና በፊት በነበረው ሁኔታ ንግግሩን ይቀጥላል/** በመጀመሪያ ሁላችሁም ልታምኑበት ይገባል፡፡ ይህ ለቀጣዩ የቤተሰባችን ህልውና ወሣኝ እርምጃ መሆኑን ልንገነዘበው ይገባል፡፡

ዮሴፍ፡- ወንድም አለም እኔ ግን ክፍፍሉን አልቀበለውም ምክንያቱም የአባታችን ኑዛዜ አንድ መሆናችንን እንጂ መከፋፈላችንን አይደግፍም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም «መከፋፈልን የሚያመጣ እርሱ ጠማማ ነው ገንዘቡም የሃጢአት ሁለ ስር ናት» ይላል፡፡ ይልቅ ስለሁሉም የአባታችን የንስሃ አባት ዛሬም የቤተሰቡ ሁለ አባት ናቸውና እርሣቸውን አማክረን የሚሉንን ብናደርግ መልካም ይመስለኛል፡፡

ታዬ፡- ተው ዮሴፍ..... የውርስ ድልድል የአንድ ቤተሰብ የግል ጉዳይ እንጂ የወጪ ሰውን የሚጋበዙበት የክርክር ጭብጥ አይደለም፡፡ የንስሀ አባታችሁን በምንም መልክ ብታቀርባቸው የቤተሰባችን አባል የሚያደርጋቸውን አንዳች የዝምድና ሃረግ አትመዝላቸውምና ባትነግራቸው ይመረጣል፡፡

/በዚህ ጊዜ ሜላት ከውስጥ ትጣራለች «ዮሴፍ... ዮሴፍ...ስልክ» ዮሴፍ ይቅርታ ጥይቆ ይወጣል፡፡

ታዬ፡- ልጅ ሶፊያ ያባታችንን ንብረት ዝርዝር እንድታመጪ ነግሬሽ ነበር፡፡ እስቲ አንብቢልን

ሶፊያ፡- አንድ ገልባጭ መኪና፣ የ900,000 ብር የባንክ ቼክ፣ 20 የኪራይ ቤቶች እያንዳንዳቸው 100 ብር የሚያስገኙ፣ ቁጥሩ ያልተገመተ በሣጥን ያለ ብዙ ብር ከቡዙ በጥቂቱ ይህን ይመስላል፡፡

ታዬ፡- ታዲያ እነዚህ የተዘረዘሩትን ንብረቶች ቅድም እንዳልኩት በስነ-ስርዓት ለቤተሰቡ አባል ሁሉ መታደል አለባቸው፡፡

ዳንኤል፡- ጌታ ይክበርና ታዬ እኔ ግን ነገሩን በፍፁም አልደግፈውም ምክንያቱም ዛሬ ሁላችንም በእማዬ ስር ነው ያለው፡፡ ቤተሰቡን የምታስተዳድረውም እርሷ ናት፡፡ እናም ሁሉን ለእርሷ ትተን ይልቅ ሁላችንም ኢየሱሴን ተቀብለን.....

ኢያሱ፡- በቃህ! ይልቅ ለመጀመሪያው ሃሣብህ ጭብጨባ **/ያጨበጭባል/** እደግፈዋለሁ፡፡

ሶፊያ፡- ኢያሱ ምናለበት ህፃን ባትሆን? ስብሰባውን ብንጨርስበት

ኢያሱ፡- ምንድ ነው አንቺ!? ሃሣቤን መግለጽ አልችልም እንዴ? እኔ አሁንስ ታላቁ ትዕግስቴ እያለቀ ነው፡፡

ታዬ፡- የእኔም እንዳንተው! ቃለአባይ አትሁን! ይህን ሀሣብ ሊደግፍ የሚችል አንዳች ቁምነገር በውስጡ አላየሁበትም፡፡

ሶፊያ፡- እኔም

ታዬ፡- ብታብራሪው

ሶፊያ፡- ማለት በቃ! አንተ ይልከውን እንጂ ዳንኤል ያለውን በፍፁም አልደግፍም፡፡

ኢያሱ፡- ኤድያ... ኤጭ! ተጨባጭ ምክንያት ያለው ሀሣብ መሠንዘር በፍፁም አትችልም ይህቺ ልጅ.....አንተ ያልከውን ትክክል ነው፡፡ ዳንኤልን አልደግፈውም በቃ! ጥሎብኝ እንዲህ ጭፍን ያለ ነገር አልወድም፡፡

ታዬ፡- ተው እንጂ ኢያሱ አፍህ እንዳመጣልህ አትናገር

ኢያሱ፡- ትዕግስቱ ተሟጧል ህሊናዬ የታሰረበትን የጉቦ ገመድ በጥሳል፡፡ እንኳ ያሠርክበትን ገመድ **/የሰጠውን ብር አውጥቶ ይወረውርለታል/** ክፍፍሉን አጥብቄ እቃወማለሁ፡፡ ተገቢና ወቅቱን የጠበቀ ድርጊት አይደለም፡፡ finished

ታዬ፡- ጥሩ.....ምናለ?! ትረብሸን ዘንድ ውቃቢህ ሀይ ብሎ በአለንጋው ከሸነቀጠህ ምን ይባላል!? ለማንኛውም የምታደርጋቸው ድርጊቶች ሁሉ ስርዓትና ለዛን የጠበቁ ይሆኑ ዘንድ አበክሬ አስገነዝብሃለሁ..... እናቴ ሃና ለምን ቁርጥ ውሣኔሽን አታሣውቂንም?

እናት፡- እውን አሁን ቁርጡን ሳታውቀው ቀርተህ ነው? እንዲያው ሲፈጥራችሁ እኔን ለማስጨነቅ፤ እኔን ለማሰቃየት ሆነና ነው እንጂ.....ገና አባታችሁ ከመሞቱ ሀዘኑ ሳይለቀኝ እንዲህ አይነቱን ነገር መስማት እንደማልሻ አጥተኸው ነው?

ኢያሱ፡- እንጃለት!.....እንጃለት!

ዳንኤል፡- ጌታ ይክበር በቃ የእናታችንን ነፍስ አታስጨንቃት በጨለማው የኖረችው አንሷት እየጎነታተልን ደግሞ አናድማት...ተዋት

ሶፊያ፡- አንተ ደግሞ እንዲያው ዝም ብለህ ነው **/እየተቆናጠረተ ትወጣለች/**

ኢያሱ፡- **/እየተከተላት በራሷ ድምጽ/** አንቺ ደግሞ እንዲያው ዝም ብለሽ ነው፡፡

ታዬ፡- በጥባጭ እብድ **...../ይወጣል/** ኢያሱ ይስቅበታል

ዳንኤል፡-/**ወደ እናቱ ሄዶ ፊት ለፊቷ ይንበረከካል/** እማይዬ ብርሃን ይብራልሽ.... እባክሽ ጌታን ተቀበይ! ከዚህ ጭንቀትሽ ተላቀሽ እፎይ በይ በእናትሽ እማዬ ተይ?

እናት፡-/እንባ እየነቃት/ ከእመቤቴ ፍቅር ተለይ እያለ የሚመክር ፍሬን ላፍራ ዛሬ ጭራሽ አፍ አውጥቶ ጌታን ተቀበይ ይበለኝ? ጌትዬ ይህን ጉድ ሣትሰማ ተገላገልክ! በቤቴ እንደባዕድ እየተሣቀቅሁ እስከመቼ ነው የምኖረው? እመቤቴ ኧረ ልብሽ ይራራልኝ ይቅር በይኝ ማሪኝ ማሪኝ

ኢያሱ፡- ሾተላይ እናቴ ዛሬስ ሆድ ባሣት መሠል የልሷ ሀዘን በረታ ህቅታዋ ሞልቶ ገነፈለ፡፡ በቃ መረራት፡፡ አንተ የኢየሱስ ወታደር ክላሽንኮቭ ጠመንጃህን ከሜላት ወደ አናትህ፤ ጡት አጥብታ ያሣደገች እናትህ በነዚህ ስለትም ጥርሶችህ ባታቆስላት ምናለ?.....እንኳን አንቺ ለዘመናት አብረሻቸው የኖርሽ ቀርቶ የትናንቱ እኔንም ሆድ ባሰኝ ያንቺ ሾተላይ እናቴን ሠቀቀን እያየሁ ተንገፈገፍኩ አፍፍ.....

ዳንኤል፡- ጌታ ይባርክህና ኢያሱዬ እማዬን ደጋግመህ ሾተላይ ትላታለህ፡፡ ለመሆኑ ምን ማለትህ ነው?

ኢያሱ፡- እስከዛሬ ድረስ የኢየሱስ ወታደር ይህን ቃል አያውቅም ቢሉኝ እንዴት ላምን እችላለሁ? ዳሩ ወኔና ትጥቅ አልባ ወታደር በመሆንህ ንዝህላልነትህ ጊዜ ሠጥቶህ እንዲህ ያሉ ወርቃማ ቃላትን ማጥናት እንደማትችል ግልፅ ነው፡፡ ለማንኛውም ትርጉሙ እንዲህ ነው ሲሆን ብትጽፈው አይከፋም እማዬ ሾተላይ ናት፡፡ ምክንያቱም ወልዳ የሚሞትባት እናት ናትና በፍሬዎቿ ወግ ማዕረግ ለማየት ያልታደለች ምንዱብ ናትና ያንተ ቆሞ መሄድ የሞትህን ያህል ሰቀቀን የሆነባት...../**ዮሴፍ ይገባል/**

ዮሴፍ፡- ስብሰባው አለቀ እንዴ ኢያሱዬ?

ኢያሱ፡- ያለቀ ይመስለኛል ምንም እንኳ የመዝጊያ ንግግሩ ፉከራ ቢሆንም

ዮሴፍ፡- ምነው እማዬ አንገትሽን ደፋሽሳ?

ዳንኤል፡- ብርሃን ይወጣላት ዘንድ ጌታን እንደ ግል አዳኛ ትቀበል ዘንድ እየጠየኳት ሳለ ነው የገባኸው

ዮሴፍ፡- አንተ ራስህን ሣትመክር ህይወትና እድሜ የመከሯትን እናትህን ልትገስጽ ትነሣለህ? ተው እንጂ ዳንኤል ስንፍናህ ከልክ አይለፍ፡፡ አልባሌነትህ ወደ ጥፋት አይምራህ፡፡

ዳንኤል፡- ጌታ ይክበር እኔ የኢየሱስ ወታደር አልባሌ ነገርን ከላዬ ካስወገድሁ ቡዙ ጊዜ አለፈኝ

እናት፡- ምነው እመብርሃን ይህን ከምሠማ ኑሮዬን ከባለቤቴ ጋር ብታደርጊው **/የባለቤታቸውን ፎቶ እቅፍ አድርገው ወደ ስዕሏ እየተማፀኑ/**

ዮሴፍ፡- ተይ እማምዬ ምሬት መልካም አይደለም፡፡ እግዚአብሔር በስራው ሁሉ የተመሠገነ ይሁን ይኸች ያንቺን ቤት ገበና ቀርቶ በአለም ላይ ነግሶ የነበረውን የጥንተ አብሶ ሀጢአት ቅሪት ድቅድቁን ጨለማ ነው በመስቀል ላይ ነግሶ ብርሃን ያለበሰው፡፡ ለአፍታ የዲያቢሎስ ፈተና የልብሽን ጽናት ሊፈታ አይገባውም፡፡ ደግሞኮ ነገር ሁሉ ለመልካም ነው፡፡ እማምዬ የተዘጋጀልሽን ጸጋ በምን ታወቂያለሽ? ስራው የረቀቀ አምላክሽን እጅ በትዕግስት መጠበቅ ብቻ ነው አንቺ ያለብሽ

ኢያሱ፡- ጎሽ ዮሲ! አንተኮ ለዚህ ቤት የተሰጠህ በረከት፣ ቅዱስ መልአክ፣ የንስሀ አባት ነህ፡፡ እነዚህ ፣ እነዚህ ግን.....ኤድያ!

ዮሴፍ፡- ተው ኢያሱዬ እንደዚህ አትበለኝ ብዬህ የለ?

እናት፡- የአባትህን ሞት የረሣሁት ባንተ ነው፡፡ ልክ ነው አንተ ባትኖረኝ ምን ይውጠኝ ነበር?

ዮሴፍ፡- ምኑን ረሣሽው እማዬ? ይህን ጥቁር ልብስ እንኳ መች አውልቀሽ ጣልሽ?

ኢያሱ፡- ብራቮ! እኔም ልላት ነበር። በፍፁም አያምርብሽም እማዬ!

እናት፡- መች ለውበት ሆነና የለበስኩት ልጄ?

ኢያሱ፡- መቼም በማዘን ላይ ያለሽው ለቁም ሬሳዎቹ ነው።

ዮሴፍ፡- እስቲ ኢያሱዬ እማዬን ይዘሀት ወደ ውስጥ ግባ የደከማት ትመስላለች

ኢያሱ፡- ነይ ማም እንዲያውም እፈልግሽ ነበር። ደግሞ ዳንኤል ጥቂት ምክር ያስፈልገዋልና ብቻቸውን እንተዋቸው

ዳንኤል፡- **/ይዘምራል/**.....ዮሲ ለማም ያቀረብኩትን ግብዣ ላንተም ብደግምልህስ? እንክህ ጌታን ተቀበል! **/ፋታ/**

ዮሴፍ፡- እሱ አያሣስበንም በመጀመሪያ ስለሚላት እንድንነጋገር እፈልጋለሁ

ዳንኤል፡- **/መደንገጡ እንዳይታወቅበት እየጣረ/** በጌታ ስም ደግሞ ስለምን እንድናወራ ትፈልጋለህ? ሚላት ምን ገጠማት

ዮሴፍ፡- የምታውቀውን ለመድገም ያክል ፍሬ ይዛለች። የዝሙት ፍሬ! ወንድማችን ታዬ ሊገላት ይሻል። ስለዚህ አንድ መፈትሄ መሻት አለብን። አየህ እውነቱን ባወቀ ጊዜ ምናልባት ይራራላት ይሆናል። ማለቴ የቤተሰባችን ችግር መሆኑን ሲረዳ ምህረት ያደርግላታል ብዬ አስባለሁ እናም.....

ዳንኤል፡- በኢየሱስ ስም! ምን! ጀምረህ እስክትጨርስ ድረስ ያወራኸው ጣጣ ሁሉ ግልጽ አልሆነልኝም እንዲያው ያለህን ጥበብ ሁሉ ተጠቅመህ ብታብራራው እንኳ የሚገባኝ አይመስለኝም። ስለዚህ ርዕስ እንቀይር

ዮሴፍ፡- **/በተረጋጋ መንፈስ/** እባክህ ቆይ ዳንኤል መቅደም ያለበትን ቅድሚያ እንስጥ። ሚላት ማንነቱን እንኳን ለታዬ ለኔም ልተገለጽልኝ ፈቃደኛ አልሆነችም። ነገር ግን አስቀድሞ ከነበራችሁ ግንኙነት አንፃር ዛሬ ዛሬም ውልብ ከሚለኝ የጠበቀ ግንኙነታችሁ ስገምት አንተነትህን ለማወቅ ብዙ አልተቸገርኩም

ዳንኤል፡- ምን? ምን? በጌታ ስም! ተው እንጂ ዮሴፍ ስም አታጥፋ ጌታ ይቅር ይበልህ የሚላት ጉዳይ ከዛሬው የኢየሱስ ወታደር ቅንጣት ግንኙነት የለውም። አንዳች! እንዲህ አይነት ቀልድ አይዳዳህ

ዮሴፍ፡- እንዲህማ አይባልም፡፡ የአዳም የትናንት ማንነቱን በንስሃ እንባው ቢታጠበውም ከሱነቱ ጋር ግንኙነት ቢኖረው ነውኮ ጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያንን ሁሉ ፀዋተ ወመከራ መቀበሉ እንዲህማ ባይሆን ነቢያት ጽድቃችን እንደመርገም ጨርቅ ሆነብን ባላሉ፡፡ ተው! ብዙ ጊዜ አትፍጅ ግራ በተጋባ አማርኛህ ትክክለኛውን መፍትሄ አታድባብሰው ራስህን ገልጸህ ንገረው በቃ! መፍትሄው ይህ ብቻ ነው

ዳንኤል፡- ንግግሬ አንድና አንድ ብቻ ነው፡፡ በትናንት ማንነቴ አልጠየቅበትም፡፡ ስለምትለው ነገር አንዳች አላውቅም፡፡ ጌታ ይክበር!

ዮሴፍ፡- **/በአትኩሮት ያስተውለዋል/** ታዲያ የትላንት አንተነትህ ሰለባ ለምትሆን ነፍስም ግድ የለህም? ሚላት ከነሆዷ ጸንስ ትሙት? ወንድምህ ንጽህ ደም አፍስሶ በሀጢአት ላይ ሀጢአት ይጨምር? የታዬን ቁጡነት የተናገረውን ከመፈጸም ኩቶ እንደማይቆጠብ ታውቅ የለም? ጥቂት አይቀፍህም?

ዳንኤል፡- የኔ ኑሮስ ለሌሎች ምን ያክል እንደሚጠቅም አይገባህም?

ዮሴፍ፡- **/ፉታ/**.....ጥሩ! ለትናንት አንተነትህ ተጠያቂ እሆንልሀለሁ፡፡ በአሣማኝ አንበደትህ ተጠቅመህ ዮሴፍ እንዲህ አደረጋት ብለህ አስረዳው፡፡

ዳንኤል፡- ጌታ ይክበር! እኔም ብያት ነበር፡፡ በጨለማ ሣለሁ በፈፀምኩት ተልካሻ ስራ የዞሬ ብርሃናዊ ህይወቴ ከሚናጋ የጨለማውን ስራ ለጨለማው ግዞተኞች አስተላልፊልኝ ብዬ ነግራያት ነበር፡፡ ላትሰማኝ ከራሷ ጋር ተስማምታ ኖሮ ደረቀች፡፡ አሁን አንዲህ ነገሩ ሊቀል ጌታ ይመስገን አነግረዋለሁ፡፡ **/ዮሴፍ በማዘንና በተዘበራረቀ ስሜት ያስተውለዋል፡፡ ዳንኤል ወደ ውስጥ ይገባል፡፡/**

ዮሴፍ፡- ይህችኮ በሱ ቤት ትልቅ መስዋዕትነት ናት፡፡ ኢምንትነቷን፣ ምናምንቴነቷን ቢረዳ ምን ነበረበት? የጨለማው አለም ግዞተኛች?! ህ.....! የህይወቴን ብርሃን በተግባር እሰብከዋለሁ፡፡ ያኔ ብርሃኑ የት እንዳለ ይገባው ይሆናል፡፡ ኦ.....ፍ.....ፍ አባዬ አደራህ ከባድ ነው፡፡.....ጌታ ሆይ እባክህ በቃ በለን፡፡ የየዋሀዋን እናቴንም ሀዘን መቋጫ አብጅላት፡፡ አንድ ቀን እንኳ እፎይ ብላ በጎኗ ሣትተኛ ዘመናት ተቆጠሩ፡፡ አቤት...../**መብራት ይጠፋል/**

ትዕይንት ፫

በደብዛዛ ብርሃን ኢያሱ ጥግ መሬት ላይ ከተጋደመበት ብድግ እያለ የያዘውን ሻማ እያስተዋለ ይናገራል፡፡

ኢያሱ፡- የቀን ክፉ! የቀን ጎደሎ! እኔን በሰዎች ፊት እብድ አስመስላ የከሰተች የቀን ጣይ! ኤድያ!.....ምነው አንቺ ከቀናት መሀል ድራሽሽ በጠፋ? ደምስሰው ባዶ ባደረጉሽ ከአመታት፣ ከወራት፣ከሣምንታት ጋር ባትቆጠሪ ተቆርጠሽ በተቀበርሽ! ክፉ! የቀን ክፉ! ዳላስ ገነቴን አስነጠቅሽኝ፡፡ ባንቺ ጀምበር ባንቺ መአልት በወጣች ፀሀይ ብርሃን ሰዎች አይናቸውን ገልጠው በውስጤ የሌለን እብደት አዩብኝ፡፡ ምን ነበረበት ያኔ አንቺ ጨለማ በሆንሽ? ሰዎች ባልተሞኙ እኔንም ባልገደሉኝ እብድ ብለው ባላደሙኝ፡፡ ኤድያ! ክፉ! የቀን ክፉ! ሰዎች ቀን ይሞት ይሆን? እስቲ በምድር ሞት ንገሩኝ ቀን ይሞታል? አቤት ቢሞት ይህች ውግዝ ከመአርዮስ ቀን የመተች ለታ የማደርገው ፌሽታ፣ የምቅመው ጫት፣ የምጠጣው ውስኪ፣ የምቆርጠው ጮማ አቤት!.... **/ወደኃላ እያፈገፈገ ይወጣል፡፡ መብራቱን ሙሉ በሙሉ ይበራል፡፡ ታዬ ያልተቀደደ ፖስታ ይዞ ይገባል፡፡ በችኮላ እየቀደደ ማንበብ ይጀምራል፡፡ የሜላት ድምጽ.../**

«.....ታዬ አማራጭ የሌለው ውሣኔ እንደሆነ ባላውቅ አላደርገውም ነበር እርግጥ ላንተ በቀል ለተጠማች ነፍስህ መጥፎ አጋጣሚ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የናፈቀችውን ሞት ለማየተ አልታደለችምና አይገርምም? ሙት ከሞት አመለጠ.....ታዬ ሙት ነኝ ግን ሞትን እሻሻለሁ፡፡ ምስኪን ምንም ምን የሌለኝ አንድ ለጣዬ መሆኔንም ያወቅሁት አንተ የመግደያ ጦርህን በሰነዘርክብኝ ወቅት ነው፡፡ ለካ ያንተ መኖር አንድ መሆኔን አስረስቶኝ ነበር፡፡ ሰፊው አንተነትህ የማይደርቅ የገንዘብ መፍለቂያ ምንጭህ በአጠቃላይ የተሳካ ስለነበር ሁሉን አስረስቶኝ ኖሯል፡፡ እንዳገኘሽኝ አንዴም ሳታውቅ ተለያየን፡፡ ጠንካራ ፣ ለቆምክበት አላማም ጽኑ መሆንህን ይመሰክራል፡፡ የት እንደምሄድ ባላውቅም ብቻ ወጥቻለሁ ለበደል በደልን እጨምር ዘንድ የጠየከኝን ልገልጽልህ ባለመቻሌ አዝናለሁ፡፡.....ታዬ እንገናኝ ይሆን ?!.....»

ታዬ፡- አዎ! እንገናኛለን! ያኔም እገልሻለሁ! ቃሌን የማጥፍ እንከፍ አይደለሁም፡፡ ወይኔ! **/ዳንኤል ይገባል/**

ዳንኤል፡- ጌታ ይባረክ ታይዬ እንደምን ውለሀል?

ታዬ፡- ደህና አንተ ደህና ውለሀል?

ዳንኤል፡- ጌታ ይክበር ደህና ነኝ የሰሞኑ መረበሽህ ረበሸኝ መጨነቅህ አስጨነቀኝ፡፡ እንደምነህ ልልህ ብቅ አልኩ

ታዬ፡- ሰሞኑን ውቃቢ ርቆኝ ከስራ ተለይቻለሁ፡፡ ይህ ሲያምኑት የማይታመን ከጂ ትውልድ ልቤን አስመርሮት ሁሉም ምስቅልቅል ብሎብኛል፡፡

ዳንኤል፡- ጌታ ይክበር ተወው የራስ ገመናን ሸፋኝ ከራስ ውጪ ማን ሊመጣ ሁሉን ልትረሣው እንደሚገባህ የምታውቀው የጠላትህን ቅርብነት በተረዳህ ወቅት ነው፡፡

ታዬ፡- የምን ቅርበት ነው የምታወራው? ከቅርበት አልፎ ግማሽ አካሌ ያልኳት ሳላገባት ሳላውቃት ቃል ገብቼ አብራኝ የምትኖር እጮኛዬ ናት እንጂ

ዳንኤል፡- የምልህ የሷማ አንዴ የታወቀ ነው፡፡ ግን እኔ የማወራው ስለዋናው ደመኛህ ነው፡፡

ታዬ፡- እሱን ነው እኔም ለረዥም ጊዜ ስሻው የኖርኩት በተለይም ዛሬ በተፈጠረው ክፉ አጋጣሚ የወንጀለኛው ቅጣት በእጥፍ ጨምሯል፡፡

ዳንኤል፡- በጌታ ስም! ይህንንማ ልታደርገው አትችልም ምክንያቱም የራስህ ገላ ነውና እንደራስህ ምስጢር ልትጠብቀው ይገባል፡፡

ታዬ፡- አፋ! አጉል ዳርዳር እያልክ ልቤን አታንጠልጥለው ማነው?

ዳንኤል፡- ወንድማችን ዮሴፍ! ጌታ ይባርከውና ዮሴፍ ይህን አደረገ ሆኖም ሆነም! ተደረገም! ሜላትንም ከሞት አዳነ ለሁለቱም አለም እንዳይጨልምባቸው ምናልባት ከቆረጠች የአንዱን ጨለማ ጣዕር አቅለለላት በቃ ሆነም ጌታ ይክበር፡፡

ታዬ፡- ሂድ.....ሂድ! ውጣልኝ! **/ዳንኤል ይወጣል/** አቤት!....አቤት! ጥፋት! ደጋግመው ሲንሾካሾኩ አለመጠርጠሬ...ለካ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ፍቅራቸውን እየተወጡ ነበር?! አቤት!.... ብምረው አትማሩኝ ባላጠፋው አጥፉኝ አቤት! **/ሶፊያና እናት ይገባሉ ምንም እንዳልተፈጠረ ቁጭ ይላል፡፡/**

ሶፊያ፡- ደህና ዋልክ ታዬ?.....አስደንጋጩን ወሬ ሰማህ?.....ሜላትኮ ጠፋች!

ታዬ፡- አዎ ጠፋች

እናት፡- ውይ ላንተም ጥፋልህለች እንዴ? ነው ወይስ ሳራ አነበበችልህ?

ታዬ፡- ለኔም ጽፋልኝ ነበር

አናት፡- ምነው እንደዚህ ቀዝቀዝ ማለትህ? ምንም ቢሆን እጮኛህ አልነበረች? ክፉ ቢገጥማት ያንድ ጊዜ ስህተቷን በጐረምሣ መደፈሯን እንደትልቅ ጥፋት ቆጥረህ ዛሬ እንዲህ ልብህ ድንድን ማለቱ ለምን ነው? እኔም በዘሬ የለብኝ፡፡ አባትህም ቢሆን ሆደ ቡቡ ነበር፡፡

ታዬ፡- ተይኝ እስቲ እማዬ ተይኝ! የማንም ምንነት ለኔ አንዳች አይፈይድልኝም፡፡

ሶፊያ፡- ታዬ እውነት በአላህ? ከአንጀትህ በሚሊ ጨከንክ?

ታዬ፡- እስቲ ተውኝ በቃ! ምን ነበረበት አሁን በመጣችና አጠገባችሁ የማደርጋትን ባጣያችሁ! ተውት አሁን ግድ የለኝም፡፡ የበቀሌን ጥማት በከፊልም ቢሆን የማረካበት አግኝቻለሁ፡፡

እናት፡- የምን በቀል አንተ?! ኧረ እንዲህ ያለ ሰይጣናዊ ጀብደኝነት አይሰማህ! ኧረ ሁለንተናህ በክፋት የታጠረ መስሎ ታየኝ። ምንድነው የምታወራው?

ታዬ፡- ልጅሽ ዮሴፍ! የኔና የሷ ወንድም ዮሴፍ ነወ ሚላትን የደፈራት ጎረምሳ እናም ከዚህ በኃላ ያለችው የመጀመሪያዋ ግንኙነታችን መሞቻው ትሆን ዘንድ ውቃቢዬ አዞኛል። **/እናት ራሳቸውን ስተው ይወድቃሉ ታዬ እየሮጠ ይወጣል። ሳፊያ እናቷን ደግፋ በጭንቀት ትርበተበታለች ዮሴፍ ከውጭ ሆኖ አሾልኮ ይመለከታል። ቀስ ብለም ወደ ውስጥ ይገባል/**

ዮሴፍ፡- ምንድነው እሱ ሣራ? እማዬ ምን ሆነች?

ሶፊያ፡- ኧረ.....ኧረ.....ታ...ዬ የሚሉን ጉዳይ ሰምቶ ሊገድልህ ይፈልጋል። ኧረ **/ወደውጭ ትመለከታለች/**

ዮሴፍ፡- አይዞሽ ሣራ አትጨነቂ.....እግዚአብሔር ከፈቀደው ቀን ውጭ የሚሆን አንዳተ ነገር የለም። ይልቅ እማዬ ምን እንደሆነች ብትነግሪኝ...../**እናት ይነቃሉ፣ ያማትባሉ/**

ሶፊያ፡- ይህንን ክፉ ወሬ ስትሰማ ራሷን መቆጣጠር አቅቷት ነው። አሁን ታዬ ከዚህ ነበር እዚሁ እንደሚሆንም ቅንጣት ያህል ጥርጥር የለኝም ስለዚህ.....

ዮሴፍ፡- እማዬ ምነው?

እናት፡- ዮሴፍዬ እውነት ብቻዬን ነኝ? እውነት የምሰማው ትክክል ነው? ወይስ የሰይጣን ሹክሹክታ እባክህ ልጄ በጡቴ ይሁንብህ በፍጥነት ነግረሽኝ ከዚህ ተሰወር

ዮሴፍ፡- ሀሰትም እውነትም ነው። እማዬ አንቺ ብቻ በርቺ እባክሽ ሳራ ቀና አድርገሻት ወደ መኝታ ቤቷ ውሰጃት ደህና ዋሉ **/ስዕለ ማርያምን ከግድግዳው ላይ አንስቶ በፍጥነት ይወጣል/**

እናት፡- ዮሴፍዬ ኧረ ተው ልጄ.....ተው ዮሴፍ እመቤቴ እናቴ ምነው ፍቅርሽ ራቀኝ? ኧረ አለሁልሽ በይኝ ጨለማ ውስጥ ስወድቅ አይገድሽም? **/ኢያሱ ይገባል/**

ኢያሱ፡- **/ለጥቂት ጊዜ ሁኔታውን ያስተውላል። እናቱን በተቀመጠችበት ሄዶ እየደባበሰ/** ዛሬስ እማዬ የትዕግስት መቀነቷን ፈታች ተረታች መሠል! እኔ እንዲህ ቅዝቅዝ ልበልልሽ ይገፍሽ ወዴት ልብረር? ማንም ወደማያገኝ ስፍራ የት ይገፍሽ ልግባ?.....እኔ ደግሞኮ በሽተኛ ነኝ ውሸት ተደጋግሞ ሲነገር እውነት ይሆናል እንዲሉ አሁንስ እብደቴ እያየለ መጥቷል.....No! ግን በፍፁም ላንቺ አላንስም **/እጀጌውን ይሰበስባል/** አንቺ ሶፊያ ማም ምን እንደሆነች አትነግሪኝም?

ሶፊያ፡- አሁን እውነት የሚላትን መጥፋት ሳትሰማ ቀርተህ ነው?

ኢያሱ፡- በፍጹም! ዘር ስለመቋጠሯ በቀር አንዳች የማውቀው ነገር አልነበረም። **/ፋታ/ /ድንገት/** ታዲያ ሚላት ጠፋች ምን ይጠበስ?

ሶፊያ፡- አትሳደባ! ለመሆኑ ምን እንዲጠበስ ትፈልጋለህ?

ኢያሱ፡- የጠየኩሽን ጥያቄ ነው እንዴ የምትደግሚው? ምን ይጠበስ ተባለ?

ሶፊያ፡- ታዲያ ችግሩ ዘር ከማን ቋጠረች የሚለው ነው እንጂ...

ኢያሱ፡- ማን ይሁን ተባለ?

ሶፊያ፡- የታዬ ውቃቢ ዮሴፍ ላይ አቃጭሏል

ኢያሱ፡- እግዚኦ ውሸት! እግዚኦ ሀሰት! እማም!ማም!

እናት፡- አቤት ልጄ

ኢያሱ፡- ጆር የለኝም በይ ለዚህ ውሸት ደንቆሮ ነኝ በያቸው። ምስኪኑን በግ ለመወንጀል የተጠነሰሰ ሴራ ነው

እናት፡- ኢያሱዬ! እኔኮ ዮሴፍ ነወ ግራ ያጋባኝ ነገር እንዴት ነወ ብለው ሀሰትም እውነትም ነው ብለ ልቤን ክፍሎት ወጣ

ኢያሱ፡-ፐ! ከዮሴፍ አንደበት መች ይሆን የሀሰት ቃል የሚወጣው? እውነትም ወሸትም ነው ብሎ በጥሩ አማረኛ ገለጸው በጥቅሉ እውነት ሲሆን በተናጥል በርሱ ላይ ብቻ ማነጣጠሩ ግን በፍጹም ሀሰት ነው። በአንድ አበራክ ክፋይነታቸው የጋራ እውነት ሲሆን ሁሉን በዮሴፍ ላይ መጫኑ ግን ያገጠጠ ሀሰት ነው ማም ሾተላይ አይደለሽም ያንዱ ጽንሽ ፍሬ ጸንቷል።

ሶፊያ፡- **/ነጠል ብላ/** ያ አላህ! ምናለ ከዚህ ውጥንቅጥ ህይወት ብትለየኝ? ምናለ ከዚያ ጀነቱ ብትከተኝ?

ኢያሱ፡-ኤድያ! ክፉ ህልመኛ ዘላለም እንዳለምሽ ትኖሪያለሽ። አንዴም ከገንዘብ ጥማትሽ ሳትረክ እድሜሽን ገፋሽ አሁንስ አንቺን በማየት ብቻ ብሮችን ልጠላ ነው። ለዚህ ሣይሆን አይቀርም እንደወረቀት የምበትናቸው

ሶፊያ፡- አንተማ እድሜ ለማማ ተርፎሃል

ኢያሱ፡- የአንቺስ እናት አልነበረች? ፍላጎታ ከፍላጎትሽ አልስማማ ብሏት ቢመራት አንጀቷ ቆረጠ እንጂ ለገንዘብ የተፈጠርሽ አድርሽ አታስቢ። ገንዘብ ነው ላንቺ መገልገያነት የተፈጠረው ለመሆኑ ሃይማኖትሽ ምንድነው?

ሶፊያ፡- ያንተን ንገረኝና እነግርሃለሁ

ኢያሱ፡- ተጠያቂ እንጂ ጠያቂ ማን አደረገሽ? ለማንኛውም የኔ ሃይማኖት እውነት ነው

ሶፊያ፡- የኔም ውሸት አለመሆኑን አውቃለሁ።

ኢያሱ፡- እንግዲያውስ ምንድነው?

ሶፊያ፡- ውሸት አለመሆኑን ብቻ ነው የማውቀው.....በቃ አትጨቅጭቀኝ ይልቅ እማዬን ወደመኝታቤት አስገባት

ኢያሱ፡- እሺ የመጨረሻ ጥያቄ ልጠይቅሽ አሁን ሶፊ እንዳው በአባባ ሞት እ.....የመቶ ብር ኖት ፊት ለፊትሽ ሰቅለው ጎንበስ ቀና እያልሽ ስገጅለት ቢሉሽ አታደርጊውም?

ሶፊያ፡- እህስ! ታዲያ ገንዘብ ጎንበስ ቀና ሣይባል የማታፈስ ሲሳይ አይደል።

ኢያሱ፡- **/እናቱን ለመደገፍ እየሞከረ/** ባክሽ ያንቺ መታመኛ፣ ያንቺ ሀይማኖት ገንዘብ ነው። ማም ነይ ተነህ ነይ ባክህ መኝታ ቤት እንግባና የድሮ ወግ ትተርኪልኛለሽ! ተነሽ።

እናት፡- ቆይ ኢያሱዬ ጥቂት ልረፍ

ኢያሱ፡- ጥሩ ማም! ከሶፊ ጋር ጣፋጭ ተረት ልሰልቅ.....No! ተረት አይደለም ቁም ነገር ነው። ሶፊ 9ኛ ክፍል ስለባርያ ንግድ አልተማርሽም?

ሶፊያ፡- ሊያውም እንዳንተ በትምህርቴ ንዝህላል እንዳልነበርኩ እማዬ ምስክር ናት። አቤት መምህራችን ስለባራዎቹ ስቃይ የነገረን መቼም አይረሳኝም።

ኢያሱ፡- **/ከት ብሎ ይስቃል/** ታዲያ ዛሬም ጥሩ የባርያ ንግድ ነውኮ እየተካሄደ ያለው። ያኔ በዱር በገደሉ እየታደኑ፤ በዲሞትፈር ጥይት ጩኸት እየተማረኩ ነበር ባሮቹ የሚጋዙት ዛሬ ደግሞ በአቦ፣ በገብርኤል የጂዳ ያለህ ኡኡኡ.....ግራ አይኔን አጥፍታችሁ በቀኜ እየመራችሁ ውሰዱኝ ማለታችሁ ብቻ ነው የሚለየው እንጂ። ቁጭ! አንድ።

ሶፊያ፡- አሁንስ ልክህ እንደተሰወረብህ በፍጹም መመጠን እንዳቃተህ ግልጽ ነው። እማ አቅም አንሷታል እትቆጣኝም ፣ታዬም እጮኛው ኮብልላበታለች ስለዚህ ለኔ ግድ አይኖገረውም ብለህ ትለፋደዳለህ?

ኢያሱ፡- እማም አቅም እንዳነሣትማ የታወቀው እኔን ጨዋ ልጂን ባልግ ብላ መቆጣት ስለተወች ሳይሆን እንዲያው እንዲህ ውጭ፣ውጭ ብሎ የቆመ ልብሽን የቁጣ ናዳ አውርዳበት ቁጭ ማድረግ የተሣናት ለታ ፣ታዬም እኔን መቆጣት ያቆመው የጥንቆላ ገቢው አይሎ አይኑ በተጋረደ ጊዜ ነው። ተይ ባክሽ መች አጣሽውና! ማም ነይ ተነሽ በቃ ነገሩ ሁሉ አላማረኝም ወደውስጥ እንግባ **/ያነሣትና ተያይዘው ይወጣሉ/**

ሶፊያ፡- /ከወጡ በኃላ/ መርዘሃ እብድ! ምላሳም! ሴት!....ወይኔ! ፊቱ ቢያገኘኝ እንጂ መች እንዲህ አፉን ይከፍትብኝ ነበር? ናፈቅሽኝ እያለ የደብዳቤ መአት ያዥጐደጉድልኝ እንዳልነበር...../**ታዬ እየፈጠነ ይገባል/**

ታዬ፡- ሶፊያ የት እንዳለ ልትነግሪኝ ፈቃደኛ አይደለሽም?

ሶፊያ፡- ኧረ እኔ አላየሁትም/**ጥቂት ቆይታ/** .....ታዬ! ብዙ ሰዎች እየመጡ ተመልሰዋል ትንሽ ቆይተው እንደሚመጡ ያስታወቁኝም ጥቂት አይደሉም::

ታዬ፡- በይ እስቲ በር ላይ ቆመሽ ተጠባበቂና የሚመጡትን ሰዎች አስገቢያቸው ዛሬ ጥቂትም ቢሆን መስራት አለብኝ:: **/ይልና ልብሱን ይለብሳል፣ ኮቱን አውልቆ ይሰቅላል:: የተሰቀለውን ጫት አውርዶ ያስተካክላል፣ያነጣጥፋል፣ማጨሻ ያቀርባል/** እንዴት ነው ብቅ የለ የለም?

ሶፊያ፡- ከሩቅ ሰው ይታየኛል ወዲህ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም:: ለማንኛውም በሩን ገርበብ አድርገው:: መናፍስቶችህን ጥራ:: እጣኑን አጢስ ቶሎ በል::

ታዬ፡- ቱ.....ቱ.....ቱ.....አማን አማን ብለናል:: አርሒቡ በናንተው መጀን ሃይላችሁ ይጋርደን:: እሣታችሁ አይፍጀን ልቦናችንን አብሩልን የሰውን ችግር ከስቱልን መፍቴውንም አስጨብጡን አርሂቡ አማን.....አማን...አቦል ጀባ ቀዋ ጀባ ይመጣብን ግቡ ግቡ **/ሶፊያ እንግዶች ታስገባለች/**

ሶፊያ፡- **/በዛ ያሉ ሰዎች ስለመጡ የተወሰኑትን ታስገባና/** ጌቶች ስደራረብባቸው ሀድራው ይርቃቸዋል:: አድባሯ ትቆማለች:: እናም ከወደሰገነቱ ገባ በሉና ከድካማችሁ አርፋችሁ ተራ ጠብቁ ፈጣን ስለሆነ ቶሎ ትጠራላችሁ:: **/ይህን ተናግራ ወደ ውስጥ ትገባለች:: ከጥቂት ጊዜ ቆይታ በኃላ ሰዎች ቀስ በቀስ ይወጣሉ::/**

ሶፊያ፡- ብዙ ሰዎችኮ ቀርተዋል

ታዬ፡- ይደሩ....የኔ መድሀኒት ያለደጅ ጥናት አይገኝም እጅግ በጣም ውድ ነው::

ሶፊያ፡- /**ቁጭ እያለች**/ የሆነስ ሆነና ታዬ የጉዞዬን ነገር እንዴት አደረግሽው?

ታዬ፡- እርግጠኛ ነኝ በቅርብ ጊዜ ትሄጃለሽ ሰሞኑን አንድ አጋጣሚ ይከሰታል ብዬ አገምታለሁ የጋራ ስራ ቢሆንም ሀላፊነቱ የኔ ስለሆነ የህይወት ካሣ እንኳ ቢያሻው ተጠያቂው እኔ ስለሆንኩ በሚገኘው ገቢም ተጠቃሚ /አዛዥ/ እኔ ነኝ ካንቺ መጓጓዣ አልፎ ለብዙ ቁምነገሮች የሚተረፍ ገቢ እንደማገኝበት እርግጠኛ ነኝ::

ሶፊያ፡- አላህ ይርዳህ በርታ!

ትዕይንት ፬

መጋረጃው ሲገለጥ በጨለማ ቤት ውስጥ ኢያሱ የሌሊት ልብሱን እንደለበሰ ወዲያ ወዲህ ይላል። መብራቱን በዳሰሳ ፈልጎ ያበራዋል።

ኢያሱ፡- ነፍሣት በዝምታ በአርምሞ ተውጠዋል። አካልም ከድካሙ ያርፍ ዘንድ በብርድ ልብስ፣ በአንሶላ ተጀቡኖ በአልጋ ላይ ይንፈላሰሳል። የአንዳንድ ምስኪን አካል ደግሞ ከደጅ የምድሩ ቅዝቃዜ ከላይ ውርጩ እያፏጨ በረዶ ሆኗል። ምድር እራሷ አንቅራ የተፋቻቸው ይመስል እየጉረበጠች አልመች ብላቸዋለች። ትናንት ወደ ምዕራብ የጠለቀች ጸሀይ ዛሬ ከወደምሰራቅ ብቅ ልትል ዝግጅቷን ጨርሳለች ለታዬም ፣ ለዳንኤልም ፣ለሶፊያም እኩል ከእማዬና ከስደተኛው ዮስፍ ጋር ታበራላቸዋለች ሰው ከሰው አትመርጥም ለሁሉም አንድና አንድ ናት።

ቀኝ እጁ ግማሽ አካሌ ያለችው አባታችን የተለያት እማዬ አሁንስ ማቃሰት ጀመረች ጣር ጭንቋ ሞልቶ ሊገነፍል እየቃጣው ነው። ርግቧ ማም በአንድ ክንፏ መብረር እንደማትችል ገባት መሰል ዛሬስ አንገቷን ደፋች ገመናዋ እጅ ወደላይ ብሎ ማረካት የትዕግስት ትጥቋን አስፈታት። አንድ ፍሬ አለኝ የማታ ማታ እፎይ መባያዬ ብላ ከተመካችበት ሶተላይነቷን ከሻረላት ዮሴፍ ይለያት ዘንድ ያቀደው እሳቤው ተሳክቶለት አስኮበለለባት በዚህ ቤት የነገሰው የእማም ተቃዋሚ ስውር ቀንዳም ጠላት፤ ሌሎቻችን እንደላባ በውስጧ በዙሪያዋ የበቀልን ፍሬዎቿ ግን ሰው ላንሆንላት ልጆች አሉኝ ብላ ከምትጽናናብን ይልቅ ሙቶች ወለድኩ ብላ እንድትፀፀትብን የምንሻ ከንቱዎች ሆንን **/ከውስጥ ረጅም የማቃሰት ድምጽ ይሰማል/** እኔን ማም ድካሟ በረታ ጣር ጭንቋ አየለ። አይዞሽ! ጸሀይ መውጫዋ ደርሷል ከብርሃን ጋር ሲሆን ጭንቁም በሀሣብ መብሰክሰኩም ይቀንሳል። እማም ብርድ ልብስ ውስጥ እየተንከላወሱ በጨለማ ተውጠው ምንም ቀና ነገር አይታሰብም ሌሊት በመልካም ሀሣብ የሚሞሉ ቤታቸውን እንደደጀሰላም ያጸዱ ፍጡራን ብቻ ይመስለኛል። ይህን ማቃሰት እየሰማሁ እንዴት እንቅለፍ ይውሰደኝ? ምናምንቴነቴን እንዴት በእንቅልፍ አሸጌ ልያዘው?...../**በድንገት ጮክ ብሎ**/ እንዴት ተስማሙ የህብረታቸውን አስቃቂ ዜማ አዳማቂ ንግስታቸውን አባሮ ብቻውን ሲያገኙ እንዴት ዝም አሉት? የጽልመት ንግስታቸው ወኪላቸው ታዬን ሳይተናኮሉት ሰላማዊ እንቅልፉን ይሰልቅ ዘንድ እንዴት ቸል አሉት?....አብሯት አጫፋሪ፣አድማቂ፣አሟቂ፣ ንግስታቸውን ሚላትን የትም ጥሏት...እኔ አላምንም/**ይስቃል**/....በፍጹም.....ታዬ.....ታዬ.....ደግም ነግቷል። የጠዋቷን ጀንበር ቢያይዋት ምንም አይደል የምስራች ጸሐይ ወጣች ልበላቸው። ሁሉም ይነሱ። ዳንኤል.....የኢየሱስ ወታደር፣ሶፊያ.....ተነሱ.....ጸሐይ ወጣች.....ታዬ **/እየሮጡ እናት፣ሳፊያ፣ዳንኤል ከመኝታቸው ተነስተው ይገባሉ/**

ዳንኤል፡- በጌታ በኢየሱስ ስም.....! ነካ አደረገህ እንዴ? ነው ወይስ መንፈስ ወረደልህ?

ኢያሱ፡- ኤድያ!...እማም አንዴም እንቅልፍ ባይኗ አልዞረም፡፡ እናንተ ግን ያለሀሣብ ታንኮራፋላችሁ እስቲ ይብቃችሁ ሁላችንም ይብቃን ብንነቃ ይሻላል ደግሞ የማታዳላዋን ለሁሉ እኩል አንድ ሆና የምትወጣውን የጠዋት ጸሐይ በጋራ ሆነን እንደምን አደርሽ እንኳን ደህና መጣሽልን እንበላት ብዬ ነው፡፡ የቀሰቀስኳችሁ

ዳንኤል፡- ግን በጤናህ ነው? ራስህ ትክክል ስለማሰቡ እጠራጠራለሁ

ሶፊያ፡- እያየኸው? እንዴ! በጤናው ቢሆን እንዲህ እየጮኸ አገር ይበጠብጥ ነበር? እማም ታዬ ወይም ደግሞ እኔንና ዳንኤልን አልነበረም ጠበል ለመውሰድ ማሰብ! ጨርቁን የጣለልሽ ይኸው

ኢያሱ፡-ተያት እስቲ! በኔ ላይ ያላትን ጥቂት እምነት አታጨልሚባት እማም አሁን አሁን ዝም ማለትን ነወ የምትመርጠው ዝም ትበልበት አትጨቅጭቂያት ይልቅ ሶፊ ሺሆች እቤት አላደሩም እንዴ?

ሶፊያ፡- አላደረም ትናንት ከሰዓት በኃላ የወጣ ነው

እናት፡- ለመሆኑ የት እንደሚሄድ ነግሮሻል?

ሶፊያ፡- ኧረ በፍጹም

ኢያሱ፡- አይ አንቺ ርግብ፡፡ ልብሽ መቼም በሀሣብ መክነፋን አትተው ምን ብንተውህ ብናስመርርሽ ስለኛ መጨነቅ አትተይ፡፡ **/በድንገት በሀይል ይቆጣና ዳንኤል ላይ ያፈጥበታል/** አንተ ዳንኤል ለማም ሰው አትሆንላትም? የምትልህን ተቀብለህ ምሬትሽ ይብቃ የልብሽ ቁስል ይሻር አትላትም?/**በዚህን ጊዜ ዮሴፍ በበር አካባብ ወደውስጥ ያዳምጣል፡፡ ቀስ ብሎ ጠጋ ይልና፡፡ «ኢያሱ» እያለ ይጣራል/**

ዮሴፍ፡- እኔ ነኝ.....ታዬ አለ?

ኢያሱ፡- የለም! **/ይልና በፍጥነት እናቱ ፊት ይንበረከካል/** እማ ንጹሁ ሽፍታ ከስደቱ ተምልሷል ናፍቆ ነው መሰል ዮሴፍ መጥቶልሻል

እናት፡-የታል ልጄ?...../ብለው ዮሴፍን አቅፈው በስስት ይስሙታል/ ልጄ ዮሴፍዬ አስችሎህ እንዴት ይህን ያክል ጊዜ ጠፋህብኝ? አልተውሽም የአባባ አደራ አለብኝ ትለኝ አልነበረም?

ኢያሱ፡- በሉ እስቲ ቆጭ ብላችሁ ወሬያችሁን ቀልጠፍ ቀልጠፍ አድርጉት እኔ በር በሩን አያለሁ፡፡ ልክ እንዳየሁት እጠቅስሀለሁ ከዚያም.....ከዚያም እማምዬ ሆድ ተመልሰህ ትገባለህ እንጂ እማማን ለአውሬ ጥለሀት ከእንግዲህ እንድትሄድ በጭራሽ አልፈቅድም፡፡

ዮሴፍ፡- እያሱዬ ና ቁጭ በል ከእንግዲህ እግዚአብሔር የፈቀደወ ይሆናል እንጂ ከቤቴ አልወጣም ከሞት አልሸሽም እስከዛሬ ወንድሜን ፈት ለፈት ተጋፍጨ ወንድነቱን አልፈትንም ብዬ እንጂ ከናንተ ርቄ የማየው ስቃይ ቀሎኝ አልነበረም፡፡

ዳንኤል፡- ጌታ ይባርክህ! እንኳን ለቤትህ ያበቃህ፡፡ ዛሬ ቤቱ እንዲህ መልክ መልክ መያዝ በጀመረበት ወቅት ያንተም ብቅ ማለት እጅግ ደስ ያሰኛል፡፡

ኢያሱ፡- እሽሽ.....እስከዛሬ የተናገርከው ይበቃል፡፡ ሶፊ ሰሞኑን ስትወተውታት ጆሮዋን ሰጥታህ ስለሰነበተችና የእማም ጭንቅ አይሎ አንቅልፍ አጥታ ማቃሰት ስለ ጀመረች ነው ቤቱ መልክ መልክ ያዘ የምትለው? ዮሴፍ እኔ ምርር ብሎኝ በጠዋት ተነስቼ ሁሉንም ከያሉበት ቀስቅሼ ሙትነታችን አይሎ ስለታየኝ እባካችሁ ለእማም ሰው እንሁንላት እይልኩ ስጨቀጭቅ ነው እንደ መልአክ ከተፍ ያልከው፡፡ ሶፊ ምነወ ዝም አልሽ አትመሰክሪም?

ሶፊያ፡- አንተ መች ለንግግር ግዜ ትሰጥና? አሁንስ የአንተን አፍ አስይዞ ዝም የሚያሰኝህ ነው የጠፋ

ዳንኤል፡-ተይው! የጌታ ፈቃድ ሆኖ ኢየሱሴን የተቀበለ ጊዜ ምናልባት እንደመጣለት መናገሩን ያኔ ይተው ይሆናል፡፡

ዮሴፍ፡- **/ኢያሱ ሊናገር ሲል አቋርጦት/** ማን ዝም እንዳለ ዳንኤል? በዚህች በእናታችን ፊት እንዲህ ያለን አሳፋሪ ቃል መናገር ዛሬም አልተውክም? እኔ ማን ነኝ? ትላንትስ ማን ነበርኩኝ ብለህ ማንነትክን ላፍታ ብትቃኝ ምናለ? እባክህን ከንቱነት በደምስርህ ሰርፆ ይገባ ዘንድ አትፍቀድለት፡፡ እውነትን ባትጸየፋት ምን አለበት በዚህተ በእናታችን ፊት ላይ የእውነትን ገጽታ ማንበብ ምነው ተሳነህ?

ኢያሱ፡- ዝም.....ዝም በል ዮሴፍ .....አንተ የፍቅርን መስዋዕት ከፍለህ ስትሰብክ እንጂ ብዙ ስትናገር ማንነትክን ዝቅ ያደረክ ይመስለኛል፡፡ ቀባጣሪነት ባህሪህ አይደለም፡፡ ዳንኤል የሚገባው ቢሆን ትክ ብሎ ውስጥ አይንህን አይቶ ንጽህናህን ተመልክቶ ይመለስ ነበር፡፡ ነገር ግን ህያው ሳይሆን ሞቷል፡፡ ሙት ነውና የሞት መስዋዕትነትን ሊከፍል አለመቻሉን በማወቁ በአንተ ላይ ለድፎ ለስደት ዳረገህ

ዮሴፍ፡-ተው.....ተው ኢያሱ ዳንኤል ይህን አላደረገም፡፡

ኢያሱ፡- አንተ! **/ዳንኤል ላይ እያፈጠጠ/** ተናገር እንጂ .....እስከ አሁን ለአንተ መሰደዱን መርጧል፡፡

ዳንኤል፡- ጌታ ይባርክህ! ያንተን አርቲ ቡርቲ ለምጀዋለሁ ወንድሜ የትናንት ማንነቴ ዳፋ የዛሬው እኔነቴ በተረሳው የጨለማው ህይወቴ ጦስ ብርሃኑን ሲነጥቅ ማየት ተሳቆ ነው ያቺንም የፍቅር ጦስ የጨለማ ህይወቷን አራዘመላት ይህም የጌታን ቡራኬ ያስገኝለታል፡፡

/በዚህ ጊዜ ታዬ የለበሰወ ጃኬት በደም ተለውሶ እየተቿኮለ ይገባል። ዛሪያ ቤቱን ከቃኘ በኃላ ዮሴፍ ላይ ያፈጥበታል። ዮሴፍ ተነስቶ እግሩ ስር ይወድቃል እናት በድንጋጤ ይፈዛሉ።/

ኢያሱ፡- ታላቃችን እንዴት ነወ ዛሬ ሲገባ ኮሽታ ማሰማትም የለ እንዴ?

ታዬ፡- **/ዮሴፍ/** ወይኔ! እንዴት ባደርግ ይሻለኛል? ዛሬ ልገልህ እንደማልችል ምን ጠላት ሹክ አለህና ብቅ አልክ? የበቀል ጥማቴ ገንፍሎ ሊፈስ በተቃረበቡት ሰዓት አይኔ ደም ጠምቶት በናወዘ ወቅት ጠፍተህ ዛሬ በክፉወ ቀን ዛሬ ሞት በአይኔ ጦሩን በሰበቀበት ወቅት መጣህ **/አልፎት ይንሯራደዳል። ደም የተነከረ ልቡሱን ይቃኛል/**

ሶፊያ፡- ምንድነው ጉዱ? ታዬ ምንድን ነወ ጉዱ

እናት፡- ልጄ ምንድ ነው ይህ ሁሉ ደም? አንዳች ቦታ ቆስሏል ወይስ የምን ደም ነው?

ታዬ፡- እስካሁን አንዳች ቦታዬ አልቆሰለም። ነገር ግን ከጥቂት ሰዓታት በኃላ እኔን አታገኙኝም። እማዬ በቃ አሁን ፖሊሶች የሞት መልዕክተኞች ይመጣሉ። እናም የመጨረሻዬ ይሆናል ትገላገይኛለሽ **/እናት እጅግ ይረበሻሉ/**

ሶፊያ፡- ስለ ምንድን ነው የምታወራው? በፍጹም እኔ....

ኢያሱ፡- ታዬ ሰው ገድሎ መጣ። እናም አሁን ፖሊሶች ነፍሰ ገዳዩን ሊወስዱት ይመጣሉ እግዚኦ.....

ታዬ፡- ገባሽ? ኢያሱ በጥሩ አማረኛ ገለጸው። ነፍሰ ገዳይ ነኝ እማዬ

ሶፊያ፡- **/እንባ እያነቃት/** ታዲያ ታዬ ለምን አትደበቅም? እዚህ መሆንህንስ በምን ያውቃሉ?

ታዬ፡- በቂ መረጃ አግኝተዋል። መታወቂዬንም ስለያዙ ለማምለጥ መሞከሩ በፍጹም የማያዋጣ መሆኑ ስለታወቀኝ መልክ መልክ የማስይዛቸው ጉዳዮች ስለነበሩ ወደቤት ገሰገስኩ **/የለበሰውን በደም የተለወሰ ጃኬት አውልቆ ይወረውርና ወደውስጥ ይገባል። እናት ወገባቸውን ይዘው ይከተሉታል። ሶፊያና ዳንኤል ኢያሱም ይገባሉ። ዮሴፍ ብቻውን ይቀራል/**

ዮሴፍ፡- አምላኬ ደካማ ባሪያህን ይቅር በለኝ። ቢቻልህስ ጌታ ሆይ የኔ የሃጥኡን ነፍስ ህልፈት ለወንድሜ ህይወት መድን ምክንያት ይሆን። ላንተ የሚሳንህ አንዳች የለምና **/በደም የተለወሰ ኮቱን ያነሣል/**.....አባዬ አሁንም እላለሁ አደራህ ከባድ ነው። ህያው ሳለ የነበረህን የልቦናህን መሻት እሞላ ዘንድ ደካማው ልጅህ ያቅሜን ታገልኩ።የሃጢአቴ ብዛት የአምልኮቴ ጎዶሎነት የእግዚአብሔርን የእርዳታ እጅ የራቀው መሰል ያሰብከው አልሆነም የእኔም ምኞት ህልም ሆነ። ይልቅ አባዬ አላማጅ በሌለበት የያዝከውን ኑሮ ላይልህ ነው እንደ አባትነትህ እኔ ልጅህን ለማላመዱ እንደምትተጋ ተስፋ አደርጋለሁ...../**በድንገት/** ምን እያልኩ ነው? **/ያማትብና ኮቱን ይለብሰዋል/** አይ ስጋ ገና ለገና ሞቴን ፈራሁ እንዴ? ስለነፍሴ ጸሎት በማደርስበት

ሰዓት መት አባቴን እየጠራሁ እንጉርጉሮ ቃጣኝ.....ይገርማል...../**ኢያሱ ትክዝ እንዳለ ይገባል/**

ኢያሱ፡- /**ዮሴፍን ሲያይ በንዴት!/...**I Swear you can't በቃህ! ዮሴፍ በቃ! እንዲህ ያለ ቀልድ ስትጫወት ማየት ሰልችቶኛል እኔ ቆሜ ይህ መስዋትዕነት ሲከፈል ማየት አልሻም!

ዮሴፍ፡- ተው ኢያሱ! እንዲህ አትበል! ለምን ከባድ መስዋዕትነት የከፈልኩ ይመስል ደጋግመህ ትክበኛለህ ቆይ ታዬ ሰው ገድሎ ባይመጣ በእኔ ላይ ሊደርስ ይችል የነበረውን ዕጣ መገመት አቃተህ? እኔም እኮ ስመጣ በሞቴ ቆርጬ ነበር። ሰቀቀን ሆኖ ሲያጨንቀኝ የሰነበተው በወንድሜ እጅ መሆኑ ነበር። ግን እግዚአብሔር አምላክ የቸርነቱን ስራ ሰራልኝ።

ኢያሱ፡- /**እጅግ ይተክዛል/** እ.....እማዬስ ዮሴፍ? በማን ትጽናና ማንስ አይዞሽ ይበላት? ሰው የላትምኮ!

ዮሴፍ፡- አሁንም አትሳሳት ኢያሱዬ! እስካሁንስ ማን ነበራት? እማዬ ሰው አይደለም አጽናኝዋ እንዲያው ለሰው ሰውኛው ግን አይዞሽ ባይ ሊያሻት ይችላል

ኢያሱ፡- እሱን ነው እኔም የምልህ በጉንጮቿ ላይ መንታ ሆኖ የሚወርድ እንባዋን የሚያብስላት አይዞሽ ባይ ተስፋዋ መንምኖ ልትወድቅ ስትንገዳገድ ደርሶ የሚደግፋት.....

ዮሴፍ፡-/**በድንገት**/.....አንተስ ኢያሱዬ? ካንተ በላይ ምን ሰው አላት?

ኢያሱ፡- አቤት! አቤት! ለመጀመሪያ ጊዜ ከዮሴፍ አንደበት ውሸት ሲወጣ ሰማሁ ሰው ከህይወት ወደሞት ልክ አንዳንተ ይሔዳል እንጂ የሞተ ሰው ተነስቶ ጤና ይስጥልኝ ብሎ ህያው ሆኖ እጅ ሊነሳ ይችላል? እኔኮ ለክፉ እንጂ ለመልካም ስራ ብቁ ላልሆን ሞቼያለሁ..... ዮሴፍ ግልጽ ውሸት ዋሸህ

ዮሴፍ፡- ኢያሱዬ ማንም ከማንም አይበልጥም ለእግዚአብሔር ሁላችንም የክብር ቤቶች ነን እግዚአብሔር አምላክ ባሻው ሰዓት ቤትነታችንን ሊያጸና፣ያለብንን ሃጢአት አርቆ፣ አንጽቶ የርሱ ገንዘብ ሊያደርገን ይችላል። የፖሊሶች መምጫ ሰዓት የደረሰ ባይመስለኝና ብዙ የመናገር ልምዱ ቢኖረኝ የእኔን ሀጢአቶች አንድ በአንድ ዘርዝሬ ካንተ ምንኛ እንደማንስ አሳውቅህ ነበር። .....ይልቅ ኢያሱዬ አሁን ያልከውን አይነት ሰው ሁንላት ለእማዬ .../**ኢያሱ በጥልቅ ያስባል እናም በደስታ ይዝላል። በደም የተለወሰውን ጃኬት ከዮሴፍ ላይ አወልቆ ለራሱ ሊለብስ ዚፑን መፍታት ይጀምራል ይታገለዋል።/**

ኢያሱ፡- አየህ ድንቅ ሀሣብ መጥቶልኛል ተው ዮሴፍ አትከልክለኝ ጊዜ ይወስዳል። ውልግድግድ ያለን ድንጋይ ጠርቦ ለማስተካከል ጊዜና ትዕግስት ይጠይቃል። የተስተካከለውን የማዕዘን ራስ ግን በእጅ እያለ ትግሉን ምን አመጣው? Please ዮሴፍ አትታገለኝ

ዮሴፍ፡- ለአንተ ሁሌም ሰርዖ ሊኖር የሚገባው ነገር ለእግዚአብሔር አንዳች እንደማይሣነው ነው። ጠርዐ የማስተካከሉን ስራ በራስህ የምትፈጽመው አድርገህ አትገምት። ይህ የእግዚአብሔር ፍጹም ከሀሊነት ነው። ኢያሱዬ ይህን ቃሌን ብቻ ጠበቅልኝ ለእግዚአብሔር አንዳች የሚሳነው ነገር የለም/**አይሣነውም**/

ኢያሱ፡- /**ቀስ እያለ ይለቀዋል**/ ቃልህ አይሰብከኝም። ግን ምግባርህ ገዛኝ አምንህለሁ፤ ላመንከውም እታመናለሁ። የህይወትን መስዋዕትነት ትከፍል ዘንድ ሀይልን የሰጠህ ለኔም እንዳይነሳኝ እለምናለሁ። ለእማዬ ቢያንስ ሰው ያላት እንዲመስላት አደርጋለሁ። ዮሴፍ የምትከፈለውን የደም መስዋዕትነት ለኔ ብርታት ለእማዬም ጽናቱን ይሰጣት

ዮሴፍ፡- /**ከአንገቱ ማህተቡን አውጥቶ**/ ያዛት! የጭንቅ ጊዜ ረዳት፣ መከታ ፣ድጋፍ ትሆንህለች። በመጨረሻ የማሳስብህ ኢያሱዬ አባ በዚህ ሰዓት እንደሚመጡ ነግረውኝ ነበር። የአባታችን አባት ነበሩ። ዛሬም የሁላችንም አባት ናቸውና ሃላፊነት ይሰማቸዋል። ስለዚህ በቡዙ ችግሮችህ ሊረዱህ ይችላሉና ተጠቀምባቸው። /**ተቃቅፈው እያሱ ፖሊሶች ይመጣሉ ሁኔታውን ይቃኙና ከተሰጣቸው መረጃ ጋር ዮሴፍ በትክክል እንደሚገጥም ካረጋገጡ በኃላ ይዘውት ይወጣሉ**/

ታዬ፡- የምን ጫጫታና የዱላ ድምጽ ነው የሰማሁት? /**ኢያሱ ዝም እንዳለ ነው**/

ሶፊያ፡- ኢያሱ ምንድነው የአሁኑ ድምጽ? አትናገርም እንዴ?

ታዬ፡- ጃኬቴንስ የት አደረጋችሁት? አንተ ኢያሱ ምናለበት ብትመልስልኝ?

ዳንኤል፡- በጌታ ስም! ቆይ እስቲ አጅሬው ሳይጫጫነው አይቀርም። በየሱስ ስም /**እንደጸሎት ይቃጣዋል እናት ገለል ያደርጉታል**/

እናት፡-እስቲ ዞር በል ልጄ /**ያማትባሉ**/ ኢያሱዬ..... ዮሴፍ ልጄ የት ሄደ? በል እንጂ ልጄ አናግረኝ።

ኢያሱ፡- /**በዝምታ እናቱን ደግፎ ወደውስጥ እየገፋ ይሏቸው ይገባል። ከጥቂት ቆይታ በኃላ ኢያሱ ይናገራል።**/ ወንድማችን ዮሴፍ አንተ ልትጠጣው የነበረውን የሞት ጽዋ ላያልፋት ሽቶ አንተን መስሎ ያንተን በደም የተነከረ ልብስ እንዳለበሰ በፖሊሶች ተወሰደ። ስላንተ ተላልፎ ተሰጠ /**ታዬ አጓርቶ ይወድቃል ኢያሱ ግራ ተጋብቶ ታዬን ደግፎ ሳለ ዳንኤል ፈዞ ሲመለከት ሶፊያ በዮሴፍ ሀዘን እያለቀሰች ሳለ መምሬ ተክሉ ይገባሉ የቤቱን ሁኔታ አይተው እንደመደናገጥ ይሉና ወደቀረቀረው ታዬ ሄደው መስቀል ሊያሳልሙት ሲሉ ይጮሀል፣ ይወራጫል ኢያሱና ሶፊያ ይደግፉታል። እናተ ጩኸቱን ሰምተወ ይመጣሉ**/

መምሬ፡- ማነሽ ልጄ.....እስቲ ውሀ አምጭ ጎሽ ፈጠን በይ /**ሳፊያ ውሀ ይዛ ትመጣለች**/ /**መምሬ ጸሎት እየደገሙ ውሀውን እፍ ብለው ከባረኩት በኃላ/ ምንድነህ?**

ታዬ፡- አጋንንት

መምሬ፡- ከወዴት ያዛችሁት?

ታዬ፡- ገንዘብ ለማግኘት ያለው ጉጉት አይሎ ግቡ እያለ ሲጠራን እየጎዘጎዘ ቢጋብዘን አለቃችን ሾመንና እና 2000 አጋንንት በየእለቱ እንታዘላለን

መምሬ፡- ምን ስታሠሩት ኖራችሁ?

ታዬ፡- የውሸት መድሀኒት እየነገደ እንዲኖርና በጥንቆላ ተሰማርቶ ሰዎችን እንዲያታልል አድርገነው ነበር፡፡

መምሬ፡- አሁን ታዲያ ምን አስባችኋል?

ታዬ፡- አሁን እንኳ መቆየታችን ያጠራጥራል ተቃጥለናል፡፡ ከዚህ ቤት እየኖረ እኛ ን ፍጽም ሰላም ነስቶናል፡፡

መምሬ፡- ድሮስ ምን ሰላም አላችሁና! ደግሞም ምን ጥርጥር አለውና? አሁን ትለቃላችሁ አትለቁም?

ታዬ፡- እንዴ! ለቀንስ የት እንግባ? የት እንሂድ? የት ብረሩ ነው የምትለን?

ታዬ፡- እሺ እንለቃለን! እንለቃለን!

መምሬ፡- ዳግም አንመለስም!....የቅዱስ ሚካኤል ሰይፍ ይቁረጠን? በሉ ጮሃችሁ ልቀቁ! ከዚያ መስቀል ያሣልሙታል፤ እናትን እያሳለሙ/ አይ ወለተ ሃና ምነው ይህን ጥቁር ልብሰ አልጥል አልሽ?

/አባት ሶፊያን አሳልመው ዳንኤልን እንዲሁ ገና መስቀሉን ሲያስነኩት ወደኃላ ከወንበሩ ላይ ዘጭ ይላል፡፡ አባ በመስቀል እየዳሰሱ ጠበል እየረጩ ይጸልዩለታ/ ተክሌ ! ተክለፃዲቅ ትሰማኛለህ?

ዳንኤል፡- አዎ አባ እሰማዎታለሁ /**ይጨነቃል**/ አንድ ነገር አልገባኝም

መምሬ፡- ጠይቀኛ ልጄ

ዳንኤል፡- ይህ መስቀል ይህን ያህል ኃይል ያደረጋል ብዬ አላምንም ነበር ነገር ግን ይኸው ታላቀ ተአምር ሲሰራ አየሁ ምንድነው ነገሩ?

መምሬ፡- ልጄ.....ተክለፃዲቅ መስቀሉማ አምላካችን የትዕቢት አባት ዲያቢሎስን ድል የነሳበት ስለኛ ሲል ተላልፎ የተሰጠበት የተሰቀለበት ነው፡፡ ድህነትም የተሰበከበት ነው በክርስትናችንም ሁለት ከአምላካችን በታች ከሰው በላይ የሆኑ የድህነት ምልክት አሉ፡፡ ከነሱም አንዱ አሁን ድህነት ሲያደርግ ያየኸው መስቀል ሲሆን ሌላዋ የድንህነታችን ምልክትና ምክንያት እመቤታችን ናት፡፡

ዳንኤል፡- አልሰማውም ብዬ እንጂ ዮሴፍ ስለሁሉም ነግሮኝ ነበር፡፡ ከኔ ውስጥ የጥርጣሬን መንፈስ አውጥቶ ለመጣል ያደረገው ጥረት ዛሬ ምነው እንዲህ ጥርት ብሎ ታየኝ? .....ደግሞኮ ስለኔና ስለወንድሜ ታዬ ሞት ተላልፎ ተሰጠ

ታዬ፡- ኢያሱ ዮሴፍ የት ሄደ ነበር ያልከኝ? **/ኢያሱ ዝም ይላል/**

ሶፊያ1- ታዬ አንተን ሊወስዱ የመጡ ፖሊሶች ይዘወት ሄዱ ነውኮ የሚለው ኢያሱዬ **/በምሬት/** ወንድምአለም የኔነቱን ትርጉም አጣሁት የፍቅርን ምንነት በአንተ አወቅሁት ሃያልነቱን በሚገባ ገለጽክልኝ ኖረህስ በሆነና እግርህ ስር ወድቄ ማረኝ ባልኩህ ጸጸት ረመጥ ሆኖ ባልፈጀኝ አንተ የምታስበውን ላሰብ የምታደርገውን ላድርግ የምታመነውን ልመን እንዴህ ልቤ ቆርጦ ሳለ ያንተ ህያውነት ቢታከልበት ምን ነበረበት? ምናለ አሁን በዚህች ቅጽበት አንተን ከሞት መንግጋ ፈልቅቆ የሚያወጣ ተአምር ቢፈጠር?

ዳንኤል፡- እኔ! እኔ ሶፊ! ከጥሩ ስራ ይልቅ ለክፉት የፈጠንኩ እኔ ቆሻሻው! እኔ በሀጢአት የወደቅሁ ከንቱው የመኖሬ ትርጉም ለእኔም ሆነ ለማንም ግልጽ ያልሆነ አልባሌ ተመፃዳቂ እኔ ሶፊ! ዛሬ ከነፍስ እፈጥናለሁ፡፡ ለመልካም ነገር እኔ ተተክቼ እርሱ ይመለሳል **/እያለ ሊሮጥ ሲወጣ ኢያሱ በፍጥነት ይይዘዋል/**

ኢያሱ፡- ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት እኔም ያንተን አይነት ውሳኔ ወስኜ ነበር እኔም ልክ እንዳንተ ከእኔ አልባሌ ህይወት ይልቅ የዮሴፍ ህይወት ልቃ ታይታኝ ተጋብዤ ነበር ግን የፍቅር ፈረሱ ሊገራ አልቻለም የሞት ፍራዳውን ለሌላ ሊያጋራ አልፈቅደም፡፡ ይህ ቆራጥነቱ ግን እንደኔ ከስሜታዊነት የመነጨ አልነበረም ብዙ ሳይናገር አሳመነኝ ሁላችንም ለእግዚአብሔር እኩል እነደሆንን አምላካችንን ለሃጥአንና ለፃድቃን ሁለት አይን እንደሌለው በአጭር ቃል አስረዳኘ፡፡ አላንገራገርኩም ተቀበልኩት አልቅሼ ሳይሆን በተመስጦ እያስተዋልኩ ከሞት መንጋጋ ሲወድቅ ባይኔ ሸኘሁት፡፡ እና ዳኒ አንተም ባክህ ሀሳብህን ለውጥ ብዙ ለህይወት በህይወት ሳለን የምንሞታቸወ ሞቶች አሉና የዛሬውን የቁርጡ ሞት ዮሲን አንጋፋው እንተውው ይሙት፡፡

መምሬ፡- ስለምን ፖሊሶች ስለምን ሞት ነው የምታወሩት? ልጄ ዮሴፍ ምን ገጠመው?

ታዬ፡- አባቴ እኔ ትናንትና ሰው ገድዬ ነበር፡፡ ሚቹም እወቅ የመንግስት ባለስልጣን ስለነበር ገዳዮቹ ተፈልገው እንደተገኙ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስድ ተባለ፡፡ ከዚያም..... ዮሴፍ ወንድሜ ዮሴፍ እኔን ሊወስዱ በመጡ ፖሊሶች ተወሰደ ዮሴፍ ስለኔ ተላልፎ ተሰጠ፡፡

መምሬ፡- ወይ አምላክ እስራኤል! ስራህ ረቂቅ ነው፡፡ እኔስ የአባትነቴን ቀኖና ሰጠሁት ወይ ግሩም! የአንድ ቀኖናውን ጨርሶ ሲመጣ ጠራኸው? ነፍሱን ተቀብለህ በአባቶቹ በአብርሃም፣ በይስሃቅ፣ በያዕቆብ አጠገብ ታኖር ዘንድ እለምንህለሁ፡፡

ዳንኤል፡- ዮሴፍ.....ወንድሜ ይቅር በለኝ ኧረ ሀጢአቱ በዛ፡፡ ባለበደልከው በደል፣ ባላጠፋኸው ጥፋት የኔን ኃጢአት ተሸክመህ በስደት ኖርክ አሁን ደግሞ አሁን ስለወንድምህ ታዬ ለሞት ተላልፈህ ተሰጠህ ኧረ እንደምን ያለ ፍቀር ነው ከልብህ ያለው!፣ አቤት!

ታዬ፡- ኧረ የእኔም ሀጢአት ብዙ ነው፡፡ ኧረ የእኔም ክፋት ከልክ ያለፈ ነው እኔስ አሁን ምን እባላለሁ አባቴ ከአምላኬ ፊት እንዴት እቆማለሁ? **/ሁለቱም በአባ ግራና ቀኝ ይንበረከካሉ፡፡ እናት ነጭ ለብሰው እየተፍለቀለቁ ይገባሉ/**

መምሬ፡- እግዚአብሔር አምላክ ስራህ ምንኛ ድንቅ ነው? ቸርነትህ ተነግሮ አያልቅም በዚህች ዕለት የሚቹን ልጄን ህልም እውን አደረግህ በአንድ ፍሬው ልጅ መስዋዕትነት በቤቱ ነግሶ የነበረውን ርኩስ መንፈስን አርቀህ የተከፈለውን የአንድ ቤተሰብ ልብ አንደቀድሞ አንድ አደረግህ እንግዲህ ላንተ ምስጋና እንጂ ምን ይከፈላል?

መጋረጃ ይዘጋል

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
ወለወላዲቱ ድንግል
ወለመስቀሉ ክቡር

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን::

ያልተገለጸው ሲገለጽ

ትዕይንት ፩

ሰፋ ባለውና ጨለምለም ባለው ሳሎን በክብ ጠረንጴዛ ዙሪያ አጋንንትን የወከሉ አለቆች ተቀምጠዋል ከፊት ለፊት አለቃቸው

የቢሮ ሃላፊ

ለመላው የሰው ዘር ይህ ስማን ክደሬንና ሰራዊት አጋንንት በተለመደው ፀረ ሰው መክፈቻ ጸሎታችን የከፈትነው ስብሰባ የሰው ልጅ ሃይማኖታዊ ክንውን እንቃኝዋለን:: እንደምናውቀው ሰው በአምላኩ አምሳል ተሰርቶ የአምላኩን ክብር ለመውረስ ተስፋ ከአምላኩ ለማራቅና ተስፋውን ለማምከን በታላቅ ወኔ ሳንታክት እንሮጣለን ሩጫችንም ስልታዊና የተደራጀ ሲሆን ይህ ቴክኒክ ዛሬ ሳይሆን ጥንት በኤዶም ከገነት አዳምን ከአምላኩ በማጣላት ጀምረዋል:: አሁንም ይህንን ሩጫ እስከ ምጽአት አለም በመቀጠል ተስፋ ተብላ የተሰጣቸውን መንግስተ ሰማያት እርቃኑን እስክትቀር ይህን ውጊያ እንዋጋለን ክቡራን የጥልቁ ዓለም የጨለማው ባለስልጣናት ዛሬ አመታዊ እንቅስቀሴያችንን የምንቃኝበትና ጠንካራና ደካማ ጎናችንን ጠበቅ አድርገን የምንቃኝበት እለት ነው::

ባለፉት ዓመታት የሰውን ልጅ በገዛ እውቀቱ ጠልፈን ለመጣል ባደረግነው የተቀነባበረ ሥልታዊ ዘመቻ ኒውክለርን የመሰለ ለራሱ መጥፊያ የሚሆን መሳሪያ የሰው ልጅ በገዛ እጁ እንዲፈጥር በማድረግ ትልቅ ድልን ማስመዝገባችን ይታወቃል:: በዚህም ምክንያት ሰላም አጥተዋል ሁሉም መጥፊያቸውን ለመስራት በመዋከብ ላይ ይገኛሉ ይህ እንግዲህ በሰለጠነው አለም ቦታና ትልቅ ድል ነው:: ዛሬስ ግዛታችን እንደ ወትሮው የተጠበቀ ነው:: ይህንን እንግዲህ በዚህ ዝግ ስብሰባችን እንቃኛለን::

የመጀመሪያው ሪፖርት ሰውና አምላኩ የሚገናኝበት ቁልፍ ድልድይ የሆነው የጸሎት ጠለፋ ክፍል የክፍሉ ኃላፊ በሆነው በሚስተር አጋንንት ፀሎት ጦሩ አማካኝነት የወሩ ዘገባ ይቀርብልናል:: /ይቀመጣል/

ፀሎት ጦሩ:-«አመሰግናለሁ ማስተር!» ሞት ለሰው ልጅ ይሁንና ዓመቱን በተፋጠንበት የጸሎት ማምከን ስራ የከወነውን አቢይ ክንውን እናቀርባለን እንደምናውቀው ጸሎት በየትኛውም ሰዓት በሰው ልጆችና በአምላካቸው መካከል የሚደረግ አደገኛ ንግግር፣ ውይይት ሲሆን ይህም ክዋኔ የእኛን መንግስት የሚጻረር ብሎም የሚያፈርስ

ታላቅ መንፈሳዊ ደባ ነው። ይህንንም አደገኛ መንፈሳዊ ደባ ለመከላከል የኛ ኃይሎች ካለ መታከት ቀን ከሌሊት ይሰራሉ። በዚህም እቅዶችን አውጥተን ከስራ ላይ አውለናል። ከነዚህም መካከል፦

1. የሰው ልጅ በጭራሽ እንዳይጸልይ ማድረግ ይህም ሲባል በስንፍና በመሙላት እና አደገኛ የእንቅልፍ በሽታ በላዩ ላይ በመልቀቅ በጸሎት እንዳይተጋ ማድረግ

2. ለጸሎት የሚንቀሳቀሱትንም በተለያዩ ስጋዊ ምኞቶቻቸው በመጥለፍ ልባቸውን በመክፈል የጸሎታቸውን አቅጣጫ በማስለወጥ ከአምላካቸው ጋር እንዳይገናኙ ማድረግ ነው። እነዚህ ከላይ የገለጽካቸውን ሁለት አገልግሎቶች በተናጥል ስንመለከታቸው የመጀመሪያው በፍጹም የማይጸልዩት ለመንግስቱ የማያሰጉንና ኃይልንም ለማግኘት የማይችሉ በመሆናቸው ከአምላካቸው የሚያገናኛቸው ድልድይ የተቋረጠ ነው። ስለዚህ ይህ ብዙ አያሳስበንም።

   ወደ ሁለተኛው ስንመጣ ግን በጸጋ ካለመሞላት፣ ከክርስትና ትምህርት እውቀት ማነስ፣ በግል ምኞትና ፍላጐቶች በውጣውረድ ጸሎታቸው ወደ ተፈለገው ግብ ከመድረሱ በፊት በህዋው ላይ ተበትኖ ይቀርና በእኛ ቁጥጥር ስር ይውላል። በዚህም ምክንያት ለጸሎት ሲቆሙ

   1. ስጋቸውና መንፈሳቸውን በመለያየት ስጋቸው ለጸሎት በቤተክርስቲያን ሲቆም መንፈሳቸው በአለም ገበያ በምኞት ተጠልቶ ከቤታቸው ወይ ከመንደራቸው ወይ ከመስሪያ ቤታቸው አልያም ደግሞ ከፍቅረኛቸው ጋር ይንጐዳጐዳል። ይህም የሚሆነው የእኛ የጸሎት ማምከኛ ንዑስ ክፍል በሚሰራው የረቀቀ ስራ ነው።

   2. ለጸሎት በሚቆሙበት ሰዓት በፈቃዳቸው እንዲዋልሉ በማድረግ የጸሎተኛውን ፈተና እንደ ብፌ ከፊቱ በመደርደር ከቀረበለት የዓለም የስጋ ፍቃድ ብፌ በፈለገው አይነትና መጠን እንዲያነሳ በማድረግ ወዲያው የጸሎቱን አቅጣጫ ማስቀየር ዋናው ስልታችን ነው። በዚህ ውስጥ ካለመረዳት የሚደረጉ አስቂኝ ጸሎቶችና ልመናዎችን እናገኛለን። ለምሳሌ ከወጣቱ ማየት ብንጀምር መጽሐፍ «በወጣትነት ፈጣሪህን አስብ» በማለት ሲነግረው እሱ ግን ፍቅረኛውን በማስብ ወደ ተራራ ላይ ወጥቶ ለመኮፈስ በማሰብ እና በሌላ ብዙ ምክንያቶች ተወጥሮ ወደ ጸሎት ይገባል። ይህም ጸሎቱ የታለመለትን ግብ እንዳይመታ ትልቅ እንቅፋት ይሆንበታል።

ለምሳሌ፦ የአንድን ቅብጥብጥ ወጣት ጸሎት እንከታተል። ልቡ በአምላኩ ሳይሆን በአንዲት እንስት ፍቅር በመቃጠሉ ጸሎቱ ተበላሽቶበት እናያለን ለጸሎት ወደ መጣበት ቤተክርስቲያን አንገቱን ደፍቶ ሲገባ ላየው ለአምላኩ ቤት ተገቢውን ክብር በመስጠት ፈርቶና ተንቀጥቅጦ የገባ ይመስላል፤ግን ውሸት ነው። የዚህ ወጣት ልጅ ልብ በዚያች ሰዓት እንኳን ከፍቅረኛው በስተቀር የሚያስበው አልነበረም። ለድምጽና እና ለምስል ክምችት ክፍላችን ምስጋና ይግባውና እስቲ ይህን ወጣት አብረን እንመልከተው.....

ወጣት፦ /አንገቱን ደፍቶ ወደ ቤተክርስቲያን ይገባል ተንበርክኮም እጁን ይዘረጋል/

የጸሎት ጦሩ:-«አያችሁት የዚህን ወጣት ሁኔታ እጁን ለበረከት የዘረጋ አይመስልም? ነገር ግን ጸሎቱ ከራሱ ጣሪያም ያለፈ አልነበረም:: ጸሎቱም ይህን ይመስል ነበር::»/**ድምፅ ከውስጥ**/

ወጣት:- «አምላኬ አመሰግንሃለሁ፣ አከብርሃለሁ እባክህ አምላኬ አንድ ነገር ላሰቸግርህ መቼም የፍቅርን ነገር ታውቀዋለህ ተፋቀሩም ብለሃል ያቺን ውብና ቆንጆ ልጅ አዎ የሃብታምና የባለጸጋ ለጅ እባክህ ልቧን እንደሰም አቅልጠህ አፋን በእሺታ ሙላልኝ እንደምወዳት የምታውቅበትን አስተዋይ ልብ ስጣት ደግሞ ካለ ብር አትንቀሳቀስም ምናለ ብርም ብትሰጠኝ ለምኑ ይሰጣችሁኃል ብለህ የለ ያ ደግሞ መንገድ ላይ የሚያስቸግራት ወጠምሻ እባክህ እኔ ከእርሱ ጋር የምታገልበት አቅምም የለኝ... እና አምላኬ ወደ ፈተና አታግባኝ...

የጸሎት ጦሩ:- ይልና የጸሎቱ አቅጣጫ አንደጠፋበት ሲያውቅ እና ልቡን ወደ አምላኩ ለመመለስ ቢታገል ከኛ የጸሎት ማምከኛ ጣቢያ የምኞት ሞገድ ይለቀቅበትና ፍቅረኛው ስትናፍቀው እሷን ለማየት እዩ ... **/ወጣቱ እየተጣደፈ ይወጣል/** ጸሎቱ የታለመለትን ግብ ሳይመታ ጥሎት ወደ መጣው አለም ይነጉዳል የዚህን ሰው የመረዳት ደረጃ ስንገመግም አምላኩ ለእሱ ፈቃድ የሚቆም ፍቅረኛ የሚመርጥለት ወይም የእሱን የሥጋ ፍቃድ የሚፈጽም የምኞት አጋሩ አድርጐ ነው የወሰደው:: በዚህ ሰው ግምት ለምንም ይሆን ለምን በስጋው ብቻ እየተጐተተ ወደ ቤተክርስቲያን መግባቱ መንግስተ ሰማያት የመግባት ያህል ጽድቅ ነው:: ይሄም ወጣቱ ዳዊት «አንተ አምላኬ ነህና ፈቃድህን ማድረግ አስተምረኝ» ያለውን በመዘንጋት የአምላክ ዓላማና ፈቃድ በሱ ሕይወት ውስጥ እንዲሰራ በራሱ የስጋ ምኞት ፈቃድ ተቀፍድዶ ተግዞ የፍቅር ኑዛዜውን ከጸሎት ቆጥሮት ባልሰራው ጽድቅ በሃሴት ሰክሮ ሲወጣ አያችሁት አይደል:: ይህ ታዲያ የእኛ የጸሎት ማምከኛ ንዑስ ክፍል ወርቅ የስራ ውጤት ነው::

እስቲ እኚን ባልቴት ደግሞ እንመልከት.....ባልቴቷ/ ወፍራም ናቸው ሃብታም ወደ ቤተክርስቲያን እየገቡ/

ባልቴት:- አቤት.....አቤት አምላኬ በሬ አይደለሁ ይሄን ሁሉ ስጋ ያሸከምከኝ አቤት ያንተ ሥራ መልሰህ ለአፈር ልትሰጠኝ... የግል ሀኪሜ ኪሎ ካልቀነሽ ሰላም የለሽም ሰውነትሽ ሁሉ ጮማ ነው አለኝ እንዲያውም ስጋሽ ሁሉ ወደ ጮማነት እየተቀየረ ነው አለኝ ምን ይደረጋል ጮማ ሁኚ ካልከኝ በቃ ጮማ መሆን ነው::.....ኡፍ... አቤት የአንተ ሥራ የሰው ጮማ አደረከኝ አምላኬ ይሁና እስቲ ጮማም ሆኜ እድሜ ላግኝ አደራህን...አደራህን አምላኬ ጮማ ናት ብለህ አትተወኝ:: አደራህን የኔ ጌታ.../**ወደ ተከተለቻቸው ልጅ ያዩና**/ አንቺ ልበ ቢስ ለመሆኑ ፍሪጁን ዘግተሻል

ልጅ:- አዎን ዘግቻለሁ

ባልቴት:- በኃላ ነግሬሻለሁ አይስክሬሙን እኔ ቤቢ መጫወቻ እንዳያደርጉት ለመሆኑ የባኞውንስ ውሃ ዘግተሻል መቼም ልጅ አይደለም የሰጠኝ

አምላኬ ዳክዬ ነው የሰጠኝ የውሃ ነገር አይሆንልሽ ብቻ ሳትዘጊ መጥተሽ ቤቱ አዋሽን ሆኖ እንዳይቆየን አደራህን ጌታዬ....አደራህን....

ጸሎት ጦሩ፡- .....ልባቸውን ቤት አስተኝተው የመጡት እኚህ ባልቴት በሰፈራቸው በጸሎት የተጉና በምጽዋትና በጾም የጠነከሩ ናቸው፡፡ ይባልላቸዋል፡፡ ጸሎታቸው ግን እነሆ.....

ባልቴት፡- ..... መቼም ይኼን ሁሉ ስጋ ይዤ መቆም አይሆንልኝ ልዘርፈጠው እንጂ/ **ተቀምጠው ይጸልያሉ**/ አቤቱ አምላኬ ተመስገን መቼም ሌላ ምን እላለሁ እንደ ሰው አፍ ቢሆን ኖሮ ይኸኔ ከቀሚሴ ሾልኬ እጠፋ ነበር ባንተ ነው ያለሁት ጌታዬ ባንተ ነው፡፡ እድሌ ሆኖ ጠላተ ብዙ አድርገኸኛል ይሁን ምቀኛ አታሳጣኝ ምቀኛ ነው ይህን ሁሉ ጥሪት ያስቆጠረኝ አሁንም ጌታዬ በጠላቶቼ ፊት አታሳፍረኝ ለምን ብዬ አንተ እያለኸኝ ከሰው ልነስ? አሁንም ጌታዬ ኑሮዬን የተሻለ ለማድረግ በማሰብ የጭነት መኪና ለመግዛት አስቤአለሁና ቀጠሮዬን የተሳካ አድርግልኝ፡፡ የአሁኑንም አደራ ጌታዬ በጠላቶቼ ፊት በምቀኞቼ በራፍ ሳላሸከረክረው አታሳልፈኝ በተረፈ አሜሪካም ካናዳም ያሉትን ልጆቼን አደራህን ጠብቅልኝ አጥብቄ ግን የምለምንህ የነገ ቀጠሮዬን አሳክተህልኝ የጥሩ መኪና ባለቤት እንድታደርገኝ ነው፡፡ እርዳኝ አባቴ እርዳኝ የኔ ጌታ፡፡

የጸሎት ጦሩ፡- .....አያችኃቸው እኚህን ቅምጥል በእሳቸው ግምትና ሃሳብ አምላካቸውን እንደ አንድ መኪና የሚገጣጥም መካኒክ ነው ያዩት ባልቴታ ፈቃዱን ለመፈጸም ሳይሆን አምላካቸውን የሚፈልጉት የስጋዊ ሃብት በረከታቸው አጋር በማድረግ ፈቃዳቸውን የሚሞላ የማይነጥፍ የንዋይ ምንጭ እንዲሆናቸው ነው፡፡ በጣም ግሩምና ድንቅ ወደሆነው አሰራራችን ስንመጣ ይሄንን ቂል ፍጥረት በጸሎት ማነስ በሽታ የተለከፈውን የእምነት ደዌዎች መሣሪያ በማድረግ የምንሠራው ረቂቅ ሥራ እንመልከት

/አንድ ቃልቻ ጀበናና ስኒ ደርድሮ ተቀምጦ ይዘይራል አንገቱን በማወናጨፍ መንፈሱ ያስጓራዋል ከፊት ለፊቱ ችግር ያመጣቸው የእምነት ድሆች ተኮልኩለዋል/

ቃልቻ፡- ቡ.....ቡ.....ቡ.....ቡ.....አምቡ**ር.....ር.....ር** ባንተው መጀን **/በህብረት/** የኔ ጌታ ባንተው መጀን

ቃልቻ፡- ማነሽ አንቺ.....ማነሽ ከነአዳፋሽ ገብተሽ ጌታዬን ከበር የመለሽው እኮ ማነሽ ቀይ እግረ ቀጭን አንገትሽ ላይ ንቅሳት ያለሽ አንቺ ተነሽ ዘንዶ ሆኜ እንዳልውጥሽ ሾተል ሆኜ እንዳልቆርጥሽ እ.ም...ም...

ከፊት ለፊት ያሉት ሰዎች፡- ማነው.....ማነው? በኛ መሃል ቀይ ንቅሳትም ኧረ ባንተው መጀን ጌታዬ የምትለውም የለ

ቃልቻ፡- እንዴት እናንተ እኔ አባ መጊል ቡራገላቢ እኔ ነኝ የማላውቅ...

ወርቁ፡- ኧረ ታውቃለህ ጌታዬ እሱንማ ብለን አይደል ችግራችንን ይዘን ወደዚህ መምጣታችን...

ቃልቻ፡- ችግር ድራሹ ይጥፋ እኔ መገል በመርፌ ቀደዳ አሾልኬ የማላወጣ ሆኜ ነው.....

ወርቁ፡- እንዴታ ጌታዬ ላንተ ምን ተስኖህ ሁሉን ቻይ ነህ.....

ቃልቻ፡- እኮ ባለሽ እያስከፋ ቢያስቸግርሽ አይደል? በጸሎት ስሜን የጠራሽ...

ወርቁ፡- ኧረ ባልም የለኝ ጌታዬ

ቃልቻ፡- ውሽማም ቢሆን ከኔ ልትደብቂ

ወርቁ፡- ኧረ ባንተው መጀን ጸያፍ ነው ባገሬ

ቃልቻ፡- እኔ አጅራ! ዘራፍ ቡራ ገላቢ ከፊቴ ቆሞ የሚጋርደኝ ውስጠ ምስጢርሽን የማላውቅ ነኝ አንቺ ከጐረቤትሽ ምቀኛ ብትነሳብሽም አይደል ጨርቅሽን እስጥላ እንዳታሳብድሽ አድነኝ ልትይኝ የመጣሽ?

ወርቁ፡- ኧረ! ጌታዬ ጐረቤትም የለኝ ብቻዬን በግቢ ታጥሬ የምኖር ነኝ...

ቃልቻ፡- **/በቁጣ/** ምን ትላለች እንኳን አንቺ ኢትዮጲያ ሃገራችንም ጎረቤት አላት ጃፖን ፣ ኮንጐ፣ ጋምቤላ ጐረቤቶቿም አይደሉ የሚያዋስናት ቡና የሚያጣጣ.....ብቻ አይደለም ጎረቤት በይ አሁን ተንበርከክ.....

ወርቁ፡- ምን አጠፋሁ ኧረ ባንተው መጀን

ቃልቻ፡- ከራማዬ ተቀይሞሻል

ወርቁ፡- **/ተንበርክካ/** ኧረ! ባንተው መጀን ባታውቀው ልንገርህ እንጂ አትቅሰፈኝ

ቃልቻ፡- ማነው የማያውቅ እኔ መጋል ባታውቂኝ ነው እንጂ በመሃል ከተማ በኦፔል መኪናሽ ስትሄጂ ክንፌን ጋርጂ የምጠብቅሽ እኔ ነኝ

ወርቁ፡- ኧረ በጉዴ ወጣሁ ኧረ እንኳን ኦፔል መኪና የረባ ጫማም የለኝ ጌታዬ

ቃልቻ፡- ባትገዥውም የሰው መኪና በበርሽ ካለፈ ያው የአንቺው ማለት አይደል

ወርቁ፡-ኧረ! ፋብሪካውም መኪናውም ቀርቶብኝ የረባ ጫማ የሚያስገዛኝ ስራ ጌታዬ እሱ ነው ችግሬ የ 50 ብር ስራ

ቃልቻ፡- ምንድነው 50 ብር የሃምሣ ሺ ብር ስራ ልስጥሽ እችላለሁ

ወርቁ፡- ኧረ ጌታዬ እኔኮ ቶምቦላ አይደለም የለመንከህ የ 50 ብር ስራ ብቻ .....

ቃልቻ፡- እመኚ ቶምቦላም የኛ ነው ዝሆኑም የኛው ካመንሽ ብሔራዊ ሎተሪንም ልንሰጥሽ እንችላለን ብቻ ለማንኛውም የ 25 ብር ጫት ገዝተሽ ነይና እየተለመነልሽ ትቅሚያለሽ ያኔ አይነጥላሽ ይገፈፋል፡፡

ወርቄ፡- ኧረ! ጌታዬ እኔ ጫት ቅሜ አላውቅም ያመኛል

ቃልቻ፡- አትቃወሚ እንኳን ጫት አይደለም ባሩድ ቃሚ ብልሽ መቃም አለብሽ አይነጥላሽ ከባድ ነው ባልም ስራም ሁሉንም የያዘብሽ እሱ ነው

ወርቄ፡- እሺ አንተ እንዳልክ ጌታዬ /**ትሰግዳለች**/

ፀሎት ጠሩ፡- አያችኋቸው እኒህን የዋሃን እግራቸው ለጸሎት አምላካቸው ፊት መቆም ሲገባው ወደ ቃልቻ ቤት በመሮጥ ቀጥኗል ምላሳቸውም እኛኑ በማወደስ አርነቱን ሸጧል፡፡ መጸሐፍ «የሰው ሆዱ ከአፉ ፍሬ ይጠግባል» ይላል፡፡ እነዚህ ግን የአፋቸው ፍሬ ጸሎት ሳይሆን እንዳያችሁት በአለም ምኞት በሥጋ ሃብት ልመና በማይሰማና ተቀባይነት በሌለው ከንቱ ድካም ከምላሳቸው ፍሬ በረከትን ሳይሆን መርገምን ይጠግባሉ የክርስትና እውቀት ደህንነታቸው በጸሎት ያለመትጋት ስንፍናቸው የአምላካቸውን እርዳታ ነፍጓቸው በባዶና ወና በሆነው ህይወታቸው ውስጥ ገብተን በመቀመጥ በቁራኝነት እንይዛቸዋለን፡፡ በአጠቃላይ የጸሎት ተራራ ውሎአቸው ይህንን ሲመስል ይህ ማለት ግን የሚጸልዩ ሰዎች የሉም ማለት አይደለም እነዚያ በጸሎት የተጠመዱት በኃይልና በጸጋ የተሞሉ ስለሆነ ልንቀርባቸውም ሆነ ልናዛቸው አንችልም፡፡

ዋና ኃላፊ፡- ዘገባው ግሩምና ድንቅ የተሟላም ነው፡፡ ነገር ግን አንድ ያላስተዋልነው ነገር አለ በየገዳማቱና በየዋሻው መሸገው ሥጋቸውን እየቀጡ በጸሎት የተጉ ገዳማውያን መነኮሳትስ አስተውለናቸዋል? አሥ የእነሱ ጸሎት የኛን አሰራር የሚቃወምና የሚያፈርስ በከተማ ውስጥ ከሚደረጉ ጸሎቶች የበረቱና በሃይል የተሞሉ ስለሆኑ እነሱን በብርቱ መከታተልና ፈተና በማብዛት ከጸሎታቸው ማዘናገት ያስፈልጋል፡፡

ፀሎት ጠሩ፡- ኧረ ጌታው ይኼ እንኳን የማይሞከር ነው ጌታዬ የነሱ ጸሎት ኒውክሌር ማለት ነው ብዙዎቹ ምኞታቸውን የገደሉ ስለሆኑ ለማስናከያም መንገድም አይገኝላቸውም

ዋና ኃላፊ፡- ይኼ እንኳን የምቀበለው ነገር አይደለም ይኼ በገዳም የሚታየው መነኩሴና ባህታዊ ሁሉ በትክክለኛ ጥሪ የመጣ አይደለም፡፡ ብዙዎቹ በስሜት ተነድተው በችግር ተገፍተው የመጡ በመሆናቸው ምኞታቸውን የገደሉ ናቸው ብለን አፋችንን ሞልተን መናገር የለብንም፡፡ እኛ ደግሞ ገዳም አይደለም ኤዶም ገነት ገብተን ጥንታውያኑን የሰው ልጆች ወላጆች ከተስፋ ምድራቸው እንዲነቀሉ ያደረግን መሆናችንን መዘንጋት የለብንም እና ይህን አይነቱን የስንፍና ንግግር ደግሜ እንዳልሰማ ለኛ ምንም ነገር የሚሳነን የለም ገባችሁ

ፀሎት ጠሩ፡- ተቀብለናል ጌታው፡፡ እኔን የገረመኝ ብዙዎቹ የሰው ልጆች ጸሎት የሚባል ነገር እኮ አያውቁም ጸሎት ካልጸለዩ ደግሞ አምላክ የላቸውም ማለት ነው አምላክ ከሌላቸው ደግሞ የእኛ ምርኮኞች ናቸው ማለት ነው ደስ አይልም! ስለዚህ ብዙዎች ስለማይጸልዩ ጥቂቶች በመፀለያቸው ልንሰጋ አይገባንም፡፡

ፀሎት ጠሩ፡- ይህ እንኳ የሚያዘናጋ አነጋገር ነው። እንደ ፀሎት ኃይል ያለው ለኛ መንግስት ስጋት የሚሆን ምንም ነገር የለም። አንድ ክርስቲያን በትክክል ከአምላኩ ጋር ተገናኝቶ ጸለየ ማለት በእኛ ግዛት ላይ የማያቋርጥ የመድፍ ድብደባ አደረገ በሚለው ቀለል ያለ አገላለጽ ማስቀመጥ ይቻላል። ጸሎት እኮ እኛ አናስተውለውም እንጂ በውስጡ ከባድ የክርስትና አረሮችን/ባሩድን/ ያዘለ የእምነት ጥይት ነው። እነዚህም ለአምላክ መታመን፣ መገዛትንና መንበርከክን የመሣሠሉ ትልልቅ የትህትና ወይም የክርስትና ቁልፍ ምስጢሮችን ክርስቲያኑ በጸሎት ገንዘብ አደረገ ማለት ነው። ይህ ማለት ደግሞ ከኛ ጋር ያለው የመገናኛ መስመር ተዘጋ ማለት ነው አዲዎስ!

ዋና ኃላፊ፡- በአጠቃላይ ሲታይ በጸሎት ማምከኛ ንዑስ ክፍል እየተከናወነ ያለው ሥራ በጣም አመርቂና ይበል የሚያሰኝ ሲሆን በቀጣዩም ከዚህ በተሻለና በረቀቀ መልኩ የጸሎት ማምከኛን ሥራ በንቃትና በብቃት እንደወጡ ከድንጋይ የከበደ አደራችንን በክፍሉ ሰራተኞች ላይ ጥለንባቸዋል። እሺ በቀጣዩ የምናየው ደግሞ የምጽዋት ክልከላ ክፍልን ይሆናል ሪፖሪቱ ይቀጥላል

ደቄ፡- አመሰግናለሁ ክቡራንና ክቡራት የኛ ክፍል የምፅዋት ክልከላ ክፍል በመባል የሚታወቅ ሲሆን በስራችንም አያሌ ሰራዊተ አጋንንት ይሰራሉ። ምፅዋት የሰው ልጅ ፍቅሩን በተግባር የሚገልፅበት ከአምላኩ የተቀበለውን ለሌለው በመስጠት ሰማያዊ ትርፍን የሚያገኝበት ሲሆን ይህም ደግሞ የሰው ልጆች ከአምላካቸው የተማሩ በመሆኑ ለኛ አሠራር ትልቅ እንቅፋት ነው። በዚህም ምክንያት የሰው ልጅን ንፉግ እንዲሆን በማድረግ ይህንን ታላቅ የበረከት ማግኛ መንገድ እያዘናጋን እንገኛለን። ለዚህም ዋነኛ መጠቀሚያ አድርገን እየሰራን ያለንበት መንገድ የሚከተሉት ናቸው።

1. የሰው ልጅ ንፉግ እንዲሆን ማድረግ ይህም ማለት ያለውን እንዳያካፍል በስስት መሙላት

2. ነጻ ስጦታ እንዳይሰጥ ቢሰጥም ደግሞ ለታይታ እንዲሰጥ በማድረግ ዋጋውን ማሳጣት እንዲሁም ሰው ምፅዋትን ረስቶ በቀጥተኛም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ራሱን ተጠቃሚ እንዲያደርግ በማሰብ «በስለት»ስም ስጦታውን እንዲወስን በማድረግ ይህንንም ስጦታ ሰዎችም ብቻ ሳይሆኑ የአገልጋዬችንም ቀልብና ልቦና እንዲስብ በማድረግ በየመንፈሳዊ አንድነቱ፣ በየንግስ በዓሉ፣ ምዕመኑ ነፃ የምፅዋት ስጦታን ሣይሆን ስለትን እንዲለመማድ፣ ሰጥቶ የመቀበሉን ባህል እንዲያዳብር እገዛ ሲያደርግ እናያለን እርግጥ ስለት ለቤተክርስቲያን ሊሰጡ ከሚገባቸው አስራት በኩራት ከመሳሰሉት ነገሮች ጋር ተደምሮ ትልቅ የቤተክርስቲያን ስጦታ ተደርጐ ቢታሰብም ነገር ግን በአንዳንድ መንፈሳዊ መድረኮች ልምምዱ ከፍቶና ስር ሰዶ አንዳንዱን ታቦት ስለት ለመስማት ብቻ የቆመ እስክናስመስለው ድረስ ምዕመኑ በረከት ለማግኘት ሳይሆን ተስሎ ስጋዊ ፍላጐቱን ለመሙላት ብቻ ሲጠቀሙበት እናያለን እስቲ እነዚህን ሁለት የዚሁ የስለት ሱሰኞችን እንከታተል /**መንገድ ላይ ይገናኛሉ ከተለያየ መንገድ መጥተው**/

ትዕግስት፡-ዛሬ በስንት ጊዜያችን ተገናኘን ጃል.....

አበቡ፡- ምነው ትዕግስት ባለፈው ወርኮ ነው የተገናኘነው ትዝ አይልሽም ለዑራኤል የምሳለው አለ ብለሽ አልነበር እንዴ የሄድነው.....

ትዕግስት፡-ወይ የኔ ነገር እረስቼው ግን በጣም ይገርማል የተሳልኩትን ነግሬሻለሁ.....

አበቡ፡- አልነገርሽኝም...

ትዕግስት፡- ሂጂ ረስተሽው ነው፡፡ ዑራኤልዬ አንዱ አረብ አገር እባክህ ላስኝ ብዬ ከልቤ ነግሬው ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አንዷ ቤይሩት ያለች ጓደኛዬ ትኬት ልካልኝ በሚያስገርም ፍጥነት ሰሞኑን ልሄድ ነው ይሽው ዛሬ ሜዲካል ሰጥቼ መጣሁ ግን በናትሽ ሜዲካሉ ላይ ጥርጣሬ አለኝ እሱን ብቻ በጥበቡ ከረዳኝ የዛሬ ሳምንት ሽው ብዬ ሊባኖስ

አበቡ፡- አንቺስ ታድለሻል እኔ ግን ብጨቀጭቀው ብጨቀጭቀው አልሰማ ብሎኛል ይሽው እኔ እሳላለሁ ጓደኞቼ ይሄዱበታል ይሽው እኔ ስለት ሰሚ ሆኜ ቀረሁ

ትዕግስት፡- ..... ኧረ እኛ በአንቺ ስለት ነው እንዴ የምንሄደው ምነው የኛ ስለት አይሰማም ያለሽ ማነው ባክሽ

አበቡ፡- .....ቢሆንም እኔ ጭቅጨቃ ከጀመርኩ ቆየሁ አንቺ እንኳን ይሽው በወርሽ ትኬት መጣልሽ እኔ ግን ይኼው ከወር ወር እየሄድኩ እለምነዋለሁ ምንም የለም ወይኔ እናቴ ምን አይነት እድል ነው ያለኝ

ትዕግስት፡- ተይ እንጂ አበቡ አትማረሪ ዑራኤልዬ ሊሰጥሽ ይችላል እኔ እውነቴን ነው አልደበቅሽም የመጀመሪያው ወር ደሞዜ ላንተ ነው ብዬዋለሁ አይዞሽ አበቡ እኔ ደግሞ ከሄድኩ ላንቺ ትኬት እልክልሻለሁ

አበቡ፡-/በማሽሚጠጥ አፋን አጣማ/ ኡ..ኡ..ቴ ጽድቁ ቀርቶብኝ በቅጡ በኮነነኝ አሉ አሁን አንቺ ማን ይሙት እዛ ሄደሽ እኔ ትዝ እልሻለሁ? ዶላሩን ማን ሊቆጥርልሽ ነው? ይልቅ እሡን ተይውና ሜዲካሉ ምን አስፈራሽ?

ትዕግስት፡- እንዴ ምነካሽ ሰው አይደለሁ እንዴ ለምን አልፈራም ይኼ የዘመኑ ደዌ እንኳን እኛን ስንቱን.....

አበቡ፡- እና ታዲያ አንቺንም ትኬትሽን እንዳያቃጥለው ፈራሽ?

ትዕግስት፡- እንዴ ታዲያ እንደምታውቂው የምርመራው ውጤት በተቃራኒው ከሆነ ቲኬቱም ጊዜው አልፎ ይቃጠላል፡፡ እኔም ሞራሌ ደቆ ቆሞ በሰዎች መሀል የሚመላለስ የሞት ምስል ሆኜ እርፍ አለቀ! ብቻ ለዑራኤልዬ እነግረዋለሁ

አበቡ፡- ይሄ እንካን ያለፈ ማንነትሽ የሚወስነው ጉዳይ ይመስለኛል «ማንም የዘራውን ያንኑ ያጭዳል» እያሉ ባለፈው ቄሱ ሲያስተምሩ አልስማሽም እና አንቺም ትንሽ ቀባብጠሽ ከሆነ ጠርጥር ብላል ያገራሰው

ትዕግስት፡-ሂጅ ምነው አንቺ አሚራች...

አበቡ፡- እና ጨዋነኝ ለማለት ነው...

ትዕግስት፡- ስባልግ አላየሽኝም

አበቡ፡- ቢሆንም ለዚህ ጉዳይ ዑራኤልን ማስቸገር ያለብሽ አይመስለኝም

ትዕግስት፡- እሱ አንቺን አያገባሽም ዑራኤል ምንም የሚሣነው ነገር የለም ባለፈው ምስክርነት አልሰማሽም ኤድስ ይዞት የዳነ ሲመሰክር እና እኔም የደም ምርመራውን ነገር እንዲያሳካልኝ ብለምን ምንም አይደለም

አበቡ፡- ባይሳካስ? ስለትሽ የታለመለትን ግቡን ባይመታ ዑራኤልን ደሜን በከልከው የቫይረሱ ተሸካሚ አደረከኝ ብለሽ ልታማርሪው ነው

ትዕግስት፡- ምን ነካሽ የምን ማሚረት ነው የያዝሽው? ዑራኤልዬ ለምኜው የነሳኝ የለም ባል እንካን የሚመርጥልኝ እሱ ነው፡፡ ወይ ብሎ ነው የሚሰማኝ

አበቡ፡- አንቺ ልጅ አብደሻል መሰል እኔን ግን የላትም ብሎ ነው መሰል ብነግረውም አይሰማኝ

ትዕግስት፡- ተስፋ አትቁረጪ ነይ ዛሬም ሞክሪ .../ተያይዘው ይሄዳሉ/

ደቂ፡- አያችሁት የነዚህን ሰዎች ውሸት አካሔዳቸው ከጥቅማቸው ጋር በተያያዘ በስለት ፍቅር የተጠመዱ የአምላካቸውን ነፃ ስጦታ ለመቀበል ራሳቸውን በህጉ ያላነፁ በዝና እየተጐተቱ ምስክርነት ለመስማትና ሰምተውም ጥቅም ሰጥቶ ለመቀበል ተራና ምድራዊ በሆነ ሃሣብ የታሰሩ ናቸው፡፡ የአምላካቸውን ስጦታ ተራና ምድራዊ አድርገው የሚገምቱ ለጥቅማቸው ህሊናቸውን የሸጡ ፍጹም ከንቱዎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ለቤተክርስቲያን አስራት በኩራት እንዲያወጡ ከአስር አንድ ተጥሎባቸዋል ይህንን እንደ ነጻ ስጦታና እንደሚያጐድልባቸው ስለሚያስቡ ለመስጠት ፈቃደኛ አይደሉም በዚሁ ንፍገታቸው በረከት እርቋቸው በአንድ እጃቸው ተቀብለው በሁለት እጃቸው ይዘሩታል በአንድ መንገድ አስገብተው በሺ ቀዳዳ ያፈስሱታል፡፡ ስለታቸውም አምላካቸው የሰጣቸውን ቃል ኪዳን በጠበቀ መልኩ «ለምኑ ይሰጣችኃል አንኳኩ ይከፈትላችኃል» ባለው መሠረት ሣይሆን አምላካቸውን ካለ ጉቦ እንደማይንቀሳቀስ ምድራዊ ባለስልጣን በማየት ይኼን ብታደርግልኝ ይሄን አረግልሃለሁ የሚል አንድምታ ያለው አካሄድ ሲሄዱ ይታያሉ፡፡ ምኞታቸውን ስለት ብለው ረግጠውት የማያውቁትን ቤተክርስቲያን እሰከምኞታቸው ማጥብያ ድረስ ተመላልሰው ሲያበቁ ስለት ያሉት የምኞት ጥሩንባቸውን ነፍተው ካሰቡት ደርሰው ችግር ላይ ሲወድቁና ህይወታቸው ብቻ ሣይሆን ክርስትናቸውም ሲፈተን መንፈሳዊ ህይወታቸውን ከመፈተሽ ይልቅ የጠንቃይና የመናፍስት መሪዎችን ደጃፍ ሲያጣብቡ ይታያሉ **/ከመድረክ ጀርባ ይሰማል/**

«የሌለበት የለም የሌለበት
ባያጋልጠው ነው ባይጮህበት
የኔ እናት የኔ መድኃኒት
ቀን አይደል ልምጣወይ ሌሊት» **/ድቤ ይደበደባል/**
መልሰው አንተው መልሰው/2/
ምንጊዜም ደግ አይሰራም ሰው
ያመኛል እኔን/2/ ራሴን ምን ይሻለኛል **/ድቤ ይደለቃል/**

/አበቡና ትዕግስት መንገድ ይገናኛሉ ፤ ትዕግስት ፊቷ ተመላልጣል ሰውነቷ ጎስቁላል/

አበቡ፡- ምነው አንቺ! ምነው እንዲህ የተጋጨ መኪና መስለሽ? በውኑ አንቺ ነሽ?

ትዕግስት፡- እኔማ ባልሆነ አታወቂኝም ነበር...

አበቡ፡- ይገርማል ቲኬት መጣልኝ ብለሽ አልነበር እንዴ? ወይስ ያ የፈራሽው የደም ምርመራ ውጤት ጉድ ሠራሽ?

ትዕግስት፡- ኧረ እሱንስ አልፈውው ነበር ነገር ግን ከዛ በኃላ ነው ጉድ የፈላው

አበብ፡- ምን ሆንሽ ምን አገኘሽ?

ትዕግስት፡- .... እንዳለኩሽ ከዚህ ተሳክቶልኝ ሄድኩኝ ከዛ ግን የገባሁበት ቤት የሰው ቤት ሳይሆን በቁሙ ሲኦል ነው፡፡ በመጀመሪያ 24 ሰዓት እንደማሽን ሳታርፊ ትሰሪያለሽ እረፍት የሚባል ነገር የለም ከዚያም የመብት ጥያቄ ለማንሳት ስሞክር አርፌ ብሰራ እንደሚሻለኝ ገለፀልኝ ሰው ሁሉ ያዝሻል መፈጠርሽን እስክትጠይ በቀለምሽ ፣ በማንነትሽ ላይ እየተሳለቁ ይተፉብሻል ይዤን ሁሉ ችዬ ተቀመጥኩኝ ደሞዝ ግን አይከፍሉኝም ነበር፡፡ በኃላ ወኪሌን አግኝቼ ነገርኩት ያለኝ አማራጭ ተስማምቼ መስራት ብቻ እንደሆነ ነገረኝ ይህን ስሰማ ሲኦል እንደተወረወረች ነፍስ ሆንኩ ብቸኝነቱ ውስጤን ቀርጥፎ በላው፣ ባዶነት ውስጤ ነግሶ ተስፋ ቆረጥኩ፣ አማራጭ ባጣ መታመሜን ለባለቤቱ ነግሪያት ወደ ሃገሬ እንድትልከኝ ነገርካት፡፡ የነገረችኝ ነገር ግን በጣም አስደንጋጭ ነበር፡፡ «ልግመት አልወድም ትሰሪያለሽ ስሪ ካለበለዚያ ፎቅ ጫፍ ላይ ወስጄ አቁሜ በጭንቅላትሽ ወደታች እልክሻለሁ» አለችኝ ተስፋዬ ተሟጠጠ አንገቴን ደፍቼ ስሰራ ቆይቼ አንድ ቀን ለባሏ ብሶቴን ልናግር እሷ የለለችበትን አጋጣሚ ጠብቄ አገኘሁት ችግሬን ነገርኩት የራራልኝ መስሎኝ ነበር እሱ ግን በጭካኔ ካለ ፍላጐቴ አስገድዶ ደፈረኝ/ ይህም ብቻ አይደለም ግብረ ሰዶም ፈፀመብኝ/ ውስጤ አነባ ልቤ በስቃይ ቆሰለ በንጋታው ግን ያልጠበኩት ሆነ ሚስትየው ማን እንደነገራት አላውቅም ተደብቆ ያየን ሰይጣን ሹክ አላት መሰል የፈላ ውሃ እላዬ ላይ ገለበጠችብኝ ጨርሳ እንዳትገለኝም ጩኸቴ ባልየውን ቀስቅሶ ነፍሴ ተረፈች አሳዘንኩት መሰል ከዛ በኃላ በድብቅ አሳክሞኝ ሲሻለኝ ወደ ሃገሬ ላከኝ ይኸው ነው፡፡

አበቡ፡- **/አዝና/** በጣም ያሳዝናል በእውነት እንዲህ ዓይነት ነገር ይኖራል ብዬ አስቤም አላውቅም የምሰማው ሁሉ ውሸት ነው የመሰለኝ እንዴት ያሰቅቃል

ትዕግስት፡- እኔም እንደአንቺ ነበርኩ ግን ያየሽው ሆነ የተሳልኩትን ብር እንኳን መክፈል ሳልችል ነፍሴ በስቃይ ታመቀች በሴትነቴ ልሸከመው ከምችለው በላይ ተፈተንኩ የብዙ እህቶቻችንም ዕጣ ከኔ ብዙ የተለየ አይደለም የሥጋ ቅጣቴ የመንፈስ ስብራቴ መቼም ፈውስ የማይገኝለት ዘለአለማዊ ቅጣት ነው ሰው መሆን በራሱ ምን ያህል መከራ ማለት እንደሆነ በተግባር አየሁት

አበቡ፡- ታዲያ አሁን የት ልትሄጂ ነው?

ትዕግስት፡- በአምላኬ ላይ ያለኝን ተስፋ ጨርሼ ወደ አዋቂ ቤት እየሄድኩ ነበር ያገኘሺኝ

አበቡ፡- በጣም የሚገርም አጋጣሚ ነው እኔም መንገዴ ወደዛው ነበር

ትዕግስት፡- ታዲያ ጥሩ እንሂዳ

አበቡ፡- የለም ሰርገፍዋለሁ እግዚአብሔር አስተምሮኛል አምላኬ እምቢ ቢለኝ ከሰይጣን ጋር ተደራድሬ ለመሄድ ነበር አሳቤ፤ ግን አሁን በቃ እግዚአብሔር በአንቺ አስተማረኝ እህቴ ሆይ አንቺም ይቅርብሽ እኔ ላለፈው ሃጢያቴ ንስሐ እገባለሁ

ትዕግስት፡- እኔ እግዚአብሔርን ምን አደረኩት ለሌላው መማሪያ የሚያደርገኝ ስለቴንም ያልከፈልኩት ሴትየዋ ደሞዜን ስላልከፈለችኝ ነው ብቻ በቃ ከእንግዲህ ሴትነቴ ጠፍቷል ሞራሌ ላይጠገን ተሰብሯል፤ በእግዚአብሔር ላይ ያለኝ ተስፋ ተሟጦ ውሰጤ የሞት ወጀብ ነግሳል እስቲ እይኝ ምን እመስላለሁ የቀድሞ ማንነቴ አይደለም ሴት የመሆኔ አሻራ እንኳን ጠፍቷል ታዲያ ከዚህ የበለጠ ቅጣት በምድር ላይ ምን ይገኛል **/ታለቅሳለች/** አዝናለሁ አበበች ከዚህ በላይ ላናግርሽ አልችልም አንቺን ግን አንድ የምልሽ ነገር ስለትሽ ባለመድረሱ እድለኛ ነሽ እግዚአብሔር ጠብቆሻል እኔ.....ግን.....እኔግን...../**እንባ/** እያለቀሰች ወደ ውስጥ ትገባለች አበበች ትመለሳለች/**ከውስጥ/**

«የሌለበት የለም የሌለበት
ባያጋልጠው ነው ባይጮህበት
መልሰው አንተው መልሰው/2/
ምንጊዜም ደግ አይሰራም ሰው/**ተደጋግሞ ይሰማል/**

ደቂ፡- አያችኃቸው በምኞታቸው ሲጠመዱ እኚህ አስቂኝ ፍጥረቶች

ዋና ኃላፊ፡- በእውነት ይህ ድንቅ ትርኢት ነው፡፡ እስቲ እዩ ለሰው ልጅኮ ከኛ የበለጠ ለራሱ ጠላቱ ራሱ ነው፡፡ አሁን ይህቺ ልጅ ብር እንጂ አምላክ ወደሌለበት ምድር ጥቅም አይታ ነጎደች የናፈቀችውን አልቅሳለት የሄደችውን ዶላር አይኑን እንካን ሳታይ የመከራ ገፈቷን ልማ መጣች ታዲያ ለዚህች ልጅ ጠላቷ እኛ ሳንሆን ምኞታ ነው እኛ በውጤቱ መደሰት ብቻ ነው ድርሻችን **/ይስቃሉ/**

ጸሎት ጦሩ፡- .....ኢ.....ሂ.....ሂ...ሂ/**ይስቃል/** የሰው ልጅ እኮ ኮሚክ ፍጥረት ነው ሁሉን ነገር በራሱ ምኞት በራሱ የስሜት ግፊት ይፈፅምና ምነው ይሄን ሰራህ ሲሉት ሰይጣን አሳሳተኝ ይላል እንደኛ አለየለትም እንጂ ከሰው ልጅ የበለጠ ሰይጣን የለም እስቲ እኛ ከሱ የከፋ ምን ሰራን እራሳችንን ከአምላክ ጋር በማወዳደራችን አይደል ወደ ታች የተወረወርነው እንዳውም እሱ ነው ተሳስቶ የሚያሳስተን

ዋና ኃላፊ፡- ትክክል ነው ይህ ቀጣፊ ሌባ እንዳውም በአሁኑ ሰዓት እኛ ከምንሰራው የበለጠ ክፋት እየሰራ ያለው እሱ ነው ኧረ እንዳውም ሰልጥኗል እኛ ኒውክለር መች ሰራን? እኛ ታንክ ፣ሚሳዬል መች ሰራን?

ደቂ፡- ጌታው ቴክኖሎጂው የእርሱ ይሁን እንጂ የጥፋት ቀመሩ የኛ ነው ጥፋት፣ጦርነት፣እልቂት የኛ ትምህርቶች ናቸው አይደል እንዴ?

ዋና ሃላፊ፡- ቢሆንም ቢሆንም ..... ሰይጣን አሳሳተን ሊሉ አይገባም እነሱ ናቸው እኛን እያሳሳቱን ያሉት እነርሱ ለአምላካቸው መታመናቸውን ባያጎድሉ እኛ በየት በኩል እናገኛቸዋለን እስቲ ክቡራት በአለም ላይ ስንት መዓት ፣ ሀጢያት የሰው ልጅ እየሰራ ወገኑን እያረደ መወገዝና መጣላት የሚገባው እሱ ሆኖ ሳለ በየጠበሉ በየንግሱ ቦታ ውጡ እየተባልን በመስቀል የምንደበደበው እኛ ነን እሱ ግን የሰው ልጅ ምድርን በቦንብ እያነደደ እራሱ በፈጠረው መሳሪያ ወገኑን እያረገፈ እንኳንስ በመስቀል ሊገስፁት ሊነኩት አይደፍሩም ሁሉም እየተነሳ ሰይጣን እያለ እርግማኑን ሲያፈስብን ሲውል ያድራል።

ደቂ፡- ዋናዎቹስ ቢሆኑ ቤተክርስቲያን በራፍ ላይ ከሚኮለኮለው መስኪን የበለጠ ስብከቱ ላይና ወንጌልን ማስተማሩ ላይ ሳይሆኑ የምጽዋት ሽሚያ ውስጥ ገብተው በተለያዩ ምክኒያቶች እያሳበቡ የብር ያለህ ሲሉ ነው የምናያቸው መች እንዲህ አይነቱን አንኳን ጥፋት ይቃወማሉ።

ዋና ሃላፊ፡- እርግጥ ነው ከተፈቀደላቸው በላይ ይሄዳሉ መቼም አንዴ ሰይጣን ብለውናል ምንም ብንል ምንም ብናረግ ከዚህ የበለጠ ስም ሊሰጠን አይችሉም አይደል እንዴ ወገኖቼ...../**አም በሕብረት**/ መቼም በሰዎች ላይ አድረን ወደ ጸበል ቦታ እንሄዳለን እዛም የአምላካቸው ገጸ በረከት በብር ሲሸጡ እናይ የለ ምን ይሄ ብቻ ለአመዳደቡም ደረጃ ወጥቶለት ደሃ የማይቀምሰው ደሃ የማይገባበትም የጸበል ቦት እንዳለ እናውቃለን ይህን ይክዱታል.....?

የጸሎት ጦሩ፡- ልክ ነው እንዲውም የአምላካቸው ቸርነት በአንዱ ጻድቃን ወይም ሰማዕት ወይም መላዕክት ስም ሲገለጥ ሰዎች ወደዚያ ተጓምራዊ ቦታ መጓዝ ይጀምራሉ። ለምን በባህሪያቸው ክፉዎችና ምልክት ፈላጊዎች በመሆናቸው ሩጫቸው ወደዚያ ይሆናል የእከሌ ጸበል ፈልቋል ይባልና አለም ሁሉ ወደ እዚያ ይሆናል። ከዛ ምን እንደሚሆን ታውቃላችሁ ተያይዞ የዛ ጸበል ገበያ ይደራል። በረከቱን ይሸጡታል ወዲያውም በሀጢያታቸው ፈውሱና ረድኤቱ ይርቃቸዋል እንደውም እራሴ በበላይነት የምመራውን የአገልግሎት እወካ ክፍል ሪፖርትን አያያዝ ላቅርብ..... በአሁኑ ወቅት ዋናው የአገልግሎት መምቻና ማወኪያችን ገንዘብ ነው። በገንዘብም አማካኝነት የአገልጋዮች አገልግሎት ተከፋፍሏል..... እስቲ ይህን ምስል እንመልከት። **/የማይነበብ ማህተብ ያለበት ወረቀት የያዙ ካህናት ይለምናል።/**

ካህናት፡- በአርባ ምንጭ ክፍል ሀገር ለሚገኘው ለቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ማሰሪያና ማስጠገኛ እጃችሁን ዘርጉልን ምዕመናን የተራቆተች ቤተ ክርስቲያን አልብሱኝ ትላለች በ----------ቦታ የተቃጠለች ቤተክርስቲያን ናት እባካቹሁ.....

ወጣቶች፡- /ወጣቶች በህብረት/ በወሎ ለሚገኘው ለ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ማሰሪያ የሚሆን እጃችሁን ዘርጉልን ፍጻሜውን ያሳይልን.....ወዘተ

ዋና ሃላፊ፡- ታያቸኋላችሁ እነዚህን አገልጋዮች የአምላካችሁ ሕያው ቤተ መቅደስ የሆነው ሰው ፈርሶ በሀጥያት እሳት ነዶ ሲቃጠል ቁብ ያልሰጣቸው አምላካቸው ቤተ መቅደሴ የሚለው ሰው በኋጥያት ክፋት ሲፈርስ እነርሱ ግን መንገድ ላይ ጨርቅ ዘርግተው ባለውም በሌለውም ቤተክርስቲያን ስም በተቃጠለውም ባልተቃጠለውም ድቃቂ ሳንቲም ይለቃቅማሉ መንጋው እዚህ ጋር ተረስቷል። በምንኩስናም አለ የተለየው አለም ናፍቆት ናፍቆቱ ሲያገረሽበት ቆቡን ቀልብሶ ቀሚሱን እየጐተተ ወደ ማራኪዋና ብልጭልጯ አለም ዘው ይላል። ከገዳም የሥጋ ምኞት አሸንፎኝ መጣሁ እንዳይልም ከእኛ ጋር የውሸት ታጌላ ይለጠፍለታል ራዕይ ታየኝ ይልና ኮብልሎ የቤተክርስቲያን አውደ ምህረት ከሚሰጠውን ትምህርት ቸል በማለት ምዕመኑን ከቤተክርስቲያን ውጭ እናስተመራለን በማለት አንድ የሆነውን ማህበረ ምዕመን ሲከፍል ይታያል በአንድ እጁ መሰቀል እያሳለመ በሌላው እጁ ፍርፋራ ሳንቲሞችን ሲለቃቅም ይታያል። ህዝቡን በስሜት ጐርፍ ይዞ ሲነዳ ይከርምና ወዲያው ደግሞ ከዓይን ይሰወራል እስቲ ይህን ምስል እንመልከት.....

ባህታዊ፡-አንተ የአዳም ልጅ ወዮልህ ምጽአት ቀርቧል እሳት ከሰማይ ይዘንባል የገሃነም ደጆች ተከፍተዋል በራዕይ ተመርቼ ነው የመጣሁት ኡ ኡ በል እሪ በል ዋይ-ዋይ-ዋይ በል ምህላ አድርስ አምላክህ ተቆጥቷል ቤተክርስቲያንም ወዮላት በኃጢያት ጠፍታለች.....

/ራቅ ብሎ ደግሞ ከጐኑ አንድ በአንድ እግሩ ቆሞ መጽሐፍ ደርድሮ ያነበንባል አሮጊቶች ከበውታል በመሃል ጸሎቱን እያቆመ

ጸሎተኛ፡- ምን አለ ያ ደግሞ ድምጹን ቢቀንስ ምኑ ልቅ አፍ ነው እሱ ብቻ ነው እንዴ መምህር..... እሱ ብቻ ነው እንዴ ደቀመዝሙር እኛስ መክሊት አልተቀበልንም ማስተማር የለብንም ተመልሶ በረጅሙ ያነበንባል።

ባህታዊ፡-/ወደ ጸሎተኛ እየጠቆመ/ በዚያን ጊዜ ሃሣዊ መሲሃን ይመጣሉ ይላል አሥ አሁንም መጥተዋል እኛው። እኛ በየት በኩል አስተምረን ሕዝባችንን እንመልስ ሁሉም ፊደል የቆጠረ እኩል ከእኛ ከገዳማውያኑ እኩል ላስተምር ይላል ብቻ ወገኖቼ እኔ ያየሁት ራዕይ ከሰማይ ዘንዶ ሲወርድ ምድሪቱንም ሲውጥ..... ነው

ህዝቡ፡- .....እግዚኦ..... እግዚኦ አምላክ.....

ባህታዊ፡- .....በሉ እግዚኦ በሉ....

ህዝቡ፡- እግዚኦ..... መሃረነ ክርስቶስ

ጸሎተኛ፡- እዩ ቤተክርስቲያን ትምህርት እየተሰጠ ሲበጠብጥ ማነህ አንተ እባክህ እንጸልይበት እንማርበት እናስተምርበት አንተ ብቻ አይደለህም መክሊት የተሰጠህ.....

ባህታዊ፡-ማንን ነው አንተ እኔን ነው እንዴ ጭራቅ!!! በሉ እግዚኦ በሉ.....እግዚኦ በእንተ ማርያም

ጸሎተኛ፡- በዚያን ጊዜ ኢየሱስም አለ የበግ ለምድ ለብሰው በስሜ ይመጣሉና ተጠንቀቁ መንጋውንም ይነጥቃሉ.....

ባህታዊ፡- አንተ እረፍ ብያለው እረፍ አሸሙርህን ተወኝ.....እንዳንተ ከመንደር አልመጣሁም አሳይሃለሁ ዋ .....እግዚኦ በሉ..... እግዚኦ.....

ጸሎተኛ፡- የጸሎቱን ድምጽ ከፍ አድርጐ ያነበንባል

ባህታዊ፡- እንደ ነገርኳችሁ ዘንዶ ከሰማይ ወርዶ ከነምናምኗ ምድርን ሲውጣት አየሁ አይደል ያልኳችሁ እንዲያውም ይህንን ሰውዬ **/ወደ ጸሎተኛው እየጠቆመ/** እሱን ሲውጠው ነው ያየሁት አዎ ዋጥ ሲያደርገው ነው ያየሁት ..... ዋጠውና.....እየዋጠው ውጦት ምን ታየኛለህ እንደውም አንተ ነህ ዘንዶውን የዋጥከው

ጸሎተኛ፡- .....ማ አንተ ማ እኔ ሰውየው ምነካው ማን ደረሰብህ አትረብሸን ነው እኮ ያልንህ.....

ባህታዊ፡- ምን አግብቶህ ማን አስተማሪ አድርጎህ? መናፍቅ

ሕዝቡ- ኧረ ክርክሩን ትታችሁ አስተምሩን.....

ጸሎተኛ፡- /ያነበንባል በድምፀት/

ባህታዊ፡- ..... ጋንጩር! በሉ እግዚኦ በሉ ፍፃሜው ቀርቧል ሰይፍ ተመዟል ካልጋችሁ ወርዳችሁ አልቅሱ እግዚኦ በሉ.....

ሕዝቡ፡- .....እግዚኦ.....

ባህታዊ፡-/ከሰው መሃል እየወጣ/ ነናግረናል.....ተው ብለናል **/በመቋሚያ ወደ ጸሎተኛው እየጠቆመ/** ዋልህ፣ ዋልሽ፣ ወዮልህ፣ ወዮልሽ...../**እያለ ይወጣል/**

ጸሎተኛ፡-/መጽሐፉን እየሰበሰበ/ ምድረ መናፍቅ የበግ ለምድ ለባሽ ሁሉ ተነቅቶብሻል አሂሂ እንዲህ ቀላል መሰለንሃል የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እምነት ቢኖራችሁ ተራራውን ታፈርሳላችሁ አይደል የተባልነው ዋ.....ብቻ **/እናያለን ተከትሎት ይገባል ሕዝቡ ይበታተናል/**

ዋና ሃላፊ፡- .....አያችኋቸው እነዚህን የስሜት መምህራን መንጋውን ሊያውኩ አያችሁ የእኛን ድንቅ አሰራር ሕብረቱን ስንከፍል፤ አንድነቱን ስናውክ፤ በቤተክርስቲያን የሚሰጠውን ትምህርት የሚሰማ የለም ሁሉም የገዛ ስሜቱን ኮርኩሮ ስሜቱን ሰማይ የሚያደርሱት በጊዜያዊ መንፈሳዊ ተሃድሶ የሚያነቃቃውን መምህር ፍለጋ የጮኸውን ሁሉ ሲከተል የቤተክርስቲያን ትምህርት ሜዳ ላይ ፈሶ ይቀራል።

ደቂ፡- ምን ይሄ ብቻ ቅዳሴ እየተቀደሰ ሰው ሲወጣ ሲገባ አገልጋዮችም ሆኑ የቤተክርስቲያን ጥበቃ ሰራተኞች አይከለክሉም። እንዲያውም ካህናቱና ዲያቆናቱ በስለት የሚገቡ ንዋየ ቅዱሳትንና የምጽዋት ገንዘብን ይሰበስባሉ ምዕመኑም በበኩሉ ቆሞ ከማስቀደስና ታቦት ከማንገስ ይልቅ በተመቸው ሰዓት መጥቶ ተሳልሞ ቤተክርስቲያኑ በራፍ አካባቢ ከተዘረጋው ገበያ

የሚሻውን ሲሸምት ይታያል ሳሩን፣ ጀበናውን ፣ጆሮ ጌጡን አርቴፍሻል ቀለበቱን አያችሁ ጽድቃቸውን.....

ዋና ሃላፊ፡- ምዕመኑን ክርስቲያናዊ ግዴታውን እንዳይወጣ በንፍገትና በስስት ስለሚዋጥ አስራቱን ስለማያወጣ ብዙዎቹ ቤተክርስቲያኖች የራሳቸውን ገቢ ለመፍጠር ሲጣጣሩ ይታያሉ ሰውም ወደ ቤተክርስቲያን ሲመጣ ጥቅሙ ላይ አነጣጥሮ ነው አስራትን እንደ ነጻ ስጦታ እና እንደ ኪሳራ ስለሚቆጥረው አያወጣም እሰቲ ይህን ተመልከቱ::

ሽማግሌ፡-አቤት የሌባ መዓት አቤት ሌባ **/ወደ ሰው እየጠቆሙ/** አንተ ፣ አንቺ ፣ እናንተ ምድረ ሌባ ሁሉ.....

ወጣት፡- ማ አንተ ጃጃታም ሽማግሌ ማነው ሌባ.....?

ጐልማሳ፡- የማነው ደፋር ሰውን ከመሬት ተነስቶ ሌባ ይላል እንዴ ምን አይነቱ ወራዳ ነው ጃል::

ሽማግሌ፡- አሁን አልሰረኩም ለማለት ነው ሁልሽም ሰርቀሻል ሞላጫ.....

እናት፡- እንዴ ሰውዬ ይከበሩ ማንን ነው የሚሉት የማናቸው ፉዞ! ሰርቋል የሚሉትን ለይተው ይናገሩ እንጂ ሁሉንም በጅምላ ሌባ ማለት አይችሉም::

ሽማግሌ፡- **/ኢሂሂሂ-ሂ ቂቂቂ ይስቃሉ/** ሌባ ሁሉ አሁን እስቲ ማን ያልሰረቀ አለ ንጹህ አለ ንጹሕ ነኝ ብላችሁ የምታምኑ ከሆነ ተፈተሹ እስቲ.....

ወጣት፡- ..... እንዴ ..... ሽማግሌው ምነካው ና እንደውም ፈትሽ.....

እናት፡- ፈትሽ የጠፋህን

/እየዞሩ እየፈተሹ ከኪሳቸው ገንዘብ ያወጣሉ/

ሽማግሌ፡- ይሄ ብር የተሰረቀ ብር አይደለም:: ተሳሳትኩ

ወጣት፡- እብድ ሽማግሌ በል ብሬን አምጣ.....

ሽማግሌ፡- ቆይ ቆይ ሁላችንም ሌባ ነን እኔም ጭምር የሰረቅነው ተገኝቶብናል

ሙንዳሲር፡- እኔ ግን የለሁበትም የጫት ብሬን ነው የያዝኩት **/በጉራጊኛ ቅላጼ/**

ሽማግሌ፡- አንተም ሌባ ነህ.....

ሙንዳሲር፡- እንዴ ሽማግሌው ምን ነካው ብትፈልግ እዚያ ሱቅ ሄደህ ሽኩርን ጠይቅ ይነግርሃል የጫት ብር ነው::

ሽማግሌ፡- አንተም እኔም እናንተም ሕዝቡ ሁሉ ሌባ ነው:: የሰረቅነው እግዚአብሔርን ነው

ሙንዳሲር፡- ያ አላህ ሸማግሌው አብደዋል ወይም አንዳች ቅጠል ቢጤ በልቷል ደሞ እኛ አላህን የት አግኝተነው ነው የምንሰርቀው **/አሁሁ..... ይስቃሉ/** ግዴለም ሰዎች ሸማግሌው ለይቶለታል

እናት፡- ኧረ ይህ የመጃጃት ውጤት ነው ይልቅ ብራችንን አምጡ ምን ይላሉ እኚህ ሰራ ፈት እኛንም ስራ ፈት አደረጉን እኮ

ሸማግሌ፡-ዓለም ሁላችንም እግዚአብሔርን ሰርቀናል የሰረቅነውም አስራቱን ነው አስራቱን ሰርቀናል፡፡

ሙንዳሴር፡- ወላሂ ይሄ ሰው ሃሺሽ ወስዷል አስራት በጣም ትልቅና ረዥም የኢትዮጵያ ሰው ነው እኛ እሱን ከየት አግኝተን ነው የምንሰርቀው ወላሂ ይህ ሰው አብዷል፡፡

ሸማግሌ፡-ስሙኝ ወገኖቼ **/ጥቅሱን ይነባሉ/** ስለዚህ ይህ ብር በመሉ የእኛ አይደለም የእግዚአብሔርን ብር እየበላን ነው፡፡

ሙንዳሲር፡- አስራትን ወስዳችሁ ካልክ ኪሳችንን ፈትሸና እይ ያን የሚያክል ረዥም ሰው የት እናረገዋልን ይልቅ ብሬን ስጠኝ የቂማ ሰአት ያልፍብኛል ደግሞም የቢዝነስ ሰዓት ነው አቦ ነጂስ አትሁንብኝ

ሸማግሌ፡- አንተኛው እንካ ባታምንም ባለ እዳ ነህ አስራት የመክፈል ግዴታ አለብህ **/ይሰጡታል/**

ሙንደሲር፡- አሰራት ወክማ ነው ያለው እዚህ የለም እንኳን አስራትን እኔ ጎራውንም አልሰረኩም ቻው፡፡

ሸማግሌ፡- ወገኖቼ እናንተስ ይኸው ብራችሁ...../**ይሰጣቸዋል/** አስራታችሁን አውጡ.....

ወጣት፡- ምነካው ሸማግሌ ከአሰር አንድ እኮ ማለት ከመቶ አስር፣ ከሺ መቶ ብር ማለት ነው ለምሳሌ እኔ ኪሴ ያለችኝ 30 ብር ናት ሶስት ብር ልስጥ ማለት ነው የለም አላደርገውም፡፡ **/ይሄዳል/**

እናት፡-ወቸው ጉድ ከቤት ወጪ ብር ከአሰር አንድ ሰጥቼ ምን ሊተርፈኝ የኑሮ ወድነቱ ሰማይ ነክቶ ሸሮው ፣ በርበሬ፣ ዘይቱ ፣ ጤፉ አረምኑቅጡ ሰዎችዬ ጊዜው ብር እንደጦመን የሚበላበት ሆናል ታዲያ ከአስር አንድ ኧረ! ወዲያልኝ...../**ይሄዳሉ/**

ጉልማሳ፡- እውነታቸውን ነው ፈትናችሁ እዩኝ የጎደለውን ባልሞላ ብሎ የለ እኔ አሁን ቤተክርስቲያን ሄጄ እሰጣለሁ አምናለሁ እግዚአብሔር ጉዶሎዬን ይሞላል.../**ይሄዳል/**

ሸማግሌ፡- «....አዎ እኔም ከጡረታዬ ላይ እሰጣለሁ ሁላችሁም ሌባ እንዳትባሉ ስጡ.....አምላካችሁ ኪሣችሁ ውስጥ ያለውን ያውቃል **/ይሄዳሉ/**

ዋና ሀላፊ፡-አያችሁ የሰው ልጆችን ንፍገት ገንዘብን ራሳቸው ፈጠሩት አሁን ግን ገንዘብ ራሱ መልሶ ፈጠራቸው፡፡ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት

አይኑሩህ ቢባልም የሰው ልጅ ግን በገዛ እጁ የሚያመልከውን አምላክ ሰራ ገንዘብን ለእርሱም ጎንበስ ብሎ ሰገደለት።

እንግዲህ ከቀረበው ዘገባ አኳያ በንቃትና በትጋት ያከናወነውን የሰው ልጅ ወደ ጥፋት መካተት አላማ ከሞላ ጎደል እየተወጣን መሆናችን ዘገባው ይገልጻል። እንግዲህ ከዚህ ተነስተን ወደ ፊት የጥፋት አላማ ለማከናወን መትጋት ያለብን ይመስለናል።

በተሰጠን የሰራ መደብ በአየርና በየብስ እየተመላለስን የሰውን ልጅ በህሊናው፣ በግብሩ፣ በሐሳቡ እንዲስት ጸሎት ፣ ጾም፣ ስግደት የመሳሰሉትን ከአምላኩ ጋር የሚገናኝባቸውን ግድግዳዎች ዳግም እንዳይጠጋ እናድርገው።

ይህ እነኳን ባይሆን በማስመሰል እንዲኖር ከእውነተኛ ኃይማኖት አውጥተው በስጋው እንዲመቸው ወደተዘጋጁት ፎርጅድ ወደ ሆኑ ሀይማኖት ማስገባት እቅድና አላማችን ሊሆን ይገባል።

ክቡራን የጥልቅ አለም የጨለማው ባለስልጣናት ያየናቸው የተወሰኑ ዘገባዎች ቢሆኑም ለሎች ድንቅ ስራዎችንን በሌላ ዝግ ስብሰባችን እንመለከታለን።


በሉ ለጥፋት እንነሳ! ሲኦል ውስጥ እንዳሉ ችሎት የሚያንቀላፉበት ጊዜ አልፋል ታጥቀን የሰውን ዘር ሁሉ በገሀነም የማኖር ትጋታችንን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርብናል ለዚህም ንግግር በአንድ ጽምፅ «የገሀነም ውስጥ ስቃያችን ከሰው ልጆች ጋር ይሆናል።» በማለት ስብሰባችንን እንዘጋለን።

«የገሀነም ውስጥ ስቃያችን ከሰው ልጆች ጋር ይሆናል።»

መጋረጃ ይዘጋል

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
ወለወላዲቱ ድንግል
ወለመስቀሉ ክቡር

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን::



ትዕይንት ፩

በአንድ ሆስፒታል ውስጥ ህክምና ለማግኘት ተራ ይዘው በሽተኞች ወረፋ ይጠብቃሉ:: በህመም አብዝቶ የሚሰል፣ ተፈንክቶ ጨንቅላቱ የታሰረ ወዘተ የተለያዩ ታካሚዎች ተራ ይጠብቃሉ:: አንድ ካርድ ይዞ ስም እየጠራ የሚያስገባ ነጭ ጓወን ለብሶ ህመምተኞችን ተራ ያስከብራል ህመምተኛው ገሚሱ የሚሰል ሌላው የሚያቃስት እንደበሽታው አይነት ብሶቱን የሚያሰማ ነው::

ህመምተኛ:-አሁ.....አሁ...እባካችሁ እነ ዶክተር ሰብስባችሁ እንደቲያትር አትመልከቱን ፈጠን ፈጠን ብላችሁ የሚደረገውን አድርጉ:: ስለፈጣሪ ይሽው እኔ ከመጣሁ ጀምሮ ፍም ላይ እንደተጣደ ዶኬ እንተከተካለሁ:: አሁ.....አሁ..... ግን ማንም ያዘነልኝ የለም አሁ.....

ቶሌራ:- ሰውዬ ሆስፒታሏ ላንቺ ብቻ አልቀመችም መንተክተክ አይደለም ለሚን አትገነፍይም እኛ ሲራኖ ወርኪኖ የያዘኖ ተራሺን ሳይደርሲሽ አትገቢም::

እናት:- ኧረ ባክህ ልጄ ይኸውልህ ይኼ ልጅ እዚህ በድንገተኛ መጥቶ ያደረ ነው:: እየው ጭንቅላቱ ተፈንክቶ ወጥ መስሏል ግን በሥርዓቱ ተራውን እየጠበቀ ነው ካልገባው ብሎ አላስቸገረም እና ጎበዝ እንደወረፋችን መሄዱ ነው የሚሻለው::

ቶሌራ:- ጐበዚች ታስተዊቃለች የተማረች ስሚ እያንዳንዲሽ ከላተራሽ ኒቅኒቃለሁ ብትይ ቶሌራ ዚም ብሎ አያይሽም ዘጊቼ እወጣና በኃላ ስትጮሂ ቲውያለሽ ጠንቅቂ ብቻ

አባት:- አቤት የሆስፒታል መከራ ወረፋው ማብቂያ የለው አቤት! መቼ ይሆን ካለወረፋ ወጥተን የምንገባው ስንወለድ በወረፋ ስንኖር በወረፋ ስንሞት በወረፋ ወረፋ...ወረፋ...ወረፋ ለሁሉ ነገር ተራ ገብተን ዳቦ ቤት፣ በገንዘባችን ለመታከም በወረፋ መቼ ይሆን ካለወረፋ ወጥተን የምንገባው አለልቼ የህይወት ጉዞ::

እናት:- ልክኖት አባቴ ጥሩ አይተዋል ለሁሉ ነገር ተወርፈን እንዴት እንደሚሆን?

ቶሌራ:- /ካርድ እያየ/ ዳጨው ተምትሜ /ተጠሪው አቤት ብሎ ይገባል/ ስትጠሪ ቂፊኒን አትበይ እኛ ጋር ጊዜ የለችም ህይወት የሚናድን ሩጫ ጊዜናት እያንዳንዷ ደቂቃ ስራ አላት የሙያችን ጉዳይ ናት ያቆመች /ወደ ውስጥ ይገባል/

ሲሻው፡- ለሰው ስሙ ጠላቱ ይሆነዋል? ወይኔ እኔ ሲሻው አባቴ ዛፍ ቆራጭ ነበር ኑሮ ከብዶት አናቱን ሲያዞረው እኔ ስድስተኛ ልጅ ሆኜ ብወለድ ሲሻው አለኝ። እግዜሩ ሲሻው ሰጠኝ ለማለት ፈልጐ ነው ይህንን ስም የሰጠህ ብላ ነግራኛለች እናቴ። ታዲያ ይኸውላችሁ ሲሻው ፈጠረኝ፣ ሲሻው ይቆርጠኛል፣ ሲሻው ይፈልጠኛል፣ ሲሻው ደግሞ ነፍሴን አስቶ ከአደባባይ ጥሎ ያስንራኝል። እና ይኸውላችሁ ወገኖቼ የበሽታ ዲፖ አርጎ ፈጥሮኝ እዚህቹ መከረኛ ግንብ ላይ ጥዶ በስቃይ ይቆለኛል። /እጁን ዘርግቶ/ ወገኖች የቻላችሁትን እርዱኝ ብርም ሆነ ሁለት ብር አነሰ በዛ አልልም የመርፌ እራት ሆኜ መቀመጫዬ ወንፊት ሆነ እባካችሁ አትጨክኑብኝ።

ቶሌራ፡- /በር ላይ ቆሞ ይሰማና/ ቲለብስ የላት ቲከናነብ አማራት አለቺ አማራ እስት አሚሳንቲ ሳታገኚ ሁለት ቢር ቲያለሽ ቀልደኛ ለማኝ ሂሊተን ያለሽ መሰለሽ እንዴ ጐበዝ ሆስፒታል እኮ ነሽ ደግሞ መንገዱን ለቀቅ አርጊ ሰው ይለፍበት ቤተክርስቲያን ሄደሽ ለሚኚ

ሲሻው፡- አሁን አንተ ላይ ማን ደረሰብህ ስጠኝ ያለህ የለ ሃብታም ለሰጠ ደሃም አከከ ነው የሚሉት

ቶሎራ፡- አፊሽን ሰብስቢ አንቺ ቡቱታም በኋላ በዘበኚች አስቀፍድጀ እንዳትወጪ ሊቂቃሚ። እዚች ጋ ያለች ሺማግሌ የታለች ኢመጣለሁ ብላ አይደለ የወጣችው

እናት፡- አሉ ይመጣሉ ቁርስ ቢጤ አፌ ጣል አርጌ ልምጣ ብለው ነው የሄዱት እንዳውም እኛው መጡ

ሰጠኝ፡- አቤት አቤት አይ ጊዜ አያመጣው የለ ኪኒን የምታክል ዳቦ ጋግረው የሚሸጡት እንድንበላት ነው እንድንውጣት? ጉድ እኮ ነው ገበሬ መዝራቱን፣ ዝናብ መዝነቡን፣ፀሃይ ማብሰሉን አልተወ ብቻ ሁሉ ነገር ሲወደድ ነው የምናየው ሰው ብቻ የረከሰበት ምድር አቤት ያንተ ስራ /በአግራሞት/ ቆም ብለው በንዴት ወደ ሰው እያዩ/ ትክብዬ ሳያት ዓለም ተግጣ ያለቀች የበሬ አጥንት ትመስለኛለች ህዝቦቿም ደግሞ በአጥንቱ ላይ የሰፈሩ የጉንዳን ሰራዊት ይመስላሉ እሷ ግን ተግጣ አልቃለች እላያ ላይ የቀሩትን ተረፈ ስጋዎች ለመቀራመት ምድረ ጉንዳን ይተራመሣል። አቤት የጉንዳን መዐት /ወደ ህዝቡ እያዩ/ ምን ጉንዳን ብቻ ይህ ህዝብ በዓለም ላይ የተጣበቀ አልቅት ነው። ይህችን ደሟ ተመጦ ያለቀ ባዶ ዓለም የሚመጠምጥ ቆዳዋ ላይ የሙጢኝ ያለ ምስጥ ነው። ምን ዋጋ አለው ሰው ሁሉ አላወቀም እንጂ ዓለም ተበልታ ያለቀች የነጋዴ እቁብ ናት /ወደ መድረክ ይወጣሉ/ እንዴት ነው ጐበዝ ፈውሳችሁን ሽጡልንና እንሂድ መቼም ኃጥያታችን ነው የእናንተ መድሃኒት ቤት የሚያደርገን

ሲሻው፡- ልክ ኖት አባት እኛ ጥቁሮች የፈረንጅ መድሃኒት ቤት ሆነናል እነሱም በሰውር እየበዘበዙን ነፍጥ እየሰጡ እያዋጉን ምድራችንን በኃጢአት እንድትቃጠል ምክንያት እየሆኑ በእርዳታ ስም እየመጡ ----------እየወሰዱ አረማችውን ይዘሩብንና ለበሽታ ይዳርጉናል ከዚያም በሰይጣን ላብራቶሪያቸው የፈበረኩትን ኪኒን ምድራችን ላይ ያራግፉብናል። ይኸው እኛም ሳናቋርጥ በደንበኝነት እንቅምላቸዋለን።

ቶሌራ፡- አሁን አንቺ ስለ ፈረንጅ ስለ ኪኒና ሚን ታውቃለሽ ለራሲሽ ቢጣሻም ደሃ

ሲሻው፡- ምነው ዶክተር! እንዲህ ጠመዱኝ?

ቶሌራ፡- ባንቺ ማሾፍ ቶሌራ ምንም አቲሆንም ደሞ እኔ አይደለቺም የጠመደቺሽ እንዳውም አንቺ ታመሽ ሣይሆን የሰው ሣንቲም ሊትለቅሚ ነው የሚትመጪ

ሰጠኝ፡- እባካችሁ ጮበዝ እዚህ ያለን ሁሉ ስራ ጥለን የመጣን ነን አንድ በሉንና እንሂድ!

ህመምተኛ፡- ኡሁ...አሁ...ምን ያክሙናል ሰብስበውን እንደትንግርት ያዩናል እንጂ ኡሁ..... ሰው እንደቲያትር ተቆጥሮ የሚታይበት ሃገር ላይ ተቀምጠን ምን መዳን አሁ.....አሁ.....ብቻ አምላክ ይይላችሁ አሁ.....ሳላችንን እንደሙዚቃ ልመናአችንን አሁ...አሁ...እንደሰማይ ቤት መዝሙር ነው መሰል የሚያዩት

ቶሌራ፡- /ካርዱን እየገለበጠ/ ሰጠኝ መርቆ /ይገባሉ/

/አቶ ሰጠኝና ዶክተር/

ዶክተር፡- እሺ አባት እንኳን ደህና መጡ ስምዎትን ይንገሩኝ

ሰጠኝ፡- መልካም ስሜ ሰጠኝ መርቆ ጉዳቴን አውቆ

ዶክተር፡- ግጥም ነው?

ሰጠኝ፡- ኧረ ግጥም አይደለም ስም ነው፡፡ ለመሆኑ ግጥም ብሎ ስም አለ እንዴ?

ዶክተር፡- ሰጠኝ መርቆ ብለ ስም አለ?

ሰጠኝ፡- ታዲያ ስም እንጂ ሌላ ምን መሰለህ/በቁጣ/?

ዶክተር፡- ኦ ኤክስኪውዝሚ አባት ያስቆጣዎታል ብዬ አይደለም ስለገረመኝ ነው፡፡

ሰጠኝ፡- ምንም እስኩዝሚ አያስፈልግም ደሞ ስሜ የሚገርምም ስም አይደለም ስሜ የስሞች ሁሉ ቁንጮ ነው፡፡ ምን ይወጣለታል እንደ እናንተ ያዘው፣ አጠጋጋው የሚል ዓይነት የሰይጣን እጁ ስራ ስላልገባበት ነው እስቲ ምን ይወጣለታል ይሄ ስም ሰጠኝ መርቆ ጉዳቴን አውቆ በዚህ ዘመን እንዲህ ያለ ስም አታገኝም፡፡

ዶክተር፡- /እየሳቀ/ ኦ! አባት ይቅርታ በጣም አስቂኝ ሰው ኖት እኔስ መጀመሪያ የሚቀልዱ መስሎኝ ነበር

ሰጠኝ፡- የታመመ ይቀልዳል ልጄ! ልታከም እንጂ ልቀልድ አልመጣሁ

ዶክተር፡- እሺ ተቀብያለሁ አባት እድሜዎን ይንገሩኝ

ሰጠኝ፡- በጣም ጥሩ እድሜዬ.... እድሜዬ! የጣታቸውን አንጓ እየነካኩ/ ዘጠኝ ዓመቴ

ዶክተር፡- ዘጠና ማለትዎ ነው?

ሰጠኝ፡- ኧረ ይሄ ሰው ጤናም አይደለህ? ከየት አምጥተህ ከመርክብኝ ዘጠኝ አመት ስልህ አትሠማም

ዶክተር፡- እባክዎትን አይቀልዱ አባት ስራ እኮ ነው የያዝነው?

ሰጠኝ፡- አልቀለድኩም ጎበዝ እድሜዬን ጠየከኝ በትክክል ነገርኩህ ምን አልባት ቋንቋዬ አልዘልቅ ብሎህ ከሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነህ ስትቆጥረው ዘጠኝ ትለዋለህ ፈረንጆች ጋር ደግሞ ናይን፡፡

ዶክተር፡- እንዴ ኧረ እባክዎትን ሌላ ሀመምተኛም አለ ተራ የሚጠብቅ ቀልዱን ትተው ትክክለኛ እድሜዎን ይንገሩኝ ካለበለዚያ ልረዳዎት አልችልም፡፡

ሰጠኝ፡- እንዴት ዶክተር ካለ እድሜዬ እድሜ ልነገርህ በኢዝም በወዝም አድርገው ዘጠኝ ነው ዘጠኝ ነው፡፡

ዶክተር፡- እንዴ ምንድን ነው ጉዱ ልንግባባ ያልቻልንበት በመካከላችን የቋንቋ ችግር አለ እንዴ ተርጓሚ ያስፈልግ ይሆን፡፡

ሰጠኝ፡- ቱርጁማን ማለትህ ነው? እኔ እራሴ ያኔ በክፉ ቀን ሃገር ፈተና ውስጥ ወድቃ እኔ በቱርጅማንነት እየሰራሁ ጐን ለጐን በሚስጢር የአርበኝነቱን ስራ አጣጡፈው ነበር ምን ያረጋል ዛሬ የጊዜው እርዝመት ሳያሰረሳኝ ይቀራል ብለህ ነው፡፡ ቢሆንም በኔና ባንተ በኩል ለመግባባት የሚያስችግር የቋንቋ ችግር ያለ አይመስለኝም፡፡

ዶክተር፡- ታዲያ በጣሊያን ጊዜ ነበሩ

ሰጠኝ፡ ኧረ የለሁም ልጄ

ዶክተር፡- /በንዴት ጦፎ/ ምን አይነት እዳ መግባት ነው እባክዎ ለስራ ይተባበሩኝ

ሰጠኝ፡- ነገርኩህ እድሜዬ ዘጠኝ ነው ዘጠኝ በቃ

ዶክተር፡- እንዴት?

ሰጠኝ፡- የኖርኩበት እድሜዬን አይደል የምትጠይቀኝ?

ዶክተር፡- አዎ

ሰጠኝ፡- እኮ ዘጠኝ አልኩህ

ዶክተር፡- ዘጠኝ አመት

ሰጠኝ፡- አዎ ዳክተርዬ

ዶክተር፡- ሊገባኝ አይችልም ይኼ ሁሉ ሽበት ግንባርዎት ላይ የተጋደመው መስመር እድሜ ጥሎት ያለፈ አሻራ ካልሆነ ታዲያ ምንድን ነው?

ሰጠኝ፡- ቁጣ....ቁጣ ነው ዓለም የጫነችብኝ የጥቃት ዳውላ

ዶክተር፡- /ከተቀመጠበት ተነስቶ/ እባካችሁ እኝህን ሰውዬ መላ በሉኝ

ነርስ፡- /ከወደ ውስጥ ትወጣና/ ምንድን ነው ዶክተር?

ዶክተር፡- ከእኚህ ሰውዬ ጋር መግባባት አልቻልኩም እድሜያቸውን ሊነግሩኝ ፈቃደኛ አይደሉም

ነርስ፡- /ቆጣ ብላ/ አባት ለሥራ ይተባበሩን እንጂ ሌላኮ ተራ የሚጠብቅ በሽተኛ አለ ስንት አመትዎ ነው?

ሰጠኝ፡- ዘጠኝ አመቴ ነው ልጄ

ነርስ፡- /ከት ብላ ትስቅና/ ዘጠኝ አመቴ ነው ገና አንድ ፍሬ ልጅ ነሃ ማሙሽዬ

ሰጠኝ፡- ተባረኪ ልክ ነሽ ልጄ ገና እምቦቀቅላ ነኝ ኑሮን ሀ ብዬ የጀመርኩ ጨቅላ

ነርስ፡- /እየሳቀች/ ዶክተርዬ ጊዜው እኮ ተገልብጣል ወጣቱ እንደ አዛውንት አንገቱን ሲደፋ አዛውንቱ ደግሞ እንደወጣት ከህይወት ጋር አዲስ ድሪያ ይዛል፡፡ ይህ ደግሞ እድሜ ከጫነበት የተፈጥሮ ክንድ እንደማምለጫ መሆኑ ነው እና ሰው እንደብሩ እድሜው አርቆ መቅበር ጀምሯል ስለዚህ ምን አሟገተህ ዝም ብለህ በአስር አባዝተህ አታስቀምጥላቸውም፡፡

ሰጠኝ፡- በአስር አባዝተህ ማለት

ነርስ፡- ዘጠና ነዋ!

ሰጠኝ፡- ዘጠና ጉድ ይውረርሽ ጠመንጃ ምላስ

ነርስ፡- ኡ ሽማግሌው ምን ነካቸው ጌታ ይገስፅዎት ከወጣቱ ይልቅ በየመንገዱ የናንተ ለከፋ ነው ያስቸገረን ልባችሁ ከውስጥ አላረጅ እያላችሁ በየደረሳችሁበት ችግር ፈጣሪዎች ትሆናላችሁ «ልብና ሣር እያደር ይበቅላል» ነው ያሉት አበው በሉ ቅብጠቱ ለወግ ይቆይዎትና እዚህ ለስራ ይተባበሩን

ሰጠኝ፡- /በንዴት ጦፈው/ እንዴት አንቺ ትሰድቢኝ ወይኔ ሰጠኝ መርቆ/ ይቁነጠነጣሉ/ ዶክተር ይህችን ሰው ዞር አድርግልኝ እንዳውም በቃ ንዴቴን ለኩሣ በሽታዬን አቀጣጠላችሁ፡፡ /ቁና ቁና እየተነፈሱ/ ወይኔ ሰጠኝ ደም ብዛቴ ገነፈለ አናቴ ፈረሰ /ራሳቸውን ይስታሉ ደጋግፈው ያስተኛቸዋል/

ዶክተር፡- /ወደ ውስጥ እየገባ/ ሲስተር እባክሽ እርጂአቸው

ሲስተር፡- /እጇን ጭንቅላታቸው ላይ ጭና/ ኦ! ምን አይነት መንፈስ ነው በጌታ ስም! እሳቸው ላይ ያደርክ መንፈስ በየሱስ ስም ይገሂለሁ ወጥተህ ወደ ጥልቁ ውረድ በላያቸው ላይ ሠፍረህ ቁጣ ሆነህ የምትነድ መዐት ሆነህ የምትወርድ በጌታ የሱስ ስም በመንፈስ ቅዱስ እሣት አስራሃለሁ/ ወደ ጆሮአቸው ተጠግታ/ በጌታ ስም..... በየሱስ ስም..... ውጣ

ሰጠኝ፡- /ጆሮአቸውን ይዘው/ ወይኔ ጆሮዬ ተበሳ

ነርስ፡- አዎ መብረቅ ሆነህ አይናቸው ላይ የምትባርቅ ነጐድጓድ ሆነህ በላያቸው ላይ የምታንጐዳጉድ መንፈስ በየሱስ ስም ይገፍሀለሁ ውጣ፡፡ ወደ ወንዝ የምትነዳቸው፣ ወደ ውሃ የምታወርዳቸው በጌታ አሠራር ወደ ጥልቁ ውረድ

ሰጠኝ፡- /እያቅሰቱ ይነሣሉ/ እ.....እ.....እ መዐት ይውረድብሽ /ይነሣሉ/

ነርስ፡- በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በኃይል ተናገረ እርኩስ መንፈስ የያዘውም ተኝቶ ተንፈራፈረ/ታያቸዋለች/

ሰጠኝ፡- ፍርፍር በይ ፍርፍር ያርግሽ/ይጠንታል/

ነርስ፡- /እየሸሸች/ ኢየሱስም እንዳሰቸገረ ባየ ጊዜ ልቀቁት ብሎ በኃይል ዕርኩስ መንፈሱን ገሰፀው፡፡ /ወደ ኃላዋ በፍርሃት እየሄደች/ እርኩስ መንፈሱም በኃይል ከሰዎቹ ይወጣ ነበር

ሰጠኝ፡- አንቺ ደፋር የሰውን ማንነት ሳታጠኚ በትህምክት የእግዚአብሔርን ሃይል ልታወጪ ያንቺን ህይወት ሣትመረምሪ በዘልማድ የምትንገዢ የመንፈስ ድሃ/ያንቋታል/

ነርስ፡- ይልቀቁኝ አንተ በሰው ተመስለህ የጌታን አሰራር ልትቃወም የመጣህ የአጋንንት ደም ፍላት ሆነህ የምትፈስ፤ቁጣ ሆነህ የምትነግስ.....

ሰጠኝ፡- ሞት ይንገስብሽ እኔ የስላሴ ባሪያ እኔ ነኝ የአጋንት ፈረስ አንቺ/ መንጭቃቸው በጠረጴዛ ዙሪያ ሲባረሩ ዶክተሩ ይገባል

ዶክተር፡- /ደንግጦ/ ምንድ ነው ምን ችግር ተፈጠረ

ሰጠኝ፡- /በቁጣ/ ምን ያልተፈጠረ አለ ዶክተር በንዴት ጦፎ ደም ፍላቴ ተነስቶ ነፍስዬን ብስት እርኩስ መንፈስ እንዳደረበት ሰው ጆሮዬ ላይ ስትደነፋ ጭንቀቴን አባብሳ ከሞት አፋፍ ጣለችኝ ለመሆኑ ዶክተር ሆስፒታላችሁ የእርኩስ መንፈስ ህክምና በድብቅ ስሜታዊነት በሚያጠቃቸው አንዳንድ ባለሙያዎቻችሁ በኩል እንዲሰጥ ፈቃድ ሰጥታችሁአል እንዴ? ይኼኮ የእምነትን ነፃነት የሚጋፋ የአንድ ግለሰብን የግል ስብዕና የሚነካ ጉዳይ እኮ ነው፡፡

ዶክተር፡- እሺ አባት አሁን ነገሩን ትተው ይቀመጡ

ሰጠኝ፡- ቆይ እንጂ ሰይጣኑ በማን ላይ እንዳለ ይለይ እንጂ እኔ የስላሴ ባሪያ የድንግል ማርያም የቃል ኪዳን ልጅ የሰይጣን ፈረስ ተብዬ የምቀር

አይደለሁም የስላሴ ልጅነቴን በማተቤ፣ የእናቱን ፍቅር በልቤ አንግቤ የምጋዝ የእምነት አርበኛ ነኝ። እሳ ግን በአፏ ከመለፍለፍ በቀር ለእምነቷ ምን የሚታይ ማስረጃ አላት

ዶክተር፡- ይገባኛል አባቴ ይተው በቃ! ወደነርሳ እያየ/ እባክሽ ሲስተር ስራና እምነትን ለይተን እንወቅ ህመምተኞቼ ተገቢውን ህክምና እንዲያገኙ እፈልጋለሁ አንቺ ግን የህክምና እርዳታሽን ለሚፈልጉ ህመምተኞች የእምነት ዶክተሪሽን ዘርግተሽ የታመመ መንፈሳቸውን ታሽበሪዋለሽ። ለሁሉም ቦታ አለው። ሰይጣን በመቅደስ አይኖርም ሆስፒታል የእምነት ማራመጃ ካምኘ አይደለም። ህመምተኞቼ ለህመማቸው ቀጥተኛ የህክምና እርዳታ የሚያገኙበት ቦታ እንጂ ያንቺን እምነት የምታንፀባርቂበት አይደለም በዚህ ነገር ብዙ ጊዜ ባንጋጭ ይሻላል። ከእንግዲህ በሽተኞቼን ከተገቢው የህክምና እርዳታ ውጪ የጎበጠ ጫንቃቸው ላይ ያንቺን እምነት እንድትጭኝባው እንደማልፈልግ ነው የምነግርሽ።

ሰጠኘ፡- /በደስታ/ ተባረክ የኔ ልጅ ይሄ ሆስቲታል እንጂ ቸርች አይደለም በላት

ዶክተር፡- እና ሲስተር ህመምተኞቼ የሥጋ ብቻ ሣይሆን የመንፈስም እረፍት እንዲያገኙ እንጂ በሙያ ሥም በሙያ ሽፋን ከሚራመድ ስውር የእምነት መረብ ትብታብ የማዳን ግልፅና የማያወላውል የሙያ ግዴታና ሃላፊነት ስላለብኝ ከእንግዲህ ይህ ሲደገም እንዳላይ አሁን ለጊዜው እኔና በሽተኛዬን ብቻችንን ብትተይን /ትወጣለች/

ሰጠኝ፡- ተባረክ.....ተባረክ..... የኔ ልጅ ጉድ እኮ ነው አንዳንዴ እኮ ዶክተር እነሱ ባሉበት ሆስፒታልና ቸርች የሚሉትን ነገር መለየት እስኪሳንህ ድረስ ብብትህ ውስጥ ቴርሞሜትር ከተው ጆሮህ ውስጥ ደግሞ ክህደታቸውን ይጨምሩብሃል። አንተ ታመህ መድሃኒት ልትወስድ ኪኒን ልትቀበል ስትመጣ «ጌታን ተቀበል» ይሉሃል። ይህን ታዲያ ምን ትለዋለህ የሙያና የሃይማኖት መድረክ ተለይቶ የማይታወቅበት ቦታ ነው እንዴ ሆስፒታል ኧረ አንድ በሉ!!

ዶክተር፡- ችግር እንዳለ ይገባናል። አባት ከግብታዊነት ይልቅ ስሜታዊነት እያጠቃን በቦታው መድረግ ያለበትን ያለቦታው በማድረግ አገልግሎታችንን የምናረክስ ብዙዎች በጥቅሉ ግን ጥቂቶች በስሜታዊነት ግልቢያ ሳናውቀው እያጠፋን መሆንኑ አውቀን እየተረዳን ነው ያለነው። እና አባት ለተፈፀመው ስህተት በሙያዬ ስም ከባድ ይቅርታ እጠይቃለሁ። ስህተቱ የተፈፀመው የግል ክትትሌን ትጠብቅ የነበረች በሽታኛዬ በድንገት በመታመሟ ልጉበኛት ሄጄ ነው። አዝናለሁ።

ሰጠኝ፡- መቼ ይሄ ብቻ ዶክተር ያንተ እምነትና ፍላጐት ከጉዳይ ሣይጥፉ እነሱ ያመኑትን ካልተቀበልክ ክብረስብዕናህን በሚጣረር መልኩ መቆሚያ መቀመጫ እስክታጣ ድረስ የሃይማኖትህን አቅጣጫና የዕምነትህን ደረጃህን ሳይለኩ እነሱ ካመኑበት በየፌርማታው በየመናፈሻው አፋቸውን ሲከፍቱብህ እምነታቸውን ሲተፉብህ ከፊሉ ደግሞ የተከበረ ደጅህን አንኳኩተው አንተም ባትኖር እንደባለጌ ጥሰው ገብተው ልጆችህን ሣይቀር ካንተ ፈቃድ ውጪ በጨቅላ አይምሯቸው ላይ ክህደታቸውን ይዘሩባቸዋል። ምን ይኼ ብቻ አሁንም ከፍለህ በምትሄድበት አውቶቢስ ፣ታክሲ ሳይቀር ማንም እየተነሣ ይጮህብሃል። ከዚህ የባሰው ደግሞ በምትጠቀምበት ፖስታ አድሪሻ የሌለው ቴምብር ያልተለጠፈበት

ማህተም ያላረፈበት የክህደት ትምህርታቸው ይደርስሃል በገዛ ፓስታችን በምንከፍልበት ሣጥን ካለፍላጐታችን ይላክልናል።

ታዲያ ይሄ የመብት ያለህ የመንግስት ያለህ አያሠኝም ትላለህ። ዶክተር ታዲያ የእናንተ ሆስፒታል የዚሁ መሰሉ በሽታ ሰለባ ሆኗል። አንዳንድ ነርሶቻችሁ በየአጋጣሚው እንደምናየው የሙያ ቃል ኪዳናቸውንና ግዴታቸውን ረስተው ቦታውን የገዛ ማንነታቸው ማራመጃ አድርገውታል። ይህ በዝምታ ሊታይ የማይችል ትልቅ የመብት ጥያቄ ነው።

ዶክተር፡- ልክ ኖት አባት ካለቦታው የሚሆን ነገር ሁሉ አግባብነት የለውም እሺ ለጊዜው ይብቃን አሁን ዕድሜዎትን በትክክል ይንገሩኝና ተገቢውን የህክምና እርዳታ ያገኛሉ እድሜዎ ሊታዘዝልዎት የሚችለውን የመድሃኒት ዓይነትና መጠን ስለሚወስነው በትክክል ቀና ትብብርዎ ያስፈልገኛል። ለመረዳት ከፈለጉ ማለቴ ነው በሉ እድሜዎን ይንገርኝ።

ሰጠኝ፡- ቅድም ጨርሰን ነግሬህ ዘጠኝ ዓመቴ ነው አልኩህ እኮ!

ዶክተር፡- ምን ዓይነት ዕዳ መግባት ነው ሰውዬ መረዳት አይፈልጉም እንዴ?

ሰጠኝ፡- በደንብ እንጂ መረዳትማ እፈልጋለሁ

ዶክተር፡- ታዲያ ዕድሜዎን ለምን ይደብቃሉ?

ሰጠኝ፡- እኔ አይደለሁም ዶክተር ዓለምና ሃጢያት ናቸው። ተባብረው እድሜዬን የነጠቁኝ ዓለም የሰጠኝን እድሜ በመርገሟ ወስዳ የበረከት ደሃ አደረገችኝ ስለዚህ ከኖርኩበት ይልቅ ያልኖርኩበት በልጦ ሳልወለድ የመከንኩ ሳልፈጠር የጨነገፈኩ የህይወት ጭንጋፍ ሽል ሆኜ እፍገመገማለሁ።

ዶክተር፡- አባት እኔ ሥጋዎትን እንጂ መንፈሣዊ ህይወቶን የማከም አይደለሁም ስለዚህ የዕደሜዎት ሚስጥርነት በህክምናው ዓለም ቦታ የለውም?

ሰጠኝ፡- ታዲያ ዕድሜ የገደለውን ሃጢያት የማረከውን ሥጋ ማከም ካልቻላችሁ የህክምናችሁ ሁልተናነት ምኑ ላይ ነው በሽታኮ የሃጢያት መገለጫ ነው?

ዶክተር፡- የህክምና ሙያዬ ይህን ዓይነቱን ስልጠና አላካተተም አባት

ሰጠኝ፡- አይ አንተ መንፈስህ የሞተ ሥጋህ በመንፈስህ ላይ ሰልጥኖ እውቀትህ ይህን የቀበረብህ ግማሽ ሃኪም ነህ ቅድም ስትናገር ስሰማህ ሲስተሯን ስትገስፅ ህመምተኞቼ ሥጋና መንፈስን ያስተባበረ ህክምና እንዲያገኙ እፈልጋለሁ ብለሃል ታዲያ የታለ የመንፈስ ህክምናህ

ዶክተር፡- /ተነስቶ/ አባት አካሄዶት ገብቶኛል አሁን ግን ሌላውን ትተው የዕድሜዎን ሚስጥር ለማወቅ ስለጓጓሁ ይንገሩኝ

ሰጠኝ፡- በጣም ጥሩ ጉዳዩ እንዲህ ነው ዓለም ከሞላ በረከቷ ሰጥታ የህይወት ፍሬ ከብብቷ ደብቃ ተፈጥሮን ገልባ ፈጣሪዋን እንዳላውቅ ብሩህ ህሊናዬን

ቆልፋ ዘመኔን እንደ እምቧይ ካብ የገለባ ክምር አደረገችው። ከዕውቀት ማዕዲ ስቆርስ ከሃብት በረከቷ ስሳተፍ ዘመኔን በአረመኔ የዕውቀትን ባለቤት ሣላውቅ ገፋሁ።

ያም ዘመን ከህይወቴ የተሰረቀ እድሜ በመሆኑ ኖርኩት ብዬ ላልቆጥረው ለራሴ ምዬ በንስሀ ታጥቤ በትህትና የተመለስኩበትን አምላኬን ያወኩበትን ወርቅ ጊዜዬን ብቻ ከእድሜዬ ተርታ አሠለፍኩት፤ እነዚህም ዘጠኝ ውብ ዓመታት ናቸው።

ዶክተር፡- በቃ ይኸው ነው የዕድሜዎ ሚስጥር አቤት!! ህይወት ከባለቤቷ ተለይታ እንደማየት በዓለም ላይ ምን ዘግናኝ ትርዒት አለ? ሰው ከራሱ፣ሰው ከሰው ጋር፣ ሰው ከኑሮው፣ ሰው ከአእምሮው ፣ ሰው ከእድሜው ሲጋጭ እነዚህ ሁሉ የህይወት ግጭቶች ያለፈ ህይወቱን ቀለም የሚያደበዝዙ የህይወት መጋዞች የእብደት ዋዜማ ናቸው ሰው ራሱን ከመካድ የበለጠ ከምድር ምን አለ? እና ----------

ሰጠኝ፡-እንዲያ ነው ልጄ አለማወቅ እንጂ እኛ ሰዎች ስንባል ከአምላክ በስተቀር በምድር ላይ ምን ተስፋ አለን። ከሰማይ ተዘርተን በምድር ላይ በቅለን ተመልሰን ወደ ሰማይ እንሰበሰባለን እዚህ መረዳት ላይ እሰክንደርስ ድረስ ግን ሁላችንም በየፊናችን የማናሸንፍበትን ከንቱ ሩጫ በምድር እንሮጣለን። እናም ዶክተርዬ ያን ሁሉ ከንቱ ያለፈ ያልኖርኩበትን ዘመን ምን ብዬ ልንገርህ በትክክል ከስላሴ በጥምቀት የተወለድኩበትን እድሜ ብቻ ነው በየደረስኩበት ከእድሜዬ መዝገብ ከትቼ የምዘክረው።

ዶክተር፡- ግሩም ነው አቶ አባት እኔ ዘጠኝ ዓመቴ ነው ሲሉ ጭንቅላትዎትን እስከመጠራጠር ደርሼ ነበር፤ ነገር ግን የዕውቀቴ ደረጃ የሰዎችን መንፈሳዊና ስነ ልቦናዊ አካሄድ ማገናዘብ የማይችል መሆኑን ተረዳሁ በሉ እሺ አሁንስ ትክክለኛ የኖሩበትንም አልኖርኩበትም ብለው የሚያምኑትን እድሜዎን ሊነግሩኝ ፈቃደኛ ኖት?

ሰጠኝ፡- አዬ ልጄ ያን ክፉ ዘመን እድሜዬን የቀማኝን ጉግማንግል በኃጢአት የኖርኩበትን የዕድሜዬን ክምር አላውቀውም። ለዛ ላለፈው እድሜዬ ደግሞ ከሁሉ በበለጠ ሰማያዊ ሃኪም የታዘዘ ድንቅ መድሃኒት ወስጄ ዘላቂ ፈውስ አግኝቼበታለሁ

ዶክተር፡- /በአግራሞት/ ምን የሚሉት መድኃኒት?

ሰጠኝ፡- ንስሐ፣ንስሐ የሚሉት የህይወት ኪኒና መድኃኒቱ እናንተ ጋር የለም። ይህ ዓለም ሁሉ ሊታከምበት ብሎም ሊፈወስበት የተሰጠ መርፌ ሳትወጋ ኪኒና ሳትቅም ኃጢአትህን በማመንና በመግለፅ የሚዳንበት ድንቅ መፍትሔ። አዎ ይህ ነው የሚያስፈልገን ዶክተርዬ አየኸው የእናንተን ህክምና ጉድለት

ዶክተር፡- ግሩም ነው ግልጽና ጥልቅ የዓላማ ጽናት አለዎት ያለፉትን አባቶች የእምነት ጽናት በእርሶ ውስጥ በማየቴ በአግራሞት ተውጫለሁ በሉ

ለማንኛውም አሁን ወደመስማማቱ ስለደረስን ይህችን ቴርሞ ሜትር በብብትዎ ይያዟት

ሰጠኝ፡- ዶክተር ክህደታችሁን በጆሮዬ አትጨምሩብኝም?

ዶክተር፡- በፍፁም ንፁህ የህክምና እርዳታ ያገኛሉ::

ሰጠኝ፡- እሺ የኔ ልጅ አንተም የተነጋገርንበትን በልብህ ያዛት ሰማያዊ ሃኪም ለአንተም ያስፈልግሃል:: ላንተም ብቻ አይደለም ለዓለሙ ሁሉ እንጂ ያ ንስሐ የሚሉትን ኪኒና የምንቅምበት ጊዜ አሁን ነው እንደ እኔ የኖርንበት እድሜ ካልኖርንበት ለይተን የተረፈውን ወርቅ ጊዜ በንስሐ ታጥበን ቀሪውን ዘመናችንን ለባለቤቱ እንስጥና እንባረክ:: ዶክተር

ሰጠኝ፡- አቤት አባት

ሰጠኝ፡- በፈገግታ እያቀረቡት /በል እኔ ያንተን ቴርሞ ሜትር በብብቴ እንደያዝኩ ከኪሣቸው መስቀል እያወጠ/ በል እንካ አንተ ደግሞ ይህን ቴርሞ ሃይማኖት ተቀበለኝ/ይዘረጉለታል/

/ነርሳ ለመልዕክት ስትገባ መስቀል ሲሰጡት ስታይ ገርሟት ቆማ ታያለች/ ይህ ፍፁም ሃይማኖት የእግዚአብሔር ፍቅር የተገለፀበት ታላቅ የፍቅር ዋጋ የተከፈለበት እንደ እናንተ ፈሣሽ ሜርኩሪ ሣይሆን ውለታው በአንደበት ሊገለጥ የማይችል ህያው ፍቅር ምትክ በማይገኝለት ደም የታተመና የተሞላ የሰው ልጅ እዳ የተወገደበት ቅዱስ መስቀል ነው እየው የአምላክን ቸርነት ይህ ብቻ አይደለም ከዚህ ውለታ ባሻገር በዙሪያችን እንደደመና በከበቡን ቅዱሣን አማላጅነት የመዳናችንን መንገድ ሰርቶ የሄደበት ታላቅ የሚስጥር አምድ ነው::

ዶክተር፡- አመስግናለሁ አባት/እየተቀበላቸው/ አባት ይህን ታላቅ ቴርሞ ሃይማኖት ማንም ሊሰጠኝ ያልቻለውን ልዩ ፍቅር ያየሁበት መስታወት ቅዱስ መስቀል ተቀበልኩት/ ወደ ሲስተሯ እያዩ/ ሲተር አንቺስ ይህን ቴርሞ ሃይማኖት ይዘሻል?

ሲስተር፡- /እየተቆናጠረች/ ድኛለሁ አያስፈልገኝም

ዶክተር፡- የለም አልዳንሽም ሲስተር ስለዚህ መዳን ብዙ ካንቺ ብሰማም እንደዛሬ እንደኚህ አባት በሚታይ በሚጨበጥ እውነተኛ ሚስጢር ልቤን ፈልቅቆ ፍቅሩን በውስጤ ያስቀመጠ ማንንም አላገኘሁም::

ሲስተር፡- ኦ ሃሌ ሉያ ክንዱ ከፍ ከፍ አለ

ሰጠኝ፡- መንግስተ ሰማያት በስሜት መንኩራኩር ተተኩሰው የሚገቡባት ኘላኔት አይደለችም በተመስጦ በሚከወን አምልኮ፣ ራስን በማያስታብይ ክርስቶሳዊ ፍቅር፣በጾምና ጸሎት የሚያገኟት ውብ ሰማያዊ አጎድ እንጂ፤ ዶክተር ዘመኑ ለመናገር የፈጠኑ ለመስማት የዘገዩ ጆሮዎቻችን ያንጠለጠሉ በስሜት የሰከሩ የዐመጸ ድውዮች የበዙበት ነውና የእጃችንን ወርቅ ነጥቀው ጠጠራቸውን እንዳያሳቅፉን እንጠንቀቅ::

ጽኑኡ በተወሀዶ እምነት የሚለው መዝሙር ይለቀቃል/ ዶክተርና ሰጠኝ በመዘምራን ተከበው በምልክት እየተግባቡ ህክምናውን ሲከውኑ ይታያል።/ በኃላም አብረው ይዘምራሉ።።

መጋረጃ ይዘጋል

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
ወለወላዲቱ ድንግል
ወለመስቀሉ ክቡር

ከያሬድ በላይነህ አፈወርቅ
ለተ.ማ.ማ.ኪ.ጥ.ክ የተሰጠ
ሐምሌ 1991 ዓ.ም.

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን::

ባልንጀራዬ ማን ነው?

ትዕይንት ፭

መጋረጃው ሲገለጥ አንድ አባት መድረክ ላይ ይታያሉ::

ካህን:- የአመፃ ገንዘብ ሲያልቅ በዘላለም ቤቶች እንዲቀበሏችሁ በርሱ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ... መጋቢ የነበረው አንድ ባለጠጋ ሰው ነበረ... ሰዎችም ወደ ባለጠጋው ዘንድ ሔደው መጋቢውን ከሰሱት «ይህ ሰው ያለህን ይበትናል» ብለው ባለጠጋውም መጋብውን አስጠርቶ «ይህ የምሰማብህ ምንድን ነው ወደፊት ለእኔ መጋቢ ልትሆን አትችልምና የእስካሁኑን የመጋቢነትህን ሒሣብ አስረክበኝ» አለው:: ...መጋቢውም በልቡ «ጌታዬ መጋቢነቱን ከእኔ ሊወስድ ነውና ምን ላድርግ ለመቆፈር ኃይል የለኝም መለመንም እፈራለሁ... እና ከመጋቢነቱ ብሻር ሰዎች በቤታቸው በፍቅር እንዲቀበሉኝ የማደርገውን አውቃለሁ» በማለት የጌታውን ባለዕዳዎች እያንዳንዳቸውን ጠርቶ የፊተኛውን «ለጌታዬ ምን ያህል ዕዳ አለብህ?»አለው እርሱም «መቶ ማድጋ ዘይት» አለው መጋቢውም «በል ደብደቤህን እንኳ ፈጥነህም ሃምሳ ብለህ ፃፍ» አለው..... በመቀጠልም ሁለተኛውን ባለዕዳ ጠርቶ«ዕዳህ ምን ያህል ነው?» ቢለው «መቶ ስልቻ ስንዴ» በማለት መለሠ «በል ደብደቤህን እንኳ ፈጥነህም ሰማንያ ብለህ ፃፍ» አለው ..... ይህ ሁሉ ከሆነ በኃላ በመጨረሻ ግን ባለጠጋው ሰውዬ ያ ዓመፀኛ መጋቢ በልባምነት ያደረገውን ተመልክቶ አመሰገነው::...ይህ ጌታችን የተናገረው በሉቃስ ወንጌል ም. 16 ከቁ.1-9 የሚገኝ ምሣሌ ሲሆን ከዚህ ታሪክ አመፀኛ መጋቢ የተባለው የሰው ልጅ ነው.....እኔና እናንተ! በባለፀጋ የተመሠለው እግዚአብሔር ለሠው ልጆች የሠጠው ስጦታ ነው ይኸውም ከስጦታ የሚያስተውል አእምሮና እድሜ ነው::.....ታዲያ እኛ የተሰጠንን ፀጋ ልናካፍለውና ልንመፀውተው የሚገባው ባልንጀራችን ማነው?...ሁላችንም ራሣችንን ልንጠይቅ የሚገባን ታላቅ ጥያቄ...ባልንጀራችን ማነው?

ካህን:- መድረኩን ለቀው ሲሔዱ አቤል ከተመልካቹ መካከል ይነሣል::

አቤል:- የአመፃ ገንዘብ ሲያልቅ በዘላለም ቤቶች እንዲቀበሏችሁ በርሱ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ ነው ያሉት አባ?...ታዲያ ለኔ ባልንጀራዬ ማነው? ቹቹ፣ ሐብታሙ ኖ ሁለቱ ሊሆኑ አይችሉም ከተያየን እንኳ ስን ጊዜያችን ከ1ኛ ክፍል ጀምሮ አብሮኝ የተማረው ሄኖክስ? አይ እሱ ደግሞ ነጭናጫና ሆዳም ነበር:: ሲጠግብ ብቻ ነበር ትዝ የምለው::

እሱ ባልንጀራዬ ሊባል አይችልም! ከእርሱስ ታገል ይሻላል ግን ደግሞ ታገል ከመዝናናትና ከመደሰት በቀር ቤተክርስቲያን መሳለም፣ መጸምና ማስቀደስ አይወድም::... እንዴ ቆይ በቃ እኔ ባልንጀራ የለኝም ማለት ነው?...ወይ ጉድ ነው ወይንስ ባልንጀራ ማለት ራሱ አልገባኝም...ግን ግን ባልንጀራ ማለት ልክ እንደኔ ሁሌ ቤተክርስቲያን የሚመጣ ማለት ይሆን እንዴ?...አይ እሱማ ጓደኛ ሳይሆን ወንድም ነው የሚባለው...ዳሩ እርሱም የለኝም ለካ! (እያለ ሲጨነቅ አንድ ሰው ባጠገቡ ያልፋል)

አቤል፡- ቆይ ቆይ ይቅርታ ወንድሜ

መንገደኛ፡- አቤት ምነው?

አቤል፡- አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ ነበር

መንገደኛ፡- ገንዘብ ከሆነ የለኝም

አቤል፡- ኧረ አይደለም? አንድ ቀላል ለኔ ግን የከበደኝ ጥያቄ ነው... ምን መሠለህ ባልንጀራህ ማነው?

መንገደኛ፡- የማን?

አቤል፡- ያንተ ነዋ!

መንገደኛ፡- ባልንጀራ ምን ማለት ነው ደግሞ?

አቤል፡- ወይ ጉድ ጭራሽ አንተው ራስህ ጠያቂ ሆንከው?...ባንልጀራ-ጓደኛ ማለቴ ነው::

መንገደኛ፡- ኦ!ፍሬንድ አትለኝም ታዲያ!

አቤል፡- እሺ ይሆንልህ ፍሬንድህ ማንው?

መንገደኛ፡- ብዙ ናቸው ዳኒ፣ቢኒ፣ዮኒ፣ዘኪ፣ቴዲ፣ሣሚ፣

አቤል፡- በቃ.....በቃህ.....የህዝብ ቆጠራ አደረግከው ኮ!

መንገደኛ፡- ቆይ መች አስጨረስከኝ.....ራስህ አይደለህ እንዴ የጠየከኝ!

አቤል፡- አይ በቃኝ.....ሰማሁህ እኮ!

መንገደኛ፡-ባንተ ቤት ከባድ ጥያቄ ጠይቀህ ሞተሃል.....ምኑ ወፈፌ ነው ባካችሁ/ጥሎት ይሄዳል/

(አቤል አንድ ፀሎት ወደማያደርግ ሰው ይሄዳል-ሊጠይቅ!)

ፀሎተኛ፡- ምነው ሰውዬ ከፊቴ ዘወር ብትል.....ምፅዋት ፈልገህ ከሆነ እስክጨርስ ልትታገስ ይገባሃል.....ወይ ጉድ ጭራህ ሰይጣን ከፊቴ በሰው እየተመሠለ ተደንቅሮ ፀሎቴን ያስታጓጉለኝ!...ምነው ዘንድሮስ ፈተናዬ በዛ!....**(እያጉረመረመ አቤልን ገልምጦት ይሄዳል)**

አቤል፡-**(እየተገረመ)** አይ አቤል እስከ ዛሬ ባልንጀራህን ሣታውቅ ኖረህ አሁን ኖርኩ ትላለህን ሰዎች ስለባልንጀራ ብዙ ብዙ ብለዋል.....«ባልንጀራ የክፉ ቀን ደራሽ ነው፡፡ ባልንጀራ ያንተን እድገት ከራሱ አብልጦ ፈላጊ ነው፡፡ ባልንጀራ ለኔ ሳይሆን ላንተ ብሎ ከራሱ የበለጠ ስላንተ የሚያስብና የሚጨነቅ ነው»....ታዲያ የኔ ባልንጀራ ማነው? የቱስ ነው? **(እያለ ሲል...አንዲ ትመጣለች)**

አቤል፡- እህትዬ.....እቱ....እታለም!

እታለም፡- አቤት...እኔን ነው?

አቤል፡- አዎ እባክሽን አንድ ጥያቄ ልጠይቅሽ!

እታለም፡- **(እንደ መሸኮርመም እያለች)**.....እውነት ሀሠት ነው? ምርጫ?

አቤል፡- ኧረ ቀላል ደረቅ ጥያቄ ነው? ስላስቸገርኩሽ ግን ይቅርታ

እታለም፡- አይ ምንም አይደል.....ጠይቀኝ!

አቤል፡- «ጠይቀኝ?» ኧረ በቶሎ እንደርሱ አይባልም እቱ.....ግን ቆይ ወዴት እየሔድሽ ነው?

እታለም፡- ባልንጀራዬ ጋር

አቤል፡- እንዴ እኔም ልጠይቅሽ የነበረው ጥያቄ እኬ ይህን ነው

እታለም፡- ምን?

አቤል፡- ባለንጀራሽ የታለች? ማናት?

እታለም፡- ባልንጀራዬ መቃብር ነው ያለችው ሰናይት ትባላለች

አቤል፡- እንዴ መቃብር! መቃብር ጠባቂ ነች እንዴ?

እታለም፡- ሥነ-ሥርዓት እሺ

አቤል፡- ይቅርታ ማለቴ መቃብር ምን ታደርጋለች?

እታለም፡-(እያለቀሰች)... እባክህ ሆዴን አታባባው ባልንጀራዬ ካረፈች ዛሬ ስድስተኛ ወራ ነው፡፡

አቤል፡- ወይ ጉድ ይቅርታ የኔ እህት.....በጣም ይቅርታ ባለማወቅ ነው.....በቃ ትቼአለሁ **እያለቀሰች ትሄዳለች)**

የሊቀ መላእኩ ያለህ እስቲ ግራ ተጋብቼ ሰው ግራ ላጋባ... ሞታለች?.....ቆይ አንዴ ባልንጀራችን ከሞተ ሌላ ባልንጀራ ሊኖረን አይትልም ማለት ነው?.....ቆይ የኔስ ባልንጀራ ሞቷል ወይስ አለ?

(በነጋታው ረፋዱ ላይ አቤል ምላሽ ያላገኘለትን ጥያቄ ሲያብሰለስል አድሮ አርፍዶ ምላሽ ቢያጣለት ትላንት ያስተማሩትን ካህን ለመጠየቅ ወስኖ መጣ)

አቤል፡- እንደምን አደሩ አባቴ ይፍቱኝ(ጉልበትና መስቀል ይሳለማል)

ካህን፡- እንዴት አደርክ ልጄ! እግዚአብሔር ይፍታህ

አቤል፡- እንዳው አባቴ ይገርምዎታል ትላንት ያስተማሩት ነገር ከባድ ጭንቀት የማይመለስ ጥያቄ አሣድሮብኝ ውሎና አምሽቶ አረፈደ

ካህን፡- የምን ጭንቀት የኔ ልጅ እስቲ አረፈ በል.....ምንድን ነው ያልተመለሰልህ ጥያቄ...እንዳው ጥያቄህ በኔ በደካማው የሚቻል ባይሆንም እስቲ ንገረኝ ልጄ?

አቤል፡- ግድ የለም አባት መልስ ከአባቶች አይጠፋም እድሜም ጥበብም አስተምሯቸዋልና... ደግሞስ ምን ቢደክሙ ከኔ ከባዶወ ይሻላሉ

ካህን፡- ማለፊያ ትህትና የኔ ልጅ.. ቡሩክ ሁን! ግድየለም ምስጢርን የሚገልጽ እግዚአብሔር ጥበብን እንዲገልጽልን በፀሎት እንለምነዋልን፡፡

አቤል፡- እውነትዎን ነው አባ! ፀልዩልኝ ብሎ ለማለትም የፀሎት ጠያቂው ቅድስናና ንጽህና ወሣኝ ነወ ለእንደኔ ያለው መች ይሆናል፡፡

ካህን፡- ተባረክ ልጄ ዛሬ ዛሬ አላፊ አግዳሚው ፀልዩልኝ ብሎ ማለትን በእንፀልይልህ ተክቶ የትህትናን ህንፃ እየናደ የትዕቢተን ተራራ እየመሠረተ ይገኛል፡፡ ከእንዲህ ያለ ግብዝነት እመብርሃን ትሰውረን!

አቤል፡- አሜን...አሜን

ካህን፡- ምን ነበር ያስጨነቀህ ልጄ?

አቤል፡- ምን መሠሎት አባ.... ትላንት በሉቃስ ወንጌል ም. 16 ላይ ያለወን ታሪክ ስሰማና የአመፃ ገንዘብ ሲያልቅ በዘላለም ቤቶች እንዲቀበላችሁ በርሱ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ የሚለውን ቃል ልብ ስል የኔ ባልንጀራ ማነው? ወዳጄ ሊሆን የሚገባው ማነው? ብይ ራሴን መጠየቅ ጀመርኩ ግን ምላሽ አጣሁለት!

ካህን፡- መልካም በወንጌሉ ላይ እነደተፃፈ /ተፋቀሩ በበይናቲክሙ/ እርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ/ ይላል እንዲሁም በሌላ ቦታ ላይ «አፍቅር ቢፅስ» ወንድምህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ ይላል፡፡ ባለእንጀራህን፣ ወዳጅህን፣ ልትለው ትችላለህ አንተ ግን ጥያቄህ ባልንጀራህን እንዴት መውደድ እንዳለበህ ሣይሆን- ከቶውንስ ባልንጀራዬ ማነው የሚለው ነው?

አቤል፡- አዎን አባቴ ባልንጀራዬ ማነው? ወይም ምን ዓይነት መሆን አለበት?

ካህን፡- ብዙ ጊዜ ሰዎች ባልጀራዬ ወይም ባልንጀሮቼ ብለው በተለይ የሚመርጧቸውና ጓደኛና ወዳጅ የሚያደርጓቸው በሀብት በኑሮ በዕውቀት እነርሱን የሚመስሏቸውን ነው?.....አንድ ምስኪን ደሃ ምን አብሯቸው ቢያድግ ምን አብረው ቢማሩ እንኳን የልብ ባልንጀራ ሊያደርጉት ቀርቶ

ከዚያ ምስኪን ጋር አብሮ መቆም እንኳን ክብራቸውን የሚቀንስባቸው ይመስላቸዋል! ስለዚህ ወዳጄ ብለው ውለታ የማያደርጉለት ውለታቸውን ሊመልሰ አቅም ላለው ሰው ነው። ሁሌም ማሰብ ያለብን ሁላችንም በመጨረሻ በእግዚአብሔር እንጠራለን። ታዲያ ምን ለብሰን? ምን ይዘን? ለማንስ የሰራነው የፅድቅ ሥራ የሆነ እግዚአብሔር ፊት የሚያቀርበን?...ይህን ፅድቅ ሰርቷል ብሎ የማመሰክርልንስ ማነው?...ልጄ እያንዳንዳችን ሶስት ባልንጀሮች አሉን!

አቤል፡- ኧረ ከዚያም በላይ 4,9,5 ያላቸውም አሉ...እኔ ግን ምንም የለኝም!

ካህን፡- አለህ ልጄ አለህ? ላንተም ለሁሉም ሰው ሶስት ባልንጀሮች አሉት የመጀመሪያው ከራሱ አብልጦ የሚወደው ነው፣ ሁለተኛውን እንደራሱ ይወደዋል፣ሶስተኛውን ግን ንቆ አጥቅቶ የሚወደው እያንዳንዱ ሰው ሶስት ባልንጀሮች አሉት።

አቤል፡- እኔ አሁን ሶስት ባልንጀሮች አሉኝ ማለት ነው? ደግሞስ ይህስ ይሁን ግን እኔ የማላውቃቸው የኔን ባልንጀሮች እርሶ እንዴት ሊያውቋቸው ቻሉ?

ካህን፡- ልብ ብለን ካስተዋልን ሁሉም ሰው ያውቃቸዋል!

አቤል፡- አልገባኝም አባ?.....ቆይ ለመሆኑ እኔ ወይም ሌላ ሰው ከራሱ አብልጦ የሚወደው ያሉት ባልንጀራው ማነው?

ካህን፡- ገንዘቡን...ብሩን!

አቤል፡- ብሩን? እንዴት?

ካህን፡- ሰው ራሱ በደሳሳ ጎጆ እየኖረ ብሩን ግን ባማረ ህንፃ በባንክ በማይሠበርና በማይሰረቅ ሣጥን ውስጥ ያስቀምጣል። ለርሱ ዋስትና ሣይኖረው ለንብረቱና ለገንዘቡ ዋስትና ያደርጋል። ገንዘቡን ከራሱና ከአምላኩ አስበልጦ ይወደዋል! ለገንዘቡ ወንድምና እህቱን አይደለም የገዛ አብራኩንም እስከመግደል ይደርሳል!....

አቤል፡- እንደራሣችን አድርገን የምንወደው ሁለተኛው ባልንጀራችንስ ማነው አባ?

ካህን፡- ቤተሰቦቻችንን ነው ልጄ? ምክንያቱም ለኛ የምንለው ነገር ሁሉ ለቤተሰቦቻችን እንዲሆን እንመኛለን.....ግን ለጠላቶቻችን አይደለም ለጎረቤቶቻችን እንኳን ያንን ለቤተሠቦቻችን የተመኘነውን ጥሩ ነገር አንመኝላቸውም

አቤል፡- ሁለቱን ባልንጀሮቼን ለየኃቸው አባ.....ሶስተኛውስ? ያ ንቀን አጥቅተን ደስ ሲለን የምንወደው ደስ ካላለን ረግጠነው የምናልፈው ባልንጀራችን ማነው?

ካህን፡- አቅመ ደካማው ያ ሃይለኛውን ዶፍ ዝናብ በተበጣጠሰ ላስቲክ ውስጥ የሚያሳልፈውና ያ ከቤተክርስቲያን ደጃፍ ወድቆ የተራበ ገላው የተጎሳቀለውን ያ ማየት የተሣነውን ፣ልንጠጋው ተፀይፈን በርቀት የምንመፀውተው ያልጣመንን እንዲሁም ሲተርፈን ብቻ የምንሰጠውን...ግን ምንም ብናደርግለት ውለታችንን ሊመልስ ምንም

የሌለውን.....ነገር ግን ይህ ባልንጀራችን እርሱ የመንግስተ ሰማያት መግቢያ! የዘላለም ህይወት መገኛ፣ የፅድቅ ሥራችን ምስክር ነው::...እና የአመፃ ገንዘባችን ሲያልቅ በዘላለም ቤቶች የሚቀበለን እርሱ እውነተኛ ባልንጀራችን ነውና ዛሬ ባለን ገንዘብ፣ ዕውቀትና ሀብት ለራሳችን ወዳጅ ልናደርገው ይገባናል::

ተፈፀመ

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!
ወለወላዲቱ ድንግል!
ወለመስቀሉ ክቡር!

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።።

የባቢሎን ጥርሶች

ትዕይንት ፩

መብራት ሲበራ

ተከስተ፡- አባባ ባለፈው ሌላ ቀን አጫውትሃለው ያሉኝን ያስታውሳሉ?

አባት፡- *መቼ?*

ተከስተ፡- ባለፈው ታሪኮን አጫውቱኝ ብሎት እስከ አሁን ብዙ አውቀሃል የቀረውን አንድ ቀን አጫውትሃለው አላሉኝም?

አባት፡- ምን ሊሠራልህ?

ተከስተ፡- በጣም ይጠቅመኛል ብዙ እማርበታለሁ

አባት፡- ያው እንግዲህ ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ፣አሁን ኮምጣጣ ወይን ላንተ ሊጠቅምህ? ወይን አውርድ ብለህ ከሾህ ብትጠጋ ከንቱ መድከም አይደል።። አሁን ከኔ ህይወት ምን ልትማር ነው መካን ታሪክህን አነብንብልኝ የምትለኝ

ተከስተ፡- ግድ የለም ምንም ይሁን ምን እድሜ ታሪክ ነው፤ ታሪክ ደግሞ አስተማሪ ነው ፍሬውም በቀጣዩ ትውልድ ይገለባል።። አሊያም ታላቁ መፅሐፍ ቅዱስ ላይ የተፃፈው ታሪክ ሁሉ ለምን ተፃፈልን

አባት፡- እሱማ ከአብሪተኞች እብሪት፣ ከከሃዲያን ክህደት እንድንርቅ ፣ ከትሁታን ትህትና ፣ ከቅዱሣን ቅድስና እንድንቀርብ የእምነታችን መሠረት ተደርጐ ተፃፈ።። ብቻ የእኔ ህይወት ብዙም የሚያስተምር አይደለም ለማለት ፈልጌ ነው።።

ተከስተ፡- እሱንም ቢሆን የአባት እድሜ ነው።። ጠጋ ብሎ ማየቱ አስፈላጊ መሠለኝ

አባት፡- ለዚህ ነው እድሚያችን አስጠግታችሁ ጥላችሁን የምትሸሹት

ተከስተ፡- አልገባኝም

አባት፡- እንዴት አይገባህም? በእድሜ ሁዳድ ከእኛ ጋር ፉክክር ጀምራችሁ ስትቀድሙን እያየን

ተከስተ፡- መች ቀደምናችሁ?

አባት፡- ቀደማችሁን እንጅ ንጋታችሁን እያየን፣ ቀናችሁን ውሏችሁን ሣናይ፣ ምሽታችሁን አየን እንደ ፀሃይ ወጥታችሁ እንደ ፀሃይ ሣትሞቁ እንደ ጀንበር ጠልቃችሁ ልጅነታችሁን ሳንሞቀው እንደበረዶ አቀዘቀዛችሁን ይኸው እኛ ቁጭ ብለን እናንተ ወደ መቃብር ስተፈጥኑ አየን ታዲያ ከዚህ በላይ መቅደም ምን አለ?

ተከስተ፡- አሁን ተረዳሁት

አባት፡- እስኪ እንዴት ተረዳኸው?

ተከስተ፡- ሥለ ኤች አይ ቪ መሠለኝ የተናገሩት

አባት፡- እና ምን ታሥባለህ?

ተከስተ፡- እንግዲህ አቅም በፈቀደ መጠንቀቅ ነው፡፡

አባት፡- አቅም በፈቀደ ደግሞ መሞት ነው፡፡

ተከስተ፡- ማለቴ መቼም ስጋ ለባሽ ነንና.....

አባት፡- ኤዲያ! ያንኑ ጥግ የሌለው ድካማችሁን አትተርክልኝ፡፡ ሰልስቱ ደቂቅ በእቶን እሳት ፊት የቆሙት ስጋ ለባሽ አልነበሩም? ነቡዩ ዳንኤል በአናብስት ፊት የቆመው ስጋ ለባሽ አልነበረም? እንግዲያውስ እናንተ እነማን ናችሁ በገዛ ስሜታችሁ ፊት በድፈረት መቆም አቅቷችሁ ስጋ መልበሳችሁን የሞታችሁ ምክንያት የምታደርጉት? በል አሁን ጥያቄህን እንዳላስረሳህ ምን ነበር ያልከኝ?

ተከስተ፡- ታሪኮትን አጫውቱኝ ነበር ያልኮት?

አባት፡- አሃ.....አሃ.....አስታወስከኝ /ፋታ/ ታዲያስ ስለእኔ የምታውቀው ምን አለ?

ተከስተ፡- ማለት እዚህ ቤት ከመጣሁ ጀምሮ ስመለከት በቤተክህነት ትምህርት የጠለቀ እውቀት አለዎት ከዚህ ሌላ ለኛ ለትምህርት የሚሆን ትህትና፣ ትዕግስትና ፅናት አለዎት ለምን ስልጣነ ክህነት አልተቀበሉም?

አባት፡- አንተ ልጅ ውዳሴ ለሰነፎች ብትሰጥ ልባቸውን ታደክማለህና ቆጠብ በል፡፡ አሁን እኔ ምን አውቃለሁና ነው ከአዋቂዎች ወንበር የምትሾመኝ ደግሞስ ስልጣነ ክህነት ሚዛኑ መች እውቀት ሆነ

ተከስተ፡- አባባ በእርግጥ ክርስትና የሚሞጋገሱባት መድረክ አንዳልሆነች አውቃለሁ፣ ቢሆንም ማነፃፀር አይሁንብኝና ለሌሎች ህይወት ያለዎት አሳቢነት ከአንድ አገልጋይ ቢበልጥ እንጅ አያንስም፤ ከምንም በላይ ደግሞ ስለሃይማኖትዎ ያለዎት ጥልቅ እውቀት ይገርመኛል፡፡

አባት፡- እስኪ ተወው ልጄ የእኔ ዕውቀት ሚዛኑ የእናንተ መዳን የእናንተ መለወጥ ነው አልያማ የጋን ውስጥ መብራት መሆኔም አይደል፡፡ ለራሡ ብቻ አብርቶ ለራሱ ብቻ ኖሮ ግን ብዙዎችን ይዞ የሚሞት የክርስቶስ

የቅዱሳን አባቶቻችን ተቃራኒ ነው። ምክንያቱም ክርስቶስ ለሠው ብሎ ተወለደ ለሠው ብሎ ተመላለሠ ለሠው ብሎ ሞተ እንደየአቀማችን እግዚአብሔር በፈቀደ ቅዱሳን አባቶቻችንን መምሠል አለብን። «እኔ ክርስቶስን እንደመሥል አናንተ ደግሞ እኔን ምሰሉ» ብሎ የለ ቅዱስ ጳውሎስ

ተከስተ፡- አረ እኔ እንጃ.....ግን

አባት፡- ተወው ይልቅ ጥያቄህነ ልመልስ አየህ ልጄ ስላጣነ ክህነት ከሠማይ እንጂ ከምድር አይደለም። ምንም ዕውቀት ቢኖርም ስለ አወቁ እንደ አንተ ድግሪና ድፕሎማ የማነጣጠቁት አይደለም ክህነት እውቀት ብቻ ሣይሆን ፈቃደ እግዚአበሔር ነው። ለማንኛውም ይህቺ እድሜዬ ብዙ አሣይታኛለች በልጅነቴ አመፀኛ ነበርኩ አባቴ ካፈራቸው አራት ፍሬዎች አንዱን ወደ ቆሎ ት/ቤት ይሠድና እኔንና ሁለት ወንድሞቼን ያስቀራል። ይሁንና ለበጐ የምለግም ለአመፅ የምበረታ ብሆንበት እኔንም ወደዚያው ይልከኛል። ምንም እንኳ ትምህርቱን ከእኩዮቼ ዘግይቼ ብጀምርም በጥቂት ጊዜ ውስጥ የበላዮቼን ሣይቀር በለጥካቸው በዚህም የተነሣ መምህሮቼና ባልንጀሮቼ በጉብዝናዬ አደነቁኝ በጣም ጐበዝኩ ከዕድሜዬ በላይ አወቅሁ ታዲያ ይህቺ አድናቆታቸው ቀድሞ ከአባቴ ቤት የመጣኋት አመፅ ታጐለብት ጀመር። በኋላ ከተማሪዎች ጋር በትንሽ በትልቁ መናቆር አመጣሁ። እኔም ይጣት ወደ ቆሎ ት/ቤት የገባሁት ዓመፀኝነት እሷም በተራዋ ይዛኝ ወጣች ከዚያም በኋላ ከሸፈተው ጋር እየሸፈትኩ ከዘመተው ጋር እየዘመትኩ ስኖር አንድ ቀን ታዲያ የምወደው ጓደኛዬን አብረን ጥሬ ስጋ ሥንበላ አንቆት አይኔ እያየው እጄ ላይ ቀረ።

ተከስተ፡- ማለት.....ሞተ?

አባት፡- አዎን ሞተ! /ፋታ/ ታዲያ ይህቺ ቀን ልቤን ሰበረችኝ የአመል አድፌን ታጥቤ ዳግመኛ ሠው ሆኜ ተወለድኩ /ፋታ/

ተከስተ፡- ባጣም የሚገርም ታሪክ ነው ከዚያስ

አባት፡- ከዚያማ ከጥንቱ ማንነቴ ተጣላሁ። አመፅ ትቼ ከልቤ ማደር ስጀምር ከምኖረው በእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን እድሜ የእግዚአብሔር ስጦታ እንጂ የጀግንነት ውጤት እንዳልሆነ ተረደሁ። ሁሉን እርግፍ አድርጌ ወደዚህ መጣሁ፤ ተጣጣርኩ የእነዚህን ልጆች አባት ወለድኩ

ተከስተ፡- እሱን ብቻ ነው የወለዱት አይደል?

አባት፡- አዎን እሱን ብቻ ነው የወለድኩት። ከዚያ በኋላነው እንግዲህ ምንም እንካ ስልጣነ ክህነት ለመቀበል ባልበቃም እድሜዬ አልፋል ብዬ በእድማዬ ሣላሳብብ አባቶች እግር ስር ቁጭ ብዬ እቆሎ ት/ቤት በተማርኩት ላየ ብዙ የጨመርኩት ከአንድ ልጅ በቀር ቢነፍገኝም ይህ አንድ ልጄ እነዚህ የምታያቸውን የልጅ ልጄ አሣየኝ። ምን ያደርጋል የዘመናችሁ ዘራፊ መቅሰፍት አንድ ልጄን ከነሚስቱ ዘረፈኝ። በዚህ አልበቃ ብሎት ለእናንተ በልጅ ልጆቼ አስፈራራኝ። ልጄ በ3 ፍሬዎች ቢወሠንም ዛሬ ደግሞ አንተን አራተኛ ልጅ አድርጐ ሠጠኝ።

ተከስተ፡- እግዚአብሔር አናቴን ቢነጥቀኝ እናት ሆኑኝ። ያኔ ከናሆም አገናኝቶ ልቡን አራርቶልኝ መግቢያ አጥቼ ስማፀነው በወጣትነቴ እዚህ ቤት ባይጥለኝ ኖሮ ይኼኔ እናቴን የወሰደ የዘመናችን በሽታ እኔንም አስከትሎኝ ነበር።

አባት፡- አሁንም በርትተህ ከዚህ በሽታ እራስህን ጠብቅ ልጄ! ወድቆ መነሣት ትላንት ቀረ ዛሬ ከወደቁ ወድቆ መቅረት ነው። ይኼ ሀጢያት የጫረው እሳት ስለማይበርድ ራስን በእግዚአብሔር ደጅ በቤተክርስቲያን ጥላ መጣል ነው የሚበጀው **/ክንዴ ድንገት ይገባል/ አረንጓዴ መብራት ይበራል** !!

ክንዴ፡- አባባ! ሌሊት በህልሜ እባብ ከኪሴ ወጥቶ ሲነድፈኝ አየሁ አያስፈራም?

አባት፡- አይዘህ አትፍራ ቅዠት ነው

ክንዴ፡- ቅዠት አይደለም አባባ። ትላንት ለሁለተኛ ጊዜ ማየቴ ነው።

አባት፡- ሁለት ጊዜ?

ክንዱ፡- አዎን!! ሁለት ጊዜ አየሁ፣ ሁለት ጊዜ ፈራሁ። /ይስቃል/ ለካ እብድም ይፈራል /ሳቅ/ ፈራሁ.....ፈራሁ አንተስ አልፈራህም ተከስተ? ነው ወይስ ለእባቡ መርዝ ማርከሻ አለህ? ግድ የለም ፍራ አለም አንዳንዴ የኮንትራት ውል ትሠርዛለች፣ አባባ ኢያሪኮ ካራ ሣለች፤ ማነው የሣለላት፣ ማነው ካራጁ ይውል ዘንድ በሬ የሆነላት አዎ በሬም ከአራጁ አይውል፣ የኢያሪኮም ካራ ደም አይነካ ባቢሎን ለምን ሣቀች፣ የባቢሎን ጥርሶች ወይ ይስቃሉ ወይ ይነክሣሉ እምቢ አልኩኝ በአምላኬ! ባቢሎን ጥርሷ ይረግፋል ቁመናዋ ይፈርሣል። ከባቢሎን የተባበሩ፣ በፈገግታዋ የፈገጉ የሷ ልጆች በመርገፋቸው ይዋጋሉ መርገፍ ውበት ነው እንዴ? በሠው ልጅ በሃጢያት ማለቅ መተላለቅ ውበት ሆነው ቀለም ሆነው ቱፍ የባቢሎን ጥርሶች ይረግፋሉ፤ የኢያሪኮ ቅጥሮች ይፈርሣሉ

አባት፡- እስኪ አረፍ በል ልጄ! አይደክምህም?

ክንዴ፡- ምን እረፍት አለ! በሚንቀለቀል እሣት እረፍት እንዴት ይታሠባል። በሠዎች ክፋት የልብ ልብ ያገኘችው ምድር በሩቅ ከምንፈራት ሲኦል ከፋች። ከሃጢያት ላንቃ የተተፋው ሠደድ እሣት እናትና አባቴን በላ እኔንም በወላፈኑ አስፈራራኝ። /HIV/ የእሳት ላንቃ የእሳት ካራ። ሔሎ ማንም በሀጢያት የሠባህ ብትኖር የኢያሪኮ ካራ ሣያርፍብህ ክብደትህን በንስሃ ቀንስ **/ወደ ተከስተ በመዞር/** አንተስ አልሰባህም? ዝም አትበለኝ ለኢያሪኮ ዝምታ መልስ አይሆንም፣ መልስህን ቀይር በሃይማኖት ክብደትህን መዝን .....ቱፍ የባቢሎን ጥርሶች ይረግፋሉ ፤ የኢያሪኮ ቅጥሮች ይፈርሣሉ **/ወደ ውስጥ ይገባል/**

አባት፡- አንዲያው ምን ይበጀን ይሆን ተከስተ? አሁን ደግሞ ጤነኛ ሠው ከሚናገረው በላይ ያናግረዋል።

ተከስተ፡- ምን ይደረግ አባባ! እናት አባቱን የወሰደ እሣት አልበርድ ብሎ ትውልዱን ወደሞት ሲያግዝ እንዴት ዝም ይበል። ይልቅ ጤንነታችን የሚያጠራጥር እኛ ነን እሣት እያየን ዝም ያልን።

አባት፡- ለአፋችን ዝም ያልን ያህል ለሠዶማዊ ግብራችን አርምሞ ብናበጅለት

ተከስተ፡- አሁንስ እኔም ፈራሁ

አባት፡- ፍርሃታችን ከከንፈራችን አይወርድም.....ልባችን ከሠዶምና ከገሞራዎች ከንፈራችን ደግሞ ከነነዌ ህዝቦች ጋር ነው፡፡ **/ናሆም ይገባል/**

ናሆም፡- እንደምን ዋላችሁ?

አባት፡- ምን ሆነሃል ልጄ? ፊትህ ጥሩ አይደለም፡፡

ናሆም፡- አባባ.....አ...ባባ እንዴት ልናገር!

አባት፡- ምኑን ልጄ?

ናሆም፡- ጉዱን ነዋ?

አባት፡- የምኑን ጉድ ልጄ

/አስደንጋጭ ክላሲካል/

ናሆም፡- ሌሊት ከቤተክርስቲያን የመፃር መስቀሉን የብራና መፃህፍቱ በአጠቃላይ ተሠረቁ

አባት፡- ሠዓሊለነ ቅድስት ምን አልክ ልጄ **/ከተቀመጡበት ይነሣሉ/**

ተከስተ፡- ማን ይሆን የሠረቀው

ናሆም፡- ለጊዜው ምንም የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ እርሱ ባለቤቱ ይወቃቸው እንጂ

አባት፡- አቤት! አቤት አንተ ትወልድ በሀጢያት ጅረት አያሌ የሞት ችግኝ የምታፈላ የእንብላ ፣የእንጠጣ ፣የእንሙት ፣ከንቱ ዜጋ! ተስፋ ቆርጠህ እግዚአብሔርን ትሠርቅ፡፡ ይኸው ሮጠህ ሮጠህ በጥፋት ብዛት መቃብር ባደረካት ምድር ዝንት አለም የምትኖር አትመስልም? ለመቼ ነው እንደዚህ የምታመቻቹት? እንግዲህ አንተም ሩጥ የፈርኦንን ሠራዊት የቀደመ አምላክ ቀድሞ ይቆይሃል፡፡ የገዛ ስንፍናህ ለሞት ደጃፍ የከለከለህ የቁም ተገናዥ! ምን አለ በሞትህ ሌሎችን ባትገድል? ሞቶ ለሞት መግደልን በአንተ አየን፡፡ ክርስቶስ በሞቱ ሲያድን እንጂ ሲገድል አላየንም፡፡ ከተነቢተ ነብያት ፣ ከስብከተ ሐዋርያት በስተግራ የምትኖር የተቃርኖ ከንቱ ዜጋ እግዚአብሔር ጨርሶ ይማርህ እንጂ ምን እላለሁ፡፡ **/ወደ ውጭ ይወጣሉ/**

ተከስተ፡- አይዞህ ናሆም እግዚአብሔር ስለቤቱ ዝም አይልም ይኼን ቀድሞ ይጠብቃቸዋል

/ክንዴ ይመጣል/

ክንዴ፡- ምንድን ነው የምሠማው ናሆም? ይህቺ ባቢሎን ጥርሷ ካልረገፈ መንከሷን ፣ ይቺም ኢያሪኮ ቅጥሯ ካልፈረሰ ማጥመዷን አትተውምና ሠላም የለንም ከጉያችን ተሠንቅሮ የሚያነቅዘን ነቀዝ መርዝ ይረጭበት፤ ለነቀዙ ሃቅ ነውና መርዙ ሃቅ ይረጭበት ::በትንሻች ሰማዕትነት ብዙዎች ይትረፉ.. /ተከስተ ብሎ ይጣራል/

ተከስተ፡- /በድንጋጤ/ አቤት

ክንዴ፡- ፈራህ

ተከስተ፡- አይ.....ማለት.....

ክንዴ፡- ተወው..... ተወው ፈርተሃል..... ፈርተሃል /ይስቃል/ መጋረጃ ይዘጋል::

ትዕይንት ፪

መጋረጃው ሲከፈት ማይክና ተከስተ ተቀምጠው ይታያሉ

ተከስተ፡- በነገራችን ላይ ጉዳዩ ከምን ደረሠ?

ማይክ፡- ጉዳዩ 4ኛ Step ላይ አድርሰነዋል:: ግን.....

ተከስተ፡- ግን ምን?

ማይክ፡- እዚህ ቤት ያለ ወጠጤ በእሳት እየተጫወተ ነው

ተከስተ፡- ማን? ናሆም?

ማይክ፡- አዎ! ኖሆም እያሠጋን ነው

ተከስተ፡- አይደረግም! በለው እንዴት ባክህ

ማይክ፡- በጣም የሚገርም ነው:: እንዳልኩህ እቃው 4ኛው Step ላይ ነው ያለው እሱ ግን አነፍንፎ የመጀመሪያውን Step ጨርሶ ሁለተኛው Step ላይ ደርሶ ነው አቅጣጫችን የጠፋበት

ተከስተ፡- በዚህ አይነትማ ጊዜ ይወስድበታል እንጅ ቅርሱ ቢወጣም እኛ መያዛችን አይቀርም ማለት ነው::

ማይክ፡- ልፋታችን ምን ጠቀመን ታዲያ እኛ ከተያዝን

ተከስተ፡- ምንም:: ስለዚህ በፍጥነት እርምጃ መወሰድ አለብን:: አስብበት:: እኔ የምልህ?

ማይክ፡- አቤት

ተከስተ፡- ለምን «X » /ኤክስ/ አይሠራም

ማይክ፡- ልጅቷ ከበደችኝ

ተከስተ፡- ልጅቱ ምን ልታወቅ ትችላለች? ደግሞም ለእሷ ያሰብነው ከሞት እንደማያንስ አስብ፡፡

ማይክ፡- ሀሊናችንስ

ተከስተ፡- እንዴ ሀሊናችን ብለን ነው እንዴ ይህን ስራ የጀመርነው፡፡ የበጐ አድራጐት ስራ አይደለም እኮ እየሰራን ያለነው፡፡ እንዲህ አይነት ጨዋታ ውስጥ ከገባህ በኋላ ሀሊና ትላለህ እንዴ! እርሳው ጨርሰህ እርሳው ሀሊናህን

ማይክ፡- በርግጥ ጨዋታው ቀላል እንዳልሆነ አውቃለሁ፡፡ ግን ሌላ አማራጭ መጠቀም ብንችል ብዬ ነው፡፡

ተከስተ፡- እየውልህ ማይክ አንድ ነገር ማወቅ አለብህ፡፡ በፊትም ይህን ፕሮጀክት ስንቀርፅ አፅንኦት ያልሰጠነው አንድ ነገር አለ፡፡ ይኸውም ናሆም የሚባል ልጅ «X » ካልተሠራ ካልተወገደ ይኼ ቅርስ ይህችን ምድር ለቆ አይወጣም፡፡ ምክንያቱም ናሆም ማለት በቤተክርስቲያን ነገር ከመጣህበት እስከመጨረሻ የሚፋለም ፣ ህይወቱን ሣይቀር አሣልፎ የሚሰጥ ቂል ቢጤ ነው፡፡ «ዘመን ከበረረ ጅል ካመረረ» አይደል የሚባለው ይታይህ አንተም እንዳልከው ልጅቱን ጅቡቲ ድረስ ወስደህ መጀመሪያ ሁኔታዎች እስኪ መቻቸልህ መደበሪያህ አድርገህ ከዚያም ለአንድ ጅቡቲ ሃብታም ሸጠሃት ሮም መወጣት ቀርቶ ወህኒ ቤት ወርደህ ዝንተ አለም ስትማቅቅ የጉም እቅድ ቅዠት ሲሆን ይታይህ፡፡

ማይክ፡- አቦ ተኬ ደግ ደጉን አውራ እንጂ!

ተከስተ፡- ደግ ደጉን እያወራን ችላ የምንል ከሆነ ነገሮች የበለጠ «Complicated» ይሆናሉ ከእንግዲህ ወደህ ደግሞ ወደኋላ መመለስ የማይሞከር ነው፡፡ እውነቱን ነው የምልህ ማይክ ለዚህ ጉዳይ ሙሉ በሙሉ potential/ ክህሎትህን/ ተጠቀም፡፡ መጀመሪያ ይታገት፡፡ ከዚህያም ቀስ በቀስ ቦታና ሁኔታዎችን አመቻችቶ ሞተር ማስጥፉቱ በፍጥነት መወገድ አለበት፡፡ አስብበት፡፡

ማይክ፡-OK! የልጁን ለኔ ተወው፡፡ ከእንግዳህ በዚህ ነገር አንድ ስንዝር የሚራመድ ከሆነ ይታገታል ይልቅ ባንተ በኩል ያለው እንዴት ነው ባለፈው የዚያ የእብድ ሁኔታ አላማረኝም ብለህ ነበር?

ተከስተ፡- አዎ! አሁን አሁን ጭራሽ እየበዛ ነው፡፡ የሚገርምህ ትላንት በጣም አስደነገጠኝ «በጥቂቶች ሰማዕትነት ብዙዎች ይትረፉ፡፡ በጉያችን ተሰንቅሮ የሚያነቅዘንን ነቀዝ የሀቅ መርዝ ይረጭበት» ብሎ ሲቀባጥር እኔ ስለዚያው ስለ HIV ነው ብዬ አይን አይኑን ስመለከት «ተከስተ» ብሎ አምባረቀብኝ «አቤት» እለዋለሁ «ፈራህ» ብሎ የመጨረሻ አርበተበተኝ

ማይክ፡- ለምን እሱ መጀመሪያ «X » አይሠራም

ተከስተ፡- No, No ባይሆን ባስ ካላበት ይታገታል ይልቅ በጣም የሚያስጨንቀኝ ያኛው ነው፡፡ የሚገርመው ሁኔታው ሁሉ ያስፈራል፡፡ ብቻ የእሱ መወገድ ይፍጠን.....ይፍጠን...

ማይክ፡- እሱን ለእኔ ተወው፡፡ የሽሮ ድንፋታ እንጀራ እስኪቀርብነው አለ እጅ እስክትገባ ነው የምትቧርቀው ወጠጤ ወዳም ይሁን ተገዳ ወደ ሞት ታቀጥናለች፡፡

ተከስተ፡- እኔ የምልህ ማይክ ከልጅቷ ጋር እንዴት ናችሁ ካስተዋወካቹሁ ወዲህ

ማይክ፡- በጣም ተግባብተናል በጣም fast ነች፡፡ «Modern» «Modern» ትሸታለች ብቻ እንደ ቤተክርያስቲያን ልጅ «Act» አተደረግም ልጠይቅህና የቤትክርስቲያን ልጅ አይደለችም እንዴ?

ተከስተ፡- ባክህ ከምኑም የለችም

ማይክ፡-OK! ለዚህ ነው “excess freedom” የምታሣየኝ፡፡ እኔ እንደውም እየፈራኋት ነገሮችን ሁሉ በጥንቃቄ ነበር የያዝኩት፡፡

ተከስተ፡- የሚገርምህ እቤት ካሉት እርሷ ብቻ ነች ለክርስትናው ችላ የምትለው፡፡ ልጅቷ ምንም ዓይነት ሃይማኖታዊ ጫና አትፈልግም፡፡ ታዲያ በዚህ ፍላጐቷ እብዱ በወጣ በገባ ቁጥር ውሻ ያደርጋታል፡፡ ሽማግሌውም ቢሆን አልፎ አልፎ አይተኛላትም፡፡ ያኛው ግን /ናሆም/ በድብቅ ነው መሠለኝ የሚመክራት ፊት ለፊት ሲናገራት አልሠማሁም፡፡

ማይክ፡- ወይ ሶስና

ተከስተ፡- እንዴ! ሶሲ በል እንጂ **/በአሽሙር/**

ማይክ፡- ኧረ እንዲያውም ሶስዬ ነው የምላት፡፡ የጅቡቲ ሃብታም ራህማ እስኪሚላት

ተከስተ፡- እኔ የፈራሁት አንተው እንዳትቀርባት ነው፡፡

ማይክ፡- ኧረ እባክህ ከሮም በልጣ?

ተከስተ፡- ለምን ይዘኋት ሮም አትገባም? **/በሹፈት/**

ማይክ፡- ምነው በምን እዳዬ እሷን ላንካትት! ደግሞ እዛ የሲኞር ግራዚያኒ የልጅ ልጅ እንደምትጠብቀኝ አትርሳ

ተከስተ፡- እስኪ ይቅናህ

ማይክ፡- አቦ እንደሱ በለኛ ሌላው ቀርቶ ከነፍሴ እዚህ አገር ከምኖር ሬሣዬ ሮም አፈር ውስጥ ቢኖር ይሻለኛል፡፡ ምክንያቱም አለሁ ብዬ እዚህ አገር ከምጠራው ከኔ ይልቅ መቃብር ውስጥ ያለው የጣሊያን ሬሣ ጥሩ መኝታ ይተኛል፡፡ ወይኔ ማይክ ባለፈው እኮ ፕሮሰሱን “Underground”

ጨርሶ ብዙ ከለፋሁ በኋላ ለጥቂት ማንቁርቴ ይዘው እዚህ ሰቆቃ ምድር የወርወሩኝን ህርም ጠጥቼ ካልተበቀልካቸው!

ተከስተ፡- አይዞህ አሁን ብዙ ልምድ ስለአካበትክ በቀላሉ ትወጣለህ

ማይክ፡- አሁን ግን በተዓምር አያቆሙኝም! እዚህ ያለውን “Step” ብቻ እንጨርስ ይሄ ትንሽ “Challenge” ያለው የፕሮጀክታችን “Step” ነው። ከዚያ በኋላ ተከስተ ሲመጣ ማይክ ሮም ላይ የድል “Ceremony” ደግሶ ይጠብቀውና በኩራትና በድል አድራጊነት ስሜት በሮም አደባባይ ዋንጫችንን እናነሳለን።

ተከስተ፡- እስኪ ለማንኛውም እርሱ ይረዳን!

ማይክ፡- ማንው የሚረዳን?

ተከስተ፡- ሣጥናኤል ልበልህ?

ማይክ፡- ትክክል! እርሱ እንደሆነ ክፉ ማድረግ አያቅተው። እኛን የሸወደ መስሎት ሣያውቅ ፋሲሊተተራችን ሆነ አይ ይሺል ቆራጡ አይተኛ!

ተከስተ፡- ከእርሱ ጋር ያለንን ውል ሮም ስንደርስ እንነጋገርበታለን።

ማይክ!- አንተ! ውል ውል ..... እያልክ ግንኙነታችንን official አታድርገው። አይበለውና ወደ እኛ የዞረ እለት እኮ.....

ተከስተ፡- እስኪባንን ሮም እንገባለን

ማይክ፡- ከዚያስ?

ተከስተ፡- ከዚያማ ተከስተ ገብሩ ለዲያብሎስ ማይክ ለሰይጣን

ማይክ፡- የተባለለት ጊዜያዊ ደብዳቤ በ.....በ.....

ተከስተ፡- በላ በምን ይደምሰስ? መቼም ክርስቶስ የእኛን ውል ለመደምሰስ ዳግመኛ ይወለድ አትልም።

ማይክ፡- በቃ ሮም የምንሰራው “Assignment” ይሁን **/ሶስና ትገባለች/**

ሶስና፡- ታዲያስ ማይክ?

ማይክ፡- ሐይ ሶሲ

ሶሲ፡- እንደምን ነህ?

ማይክ፡- አምሮብሻል!

ሶስና፡- አመሰግናለሁ

ማይክ፡- ከየት ነው?

ሶስና፡- ከገቢያ ነው ባክህ!

ማይክ፡- ገቢያው እንዴት ነው?

ሶስና፡-OK ነው መጣሁ ማይክ **/ዕቃውን ይዛ ወደ ውስጥ ትገባለች/**

ተከስተ፡- ስማ እንጂ ካራጇ የዋለች ጊደር

ማይክ፡- ሮም ፀሃይዋን እስክንወርስ ድረስ መቅረብ ያለበት መስዋዕት ሁሉ ይቀርባል፡፡

ተከስተ፡- የባቢሎን ጥርሶች አለ ያ ዕብድ

ማይክ፡- በል ፍሬንድ እኔ ልቀንጠስ

ተከስተ፡- ለምን?

ማይክ፡- በዚህ ዓይነት ሁኔታ ከወንድሞቿ አንዱ ከመጣ “hard” ነው፡፡ አይመስልህም?

ተከስተ፡- ያን ያህል አትስጋ

ሶስና፡- **/ትወጣና/** እንዴ ማይክ ለምን ተነሳህ?

ማይክ፡- ቅጣት ነው

ሶስና፡- ለማን? ለኔ?

ማይክ፡- አምን ናፍቆት አቅለብልቦ ስንት ስራ ትቼ ብመጣ ሙሉ ቀን ደጅ በማስጠናችሽ ችሎቱ ግራ ቀኙን ተመልክቶ በናፍቆት የጮዳ በናፍቆት ይቀጣ ሲል ፋይል ዘግቷል፡፡

ሶስና፡- በናፍቆት ችሎት ይግባኝ ማለት አይቻልም?

ማይክ፡- ለናፍቆት ችሎት ይግባኝ የለም

ሶስና፡- አሁን ቀልዱን ተውና ቁጭ በል እስኪ

ማይክ፡- ቁም ነገሬን ቀልድ በማድረግሽ ሌላ ፋይል እንዳልከፍት

ሶስና፡- እሺ ስሞትልህ ትንሽ ቆይና ሂድ

ማይክ፡- ምነው ሶሲ! አንቺ ከምትሞች እኔ አርባ ጊዜ ሞቼ ልነሳ

ሶስና፡- አርባ ጊዜ መሞቱ ይቅርብህና አሁን ለትንሽ ጊዜ ቁጭ በል

ተከስተ፡- ብልጡ ቀድሞውኑ መች ተነሣህና ነው አርባ ጊዜ ደጋግመህ የምትሞተው

ማይክ፡- ቀብረኸኝ ነበር እንዴ ውድ ጓደኛዬ?

ተከስተ፡- ያውም ገንዘቤ ነዋ!

ማይክ፡- ምንኛ ነው የምታወራው?

ተከስተ፡- ክርስቲያንኛ

ማይክ፡- እንዲህ ነው መደበላለቅ። ኧረ ለመሆኑ አንተ ማነህና ነው ለእኔ ቀባሪ የሆንከው?

ሶስና፡- እንጃ! ከመቼ ወዲህ ነው ሙታን ሙታንን የሚቀብሩት?

ተከስተ፡- ሙታንን ሙታን ይቅበሯቸው ብሎ የለ እንዴ በወንጌሉ

ማይክ፡- እኔን ለመቅበር ነዋ የምትኖረው የኔ ሙት?

ተከስተ፡- ሙት እስከሆንክ ድረስ

ማይክ፡- አያልቅበት በል ይብቃህ። ለማንኛውም ቻው ሶሲ

ሶስና፡- እምቢ ብለህ መሄድህ ነው ማይክ? እሺ መች ትመጣለህ?

ማይክ፡- መች ትቀራለህ ብትይ

ሶስና፡- እንጠብቅሃለን

ማይክ፡- ቻው

ተከስተ፡- እሺ ሶሲ ያልሽውን ዕቃ አገኘሽ?

ሶስና፡- አዎን እኔ እምልህ ተኬ ማይክ እንዴት መጣ ዛሬ?

ተከስተ፡-አንቺን ሊጠይቅ ቆይቷል እኮ ከመጣ

ሶስና፡- ፀባዩ በጣም “comfort” ነው

ተከስተ፡- እርሱም አንቺን እንደዛ ይላል

ሶስና፡- በእውነት?

ተከስተ፡- በእውነት **/አባት ከውጪ ይገባሉ/**

አባት፡- አላችሁ ልጆቼ **/አይቀመጡም/**

ተከስተ፡- አለን አባባ

አባት፡- ሶስናዬ ምነው ዛሬ ከነጋ ጀምሮ አላየሁሽ?

ሶስና፡- ገቢያ ሄጀ ነው አባባ

አባት፡- መቼም አንቺ የስጋ እንጂ የነፍስ ገበያ አያውቅሽ

ስስና፡- አባባ ደግሞ ሊወቅሱኝ ነው

አባት፡- የእኔ ወቀሳ ሳይሆን ከደጉ አባት ከእግዚአብሔር የምትለየውን አለምን ፍሪ ራቂያት

ሶስና፡- ሁል ጊዜ እንደዚህ ይላሉ ቆይ አለም ውስጥ እያለሁ እንዴት አለምን እርቃለሁ

አባት፡- ቅዱስ ጳውሎስ በአለም እያለው እኔ በአለም ዘንድ የሞትኩ ነኝ አለምም በእኔ ዘንድ የሞተች ናት ብሎ የለ?

ሶስና፡- እንዴ አባባ ታዲያ እኔ ቅዱስ ጳውሎስን አይደለሁ?

አባት፡- እኔ ክርስቶስን እንድመስል እናንተም እኔን ምሰለ ማለቱንስ ለማን ታደርጊው?

ሶስና፡- እስካሁን ማን መሰለው?

አባት፡- ስትመስይው የመሰሉትን ታያቸዋለሽ

ሶስና፡- ለማየት መምሰል ግድ ነው?

አባት፡- አይተው ያልመሰሉ ቢያንስ ለመምሰል ያልሞከሩ ዝንት አለም ባይተዋር ናቸው፡፡ ከልብሽ ሆነሽ በአኗኗርሽ ቅዱሳንን ለመምሰል ጣሪ፡፡ ለሷ ብቻ አይደለም ለአንተም ነው ተከስተ

ተከስተ፡- እሽ አባባ እኔማ ትንሽ አይኔን የገለጥኩ ይመስለኛል፡፡ እድሜ ለናሆም እስከ ማብቂያው ለማየት መንገድ ጀምሬያለሁ፡፡

አባት፡- እስከ ማብቂያው አልክ? ክርስና እየሄድክ የምታልፍባት ህይወት አልያም መንገድ ነው፡፡ ማብቂያውን በእውነት የምታየው ነፍስህ ከስጋህ ከተለየች በኋላ ሲሆን እስከዚያ ግን በተስፋ ታያለህ፡፡ በሉ እኔ ልግባና አረፍ ልበል፡፡ ደክሞኛል፡፡

ተከስተ፡- ቆይ ትራስ ልቀይርልዎት **/አባትን ተከትሎ ይገባል/**

ክንዴ፡- **/ከውጭ ይገባል/** የባቢሎን ጥርሶች ይረግፋሉ፤ የኢያሪኮ ቅጥሮች ይፈርሳሉ፡፡ ምናለ በሉኝ ባቢሎን ራሷን ትነክሳለች ኢያሪኮ ቅጥሯን ታፈርሳለች የሚሆነው ሁሉ በእግዚአብሔር ጥበብ ይሆናል **/ወደ ሶስና ዞሮ/** ወ/ሪት ሶስና!

ሶስና፡- **/በመደንገጥ/** አቤት!

ክንዴ፡- ኧ ለእኔ እንዲህ ከምትበረግጊ እግዚአብሔር ብዙ ሺህ ጊዜ ደጋግሞ ሲጠራሽ ምናለ አንድ ጊዜ እንካን ደንግጠሽ አቤት ብትይው፡፡ **/ዝምታ/** ዝም አትበይ አንቺ! ተናገሪ

ሶስና፡- ምን ልናገር?

ናሆም፡- **/ከውጭ ይገባና/** እንደምን ቆያችሁ

ክንዴ፡- የምትናገሪው ጠፋሽ? የምትናገሪው ቀርቶ የምትሰሪው መች ይጠፋሻል አንቺ!

ናሆም፡- አሁንም ጭቅጭቅ ላይ ናችሁ.....ተው እንጂ ወንድምዬ ለምን አትተዋትም?

ክንዴ፡- መሞቷን ካልተወች አልተዋትም **/ፋታ/**

ሶስና፡- የቅርሱ ጉዳይ ከምን ደረሰ ናሆሚ? ምንም ፍንጭ አልተገኘም?

ናሆም፡- ተንሽ ፍንጭ አግኝተን ነበር ግን ብዙ መጓዝ አልቻልንም ለነገሩ ምህላ ተጀምሯል፡፡ እኛን ቢቀድሙም እግዚአብሔርን አይቀድሙም፡፡

ሶስና፡- ፍንጩ አጥጋቢ አልነበረም?

ናሆም፡- በእርግጥ ተስፋ አስቆራጭ አልነበረም፡፡ ተስፋ አስቆራጭ ቢሆን እንካ ክርስቲያን ተስፋ አይቆርጥም

ክንዴ፡- ወንድሜ ናሆም ለዚህ ቅርስ መድከምህን አልጠላውም ግን ሌላውና ቅስም ሰባሪ ስርቆት ቸል ብለኸዋል

ናሆም፡- ምንድን ነው ወንድምዬ?

ክንዴ፡- ቤተ መቅድስ እየተሰረቀ ነው፡፡ ለዚህ ስርቆት ግን ማን ይባዝን! ማን ሱባኤ ይግባ! እኔ እንደሁንኩ እብድ ነኝ፡፡

ሶስና፡- ማነው የሰረቀው?

ክንዴ፡- ማነው ባዩ ቢሆንስ?

ሶስና፡- አልገባኝም

ክንዴ፡- እንዲገባሽ አትፈልጊማ

ሶስና፡- መች አልፈልግም አልኩ፡፡

ክንዴ፡- እያወራሁ ያለሁት ስለግበርሽ እንጂ ስለ አንደበትሽ ቃላት አይደለም፡፡ ለነገር በአንደበትም ቢሆን አውሮፓንና አሜሪካን እንጀራ አድርገሻል፡፡

ስሚ አውሮፓና አሜሪካ እኮ የዛሬ ማንነታቸውን የዛሬ እድገታቸው ትላንት በጥቆሮች ደም ያቦኩት የስልጣኔ ኩፍታ ነው። እኛስ ደሙን ባንሸምለምን ላባችንን አንሰዋም። ለምን የጠራ ማንነታችንን ረስተን የደም ልውሳቸውን እንናፍቃለን። በእብራዊቷ ራሔል ህፃናት ደም ተለውሶ የተገነባው የፈርኦን ግንብስ ማን ኖረባት? እንኪያስ የሰማዩ መንግስት የሰማዩ እልፍኝ ማንን ይጠብቃል። ዳሩ አነቺ ምን ታደርጊ ትውልዱ ነው። አጅ እግሩን አጣምሮ ምንም ባልነፈገችው መሬት ላይ የሚጮኸው። እስኪ ይህቺ አገር ምን ታድርግ? ብንዘራባት አብቅላለች፣ ብንተክልባት አፅድቃለች። ያልተዘራውን እንድታበቅል ለምን እንጮኽባታለን። መጮኽ ካለብን ምናለ እንደ ራሔል ሽቅብ ወደ ሰማይ በንጮኽ የክፋታችን ማጥ እንደሆነ እሷ ከረገጠችው ማጥ ይበልጣል።

ናሆም፡- ማጡ ተመችቶን ይሆናል ዝም ያልነው። ይልቅ አንተም ዝም በል።

ክንዴ፡- ዝምታ፣ ዝምታ ከእኛ ሊያምር? እሳት ውስጥ ቆሞ አርምሞ! ዝምታ እንዴት ተደርጐ በል።

ናሆም፡- በትር በእጁ ሳለ ዝም እንዳለን እንደ እግዚአብሔር

ክንዴ፡- እያሾፍክ ነው?

ናሆም፡- ክርስትና ለሹፈት የማትመች የሐቅ የቁምነገር ፎኖት ነች። እሷ ላይ ቆሞ ሹፈት አይታሰብም። ወንድምዬ የሐሳብህን በእግዚአብሔር ከመጣል ይልቅ ነገሮችን ሁሉ የመቻል አቅምህን ትጠራጠርና ቀድመህ ትሸነፋለህ።

ክንዴ፡- ናሆሜ አልተሸነፍኩም እኔ! **/በኃይል/**

ናሆም፡- ከእግዚአብሔር ሐይል በኩል መቆም አሸናፊነት መሆኑን ዘንግቶ ለትንሽ ለትልቁ በሐሣብ መናወዝና መጨነቅ ለራሱ መሸነፍ ነው። ወንድምዬ ነገሮችህ ሁሉ በቁጣና በብስጭት አይሁኑ ነው እያልኩ ያለሁት። አነተ ግን አትሰማኝም ለምን? ነው ወይስ እኔም እንደሌላው ህሊናውን ስለሳተ የሚያደርገውን አያውቅም ብዬ ዝም ልበል? ሶሲን አትምከራት አትናገራት አልልህም ግን ምክርህም ይሁን ብስጭትና ቁጣህ ያስተማሩን እናስበ እውነት በአበው መንገድ ላይ ነው ያለነው፤ የት እንዳለንና አቋቋማችንን እንመርምረው።

ክንዴ፡- ያልከወ ሁሉ ክርስትና ለሚገባው ነው። እኔ ግን ከእንዲዚች አይነቱ ጋር ነው ያለሁት።

ናሆም፡- እስኪ ታላቁን ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስን አስበው። ክርስትና ያልገባቸው ብቻ ሣይሆኑ ክርስትናን የሚቃወሙ ሴራኞች ተረባርበው ሲወግሩት ምን እንዳለ አስብ

ክንዴ፡- ያለነው 21ኛው ክ/ዘመን ላይ ነው

ናሆም፡- እና?

ክንዴ፡- እናማ ክርስትና ባትለወጥም ሰው ግን ተለውጧል

ናሆም፡- ለምን ይመስልሃል?

ክንዴ፡- ጊዜ አስገድዳት

ናሆም፡- አህያውን ፈርቶ ዳውላውን እንዲሉ የፅድቁም የኩነኔውም ባለቤት የሆነውን ትውልዱን ፈርተን ከነቅራቅንቦአችን ያዘልን መርከብ ላይ ጣታችንን መቅሰራችን በራሱ ከሃጢያት በታች የሚያስረን ይመስለኛል። ጊዜ እንዲሁ ኡደቱን አለተወ ይመሻል ይነጋል

ክንዴ፡- መሽቶ መንጋት የወለደው ሥልጣኔስ ተጠያቂ አይመስልህም?

ሶስና፡- እንዴ! ሥልጣኔ ምን አጠፋ? ሥልጣኔ እኮ በመልክዓ ምድሯ፣ በቋንቋዎቿ በባህሏና በህዝቦቿ ሩቅ ለሩቅ የነበረችውን አለም በማቀራረብ አንድ መንደር አድርጐ የመዘዋወር መብታችንን አስከበረ እንጂ ምን አጠፋ?

ክንዴ፡- ኧ.....ይህቺ ናት ሶቅራጥስ። ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ አለ። የምን ጅኦግራፊ ነው አምጥተህ የምትቀላቅይው?

ሶስና፡- ሥልጣኔ ከሆነ እሱንም ያካትታል

ክንዴ፡- እንቺ ልጅ ግን በምንሽ ነው የምታስቢው?

ናሆመ፡- መድረኩን አትንጠቁኝ ውይይቱ እኮ የጋራ ነው።

ክንዴ፡- ምን ላድርግ እህ ብንላት እዛው አውሮፖና አሜሪካ ይዛን ልትሄድ ነው። የደላት/የሞላት!

ናሆም፡- ለማንኛውም መስመር ለቃችኋል አሁንም ነገሮችን ወደየራሳችን ለማምጣት ድፍረት አጥተናል። እስኪ አንዴ ጊዜ ፣ አንዴ ሥልጣኔ ላይ መንጠልጠላችንን ትተን በራሣችን እንነሳ። የእኛስ ሥራ ለእምነታችን ብሎም ለቅርሳችን ምን ያህል ጥብቅ ነው? ምንም ከሆነ መልሳችን እኛ ባልኖርንበት ሠዎችን ኑሩ ማለት ከተራ ለፍላፊነት ውጭ ምንም ስም አያስጠንም። በምናወራው ቦታ ሁለ ቀድመን እኛ እንገኝ።

ሶስና፡- አለያ ግን አለማውራቱ ጥሩ መሰለኝ።

ክንዴ፡- /**በመናደድ**/ በቃ ወይዘሪት ስራየለሽም? ወደ ውስጥ ግቢ። ተነሽ !

ናሆም፡- እባክህ ወንድምዬ እንዲህ ስታደርግት እኮ ይሰማታል

ክንዴ፡- የምፈልገው እንዲሰማት ነው

ናሆም፡- ግን አንተ በምትፈልገው መልኩ ላይሰማት ይችላል። ምንም ቢሆን እኮ ወንድምዬ.....

ክንዴ፡- በል አሳጥረው/ **እያለ ወደ ውስጥ ይገባል/**

ትዕይንት ፫

/መብራት ሲበራ ወይም መጋረጃ ሲከፈት ሶስና ብቻዋን ቁጭ ብላ ትታያለች/

ሶስና፡-ስንት አመት ስንጓ የነበረው ውጭ የመውጣት ህልሜ ዘንድሮ በስንት አመቱ እውን ሊሆንልኝ ነው፡፡ ማይክ- የተናገርከው ሁሉ እውነት ይሆን? ምንም ይሁን ምን ተከትየው እወጣለሁ፡፡

ተከስተ፡- **/ከውጭ ይገባል/** ሠላም ሶሲ

ሶስና፡- **/በድንጋጤ/** ሃይ ተከስተ

ተከስተ፡- እንዴ ታዲያ ምነው ደነገጥሽ?

ሶስና፡- ይቅርታ ስለማይክ ብቻዬን እያዋራሁ ስለነበረ ወንድምዬን መስለሽኝ ነው፡፡

ተከስተ፡- ሶሲ ስለማይክ በማንኛውም ቦታና ሰዓት ማሰብ እንጂ ማወራት ቢቀርብሽ ይሻላል ምክንያቱም ክንዴ ቢሰማ ሊፈጠር የሚችለውን አስቢው፡፡

ሶስና፡- ምን ላድርግ ተኬ ልጁ ከማሰብ በላይ ነው፡፡

ተከስተ፡- ይህን ያህል?

ሶስና፡- ኧረ ከዚያም በላይ

ተከስተ፡- እድለኛ ነው በያ

ሶስና፡- በጣም! እኔ እምልህ ተኬ አንተስ እንዴት ነው? ሰሞኑን ወጣ ወጣ ያበዛኸው

ተከስተ፡- **/በድንጋጤ/** ማለት.....ምን.....ምን..... ለማለት ፈልገሽ ነው?

ሶስና፡- ምነው ደነገጥክ ታዲያ

ተከስተ፡- ደነገጥኩ እንዴ አይ ዝም ብዬ ነው፡፡

ሶስና፡- አይ ተከስተ ምን አስደነገጠህ እኔ እንደሆንኩኝ አይቸሃለው

ተከስተ፡- ማንን?

ሶስና፡- ቸኮሌት ናት እሽ፡፡

ተከስተ፡- እፎይ ተመስገን እሷን ከሆነ ያየሻት፡፡ ግን ያልሽው ሁሉ ስለልጅቱ ነው አይደል?

ሶስና1- ታዲያ ስለማን ነው ብለህ ፈራህ

ተከስተ፡- ስለትክክለኛዋ ልጅ ከሆነ ብዬ ነው

ሶስና፡- እና? ከማን ጋር ወጣ ወጣ ማለት እንደጀመርክ አሳምሬ ነው እማውቀው፡፡

ተከስተ፡- በናትሽ ሶስና በቅርብ እኮ ነው የጀመርነው፡፡ ምን ትሰቃቅይዋለሽ፡፡

ሶስና፡- ተማሪነች?

ተከስተ፡- ጨርሳለች

ሶስና፡- ብራቮ ሶስና! አወጣጣውህ መቼም፡፡

ተከስተ፡- እንዴ ያለምንም ማስረጃ ነው እንዴ የምታስለፈልፊኝ ወይኔ ተከስተ ለነገሩ እኮ.....

ሶስና፡- አይ ከተባነነ በኋላ ማለባበስ አይቻልም ለማንኛውም እስኪ መጣሁ፡፡ **/ወደ ውስጥ ትገባለች/**

ተከስተ፡- ኧረ! የኔ የአረብ ኮንትሮባንድ ማወጣጣትሽ ነው? እኔ ደግሞ የባነነች መስሎኝ እንዴት ደነገጥኩ፡፡ እህ የበቀል መቀሱ ድንቅ አመቃቀሱ ጀመረ፤ በሰበቃ ላይ የነበረው ጦር ተወረወረ፤ ከታዳኞቹ የመጀመሪያውን ታዳኝ ከጦሩ ስለት ጋር ተገናኘ፤ ከዚህ ቤት ባለዕዳዎች ናሆም ተብዬ ኮርማ ካራጁ ዋለ ምክንያቱም ናሆም ማለት በህይወት እያለ ሽንፈት ስለማይሆንለት በሞቱ ሽንፈትን ይጋታል፡፡ ቦታና ሁኔታዎችን አመቻችተው የሞት ፅዋ አስክግቱተ ድረስ መታገቱ በራሱ ትልቅ ነገር ነው፡፡ ብራቮ ማይክ አንጀቱን አራስከው ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ የእናቴን ቀን ስትሰጠው የበለጠ እረካለሁ፡፡ ቂል ቅርስ ፍለጋ ሰተት ብሎ መቃብር ገባ፡፡ መሰለው፤ ያ ልክስክስ አባቱ በልክስክነቱ እናቴን መቃብር አወረደ እኔም ይህንን ቤት መቃብር አወርደዋለሁ፡፡ እማ እኔ ተዝካር አላወጣልሽም ይኸው ነው ተዝካርሽ፤ ይኸው ነው መታሰቢያሽ፡፡ የበቀል መቀሱ አመቃቀሱ ይቀጥላል፡፡/ **ሶስና ከውስጥ ትወጣለች/**

ሶስና፡- እሽ ተከስተ/**ዝምታ.....ትካዜ** /አንተ ተከስተ

ተከስተ፡- አቤት.....አቤት፡፡/**በመደንገጥ/**

ሶስና፡- እንዴ! በቃ ይህን ያህል?

ተከስተ፡-- ም.....ም.....ምኑ?

ሶስና፡- ያሰረችህ ነዋ?

ተከስተ፡- ኧረ ከዚያም በላይ፣ እኔ እንጃ ገና ጨርቄን ሳታስጥለኝ አትቀርም

ሶስና፡- ታድላ በናትህ

ተከስተ፡- እስኪ አሁን ናሆሜ ቢሰማ ምን ይላል?

ሶስና፡- ምን ይላል ታዲያ? የፈለገ ነገር ቢሆን ከናሆም አንደበት ቁጣ እንደማይወጣ ታውቃለህ

ተከስተ፡- ግን እኮ ናሆሜ ትህትናውም ከቁጣ በላይ ያስጨንቃል። በነገራችን ላይ ዛሬ የትሄደ? ከነጋ ጀምሮ አላየሁትም።

ሶስና፡- ስለዚያው ስለቅርስ ጉዳይ ቀጠሮ አለብኝ ብሎ ነበር በሌሊት የወጣው ቅርሱን አግኝተውት ይሆን እንዴ? ምነው ያለወትሮው ቆየ

ተከስተ፡- ስለቅርሱ ጉዳይ? እርሱን ነገር አሁንም አልተወም?

ሶስና፡- ምን ይተዋል ናሆሜ እኮ የቤተክርስቲያን ነገር አይሆንለትም

ተከስተ፡- ኧረ ይበርታ በናትሽ

ሶስና፡- አደጋ አለው እኮ ተከስተ። የሠረቀው ዝም ብሎ የሚያየው ይመስልሃል?

ተከስተ፡- የተሰረቀው ቅርስ እኮ የእግዚአበሔር ነው። ታዲያ እግዚአብሔር እያለ እንዴት ስለ አደጋ ታስቢያለሽ? እንዲያውም እኮ እኔ እራሴ የድርሻዬን ልወጣ ስለው ለጊዜው አታስፈልግም ስታስፈልግ እነግርሃለው ብሎኝ ነው።

ሶስና፡- እኔ እንጃ ብቻ ይህ ነገር ደስ ደስ አላለኝም

ተከስተ፡- እና...../**አባት ከውስጥ ይወጣሉ/**

አባት፡- ተከስተ አለህ?

ተከስተ፡- ኖር አባባ አለሁ

አባት፡- ተከስተ ወዲዚያ አልወጣህም ዛሬ?

ተከስተ፡- ወጥቼ ነበር አልራኩም እንጂ። ምነው ጠየቁኝ?

አባት፡- አይ ያ ናሆም ጧት የወጣ እስካሁን ያልመምጣቱ እሳሰቦኝ ነው ምነው ያለወትሮው ሌሊትም ሲያቃዥኝ ነው ያደረው። አዬ ደስም አላለኝ እባክህ። ልጄ በሰላም በመጣ

ተከስተ፡- ኧረ ምን ይሆናል ብለው ነው? አሁን እኮ ከሶስና ጋር ስንነጋገር ነበር

አባት፡- ሶስናዬ ለመሆኑ ጧት ምን ብሎሽ ነው የወጣው?

ሶስና፡- የሆነ ሰው ስለቅርሱ የምነግርህ ነገር አለ ብቻህን ና ብሎኝ ተቀጣጥረናል ብሎኝ ነው የወጣው

ተከስተ፡- እንደዛ ብሎ ነው የወጣው?

ሶስና፡- አዎ እንዳውም አንድ ቀን አብረን ስንሔድ ከማይክ ጋር አስተዋውቄአቸው ነበር። እናም ጠዋት እንዳለኝ ከሆነ ከማይክ ጋር ነው የተቀጣጠሩት።

ተከስተ፡- ከማይክ ጋርማ አይደለም፡፡ ከማይክ አሁን ስመጣ ነው የተለያየነው፣ ከጧት ጀምረን አብረን ነበርን፡፡

ሶስና፡- ምን አልባት ከአንተ ጋር ከመገናኘታችሁ በፊት ከሆነ የተቀጣጠሩት?

ተከስተ፡- No…No…..ጠዋት ወደ 12:30 ገደማ ነው ቤተክርስቲያን ተሳልሜ ማይክ ጋር የሄድኩት እናም ስሄድ ተኝቷል፡፡ ከእንቅልፉ ቀስቅሼው አብረን ቁርስ በላን፣ ከዚያም እዚያው እሱ ቤት አብረን ቆየንና እኔ መጣሁ፡፡

አባት፡- ከሰዓት ይሆን እንዴ የተቀጣጠሩት፡፡

ተከስተ፡- ኧረ በፍፁም አይመስለኝም **/ክንዴ ይገባል/**

ክንዴ፡- የባቢሎን ጥርሶች ይረግፋሉ፣ የኢያሪኮ ቅጥሮች ይፈርሳሉ፡፡ ስላም ለኩልክሙ እንዴት አረፈዳችሁ?

አባት፡- እንደምን ዋልክ ልጄ **/ፋታ/** ክንዴ ናሆምን አላየኸውም?

ክንዴ፡- እንዴ ጧት በሌሊት የወጣ እስከአሁን አልገባም?

ሶስና፡- አልገባም፡፡ ምን ይሻላል ወንድምዬ?

ክንዴ፡- በነገራችን ላይ አባባ ዛሬም በህልማ ያ እባብ እንደልማዱ ከኪሴ ወጥቱ ነደፈኝ፡፡ ለምንድን ነው ይሔ ነገር የደጋገመኝ?

አባት፡- ፈራህ?

ክንዴ፡- ለምን አልፈራ፡፡ የዚህ ቤት ሰላም ባለበት ሁኔታ የሚዘልቅ አይመስለኝም፡፡

አባት፡- ተው ልጄ ከአግዚአብሔር ጋር ያለሰው አይፈራም፡፡ አልያ ፍርሃትህ እንደ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እንዳያሰጥምህ፡፡

ክንዴ፡- ፍራቴ እኔኑ ቢያስጥም ጥሩ ነበር፡፡ ግን አመጣጡ እንደዚያ አይመስለኝም፡፡

ተከስተ፡- እንዴት?

ክንደ፡- ቅቤ ጠባሹ እያለ ጮመን ጠባሹን ምች አጠናገረው እንዲሉ፡፡

ተከስተ፡- አልገባኝም

ክንዴ፡- አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ፡፡ አሁንም አልገባህም?

ተከስተ፡- እኔ ህልም ባየሁ ሌላ ሰው እንዳይጮዳ ማለትህ መሰለኝ

ክንዴ፡- ከሰምና ከወርቁ አንደኛው ገብቶሃል፡፡

ተከስተ፡- ሰምና ወርቅም አለው ክንዴ?

ክንዴ፡- ከሰጠኸው፡፡ ማለትም ሰጪ ካገኘ

ተከስተ፡- ስትል

ክንዴ፡- «የባቢሎን ጥርሶች መንታ መንታ
አንደኛው ሲስቅ ሌላኛው ተመታ
መመታት በጐ ለሳቀም ይድረስ
ራሱን እየጋጠ ራሱን ሣይጨርስ» አለ

ተከስተ፡- ክንዴ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የምትናገራቸው ነገሮች ከኔ የመረዳት አቅም ብዙ እርቀው ወደፊት ሄደዋል፡፡

ክንዴ፡- እኔ የምናገራቸው ነገሮች ወደፊት ሄደው ሣይሆን ያንተ የመረዳት አቅም ስልታዊ ማፈግፈግ አድርጐ ቢሆንስ?

ተከስተ፡- ይህም ለእኔ አዲስ ነው

ክንዴ፡- ሁሉም ላንተ አዲስ ነው እኔ የምልህ ተከስተ.....

ተከስተ፡- አቤት

ክንዴ፡- የመረዳት አቅምህን እንተወውና የመኖር አቅምህንስ የሚገታ እንዳለ ልብ ብለሃል?

ተከስተ፡- ማነው እርሱ/**በድንጋጤ**/

ክንዴ፡- HIV/AIDS!

ተከስተ፡- ሳልነካው ሳልደርስበት?

ክንዴ፡- ሊነካህ ወይም ሊደርስብህ ቢመጣስ?

ተከስተ፡- እሸሸዋለሁ፡፡

ክንዴ፡- እስከምን ድረስ?

ተከስተ፡- ከዓይኑ እስክሰወር ድረስ

ክንዴ፡- አታመልጠውም

ተከስተ፡- ስለዚህ?

ክንዴ፡- ስለዚህማ ከአይኑ እስክትሰወር ብቻ ሳይሆን እስከ መቅደሱ ሸሽ /ወደ **ሶስና በመዞር**/ ላንቺም ነው በእድሜ በቃኝ ከምጣዷ ከሚገፉት አንዷ እንዳትሆኝ፡፡

ሶስና፡- እሽ እጥራለሁ፡፡

ክንዴ፡- እንዳይረፍድብሽ፡፡ ከባብሎን ጥርሶች አምልጭ? አንገት መምዘዝ እድሜ መጠምዘዝ እንዳይሆንብሽ፡፡

አባት፡- ኧረ የዚህ ልጅ መቆየት ምን ይባላል ሶስናዬ?

ሶስና፡- ምን አውቄ አባባ እንደዚህ ቆይቶ አያውቅም

ተከስተ፡- ለነገሩ ምን ይሆናል ስለ ቅርሱ የሚያደርገው ክትትል ሰምሮለት ይሆናል፡፡

ክንዴ፡- ማን ያውቃል የባቢሎን ጥርሶች ነክሰውት ቢሆንስ፣ የኢያሪኮ ቅጥሮች አጥምደውት ቢሆንስ፣ ለቅርሱ ያልተመለሱ ራስ ወዳዶች ለነፍስ ይመለሳሉ ብሎ ማሰብ ከሰይጣን ፅድቅ እንደመጠበቅ ነው፡፡ እና እነዚህ የቃየል ልጆች የአባታቸውን ግበር ተግብረውት ቢሆንስ? ባቢሎን የውጊያ ስልቷን ቀይራለች፡፡ እንደ ጥንቱ ግንብ ላይ ቆማ ጦር ሰበቃ ሽቅብ ወደ ሰማይ አትወረውርም ይልቅስ በምድር ያሉ የሰማይ ወራሾችን በስልጣኔ ጨበጣ እየተዋጋች ቢሆንስ፡፡

ሶስና፡- ኧረ ተከስተ እኔ በጣም ጨንቆኛል እስኪ ወጣ ብለን እንጠያይቅ?

ተከስተ፡- አይ ሶስና፤ የት ነው የምንጠይቀው?

ሶስና፡- ቢያንስ ጓደኞቹ ጋር እናጠያይቅ፡፡

ተከስተ፡- ለማንኛውም እሽ ተነሽ እንውጣ **/ይወጣሉ/**

አባት፡- ክንዴ ስለቅርሱ የሰማህው ነገር አለ?

ክንዴ፡- እንዲህ ያለ ቁም ነገር ለእብድ ማን ያጫውታል ብለው ነው? አልሰማሁም እኔ፡፡

አባት፡- አይ ልጄ፡፡ እብዶቹስ እግዚአበሔርን የሰረቁት እነዚያ ራስ ወዳዶች ናቸው፡፡

ክንዴ፡- እንግዲያው እንደሚሉኝ ትክክለኛ እብድ ነኝ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔርን የከበረ መቅደስ አድርጐ ለራሱ ሊሰራኝም እኔ ግን መቅደሱን ለዓለም አከራይቼ አጭበርብሬዋለሁና ሌባ ነኝ፡፡ አቤት የሰው አንሶ ገና እርሱም ይፈርድብኛል ማለት ነው፡፡

አባት፡- ከፍርድ ያውጣህ ልጄ፡፡ በል እስኪ እኔ ውሰጥ ልግባ **/ወደ ወስጥ ይገባሉ/**

ክንዴ፡- /ፋታ/ እንዴ እውነት ይሔ ልጅ አደጋ ውስጥ ሆኖ ነው ወይስ እብደቱ ነው እንደ ልማዱ የሚያስፈራራኝ፡፡ ኧረ እብደቱ ይሆን፡፡ ወይኔ ክንዴ እናት አባቴን በማጣት ማቅ ብለብሰ እብድ.....እብድ.....ብለው ከራሴ ያጣሉኝ፣ ትናንት በዩኒቨርስቲ ስቃይ ተማሪ እንዳልተባልኩ ዛሬ እብድ፣ ወይ አንቺ ዓለም እብድ አልሽኝ፣ እብድስ አንቺ፤ ትላንት የጠራሽበተን ስም ዛሬ የማትደግሚ እብድ፣ ዘባራቂ፣ እብድ አንቺ ነሽ፣ እብድ.....

/አንድ ትንሽ ልጅ ከውጭ ይገባል/

ብርክ፡- አዚህ ቤቶች

ክንዴ፡- አቤት ማሙሼዬ ማንን ፈልገህ ነው?

ብሩክ፡- ተከስተን ነበር?

ክንዴ፡- ለምን ፈለከው?

ብሩክ፡- ሰው ልኮኝ ነው የለም?

ክንዴ፡- አ.....አ.....አለሁ ማሙሽዬ እኔ ነኝ ተከስተ ምንድን ነው የተላከው?

ብሩክ፡- ይኸው ይሔን ወረቀት ስጥ ተብዬ ነው? /ወረቀቱን ይሰጣል/

ክንዴ፡- ማን ነው የሰጠህ

ብሩክ፡- እኔ አላውቀውም፡፡ እንዲያውም ብቻውን ከሆነ ብቻ ነው ስጥ ያለኝ አልያ እውጭ አናግረኝ ብለህ ስጠው ብሎኛል፡፡

ክንዴ፡- አመሰግናለሁ ማሙሽዬ ይኸው ብቻዬን ነው የሰጠኸኝ የታዘዝከውን በትክክል ፈፅመሀል፡፡ በል አቅጥን

ብሩክ፡- እሽ /በፍጥነት ይወጣል/

ክንዴ፡- /ያነባል/ «ውድ ተከስተ ያልከው ነገር ተፈፅሟል፣አዳኙ ታዳኝ ፍፁም በማያስነቃ መልኩ X ተሰርቷል፡፡ ቅርሱንም ወደ ሚቀጥለው Steep ለማሸጋገር በዝግጅት ላይ ነኝ፡፡ ከእንግዲህ ናሆም የሚባል ሞገደኛ በዚህ ምድር ላይ የለም፤ አስወግደነዋል» /እንዴ ናሆም /ከት ብሎ ይስቃል/ እንዴ ወንድሜ.....አ....አአ.....ወይኔ ወንድሜ ወይኔ..... /ይወድቃል/ /አባት ከውስጥ በጥድፊያ ይመጣሉ/

አባት፡- ክንዴ ምነ ሆነሃል.....ኧረ ልጄን ምን ነካህ.....ክንዴ /መብራት ይጠፋል/

ትዕይንት ፬

/መብራት ሲበራ አባት፣ ተከስተና ሶስና ተቀምጠው ይታያሉ/

አባት፡- አሁን የእነዚህ ልጆች ጉዳይ ምንድን ነው መላው? ወይ ልጄን ሬሳውን እንኳን አግኝቼ ሞተ ብዬ ቁርጤን አላወቅሁ ወይ ይኼኛው አዕምሮው ተመልሶለት ራሱን ያሳተው ምን እንደሆነ አላስረዳኝ

ተከስተ፡- ኧረ አባባ ምንም የሚያሳስበን ነገር የለም ዝም ብለን ነው የምንጨነቀው

አባት፡- አዬ ልጄ ክንዴ ለራሱ ግድ የለው የመጣው መልዕክተኛ የወንድሙን ሞት ቢያረዳው ነው እንጅ ወንድሜ.....ወንድሜ እያለ ራሱን የሳተው ሌላ ምን የሚያስደነግጠው ነገር ኖሮ ነው ብለህ?

ሶስና፡- ኦፍ ተከስተ እኔ እኮ የናሆም ነገር ተስፋ አስቆርጦኛል

ተከስተ፡- ኧረ እባክህሽ ሶስና የሆነው ቢሆን እግዚአብሔር አለ አይደል እንዴ/**ይነሳል**/ አሁን እስኪ ለማንኛውም ሆስፒታል ልሒድ ክንዴን ልየው

አባት፡- በል እንግዲያው የምትሔድ ከሆነ አብረን እንሒዳለን

ተከስተ፡- እርስዎ ሆስፒታል የሚሄዱ ከሆነማ በቃ እኔም ሆስፒታል ከምሔድ የናሆምን ነገር እየዞርኩ ላጣራ፡፡ አይሻልም?

አባት፡- ይሻላል፡፡ በል አንግዲህ እኔ ወደ ሆስፒታል ላዝግም፡፡ ሶስናዬ አንቺ እዚሁ ሁኚ ምናልባት መልዕክት እንኳን ቢመጣ እንድትቀበይ፡፡

ተከስተ፡- ከቻልኩ እዚያው ሆስፒታል እመጣለሁ፡፡ /**አባባ ይወጣሉ**/ ሶስና ብቻዋን ትቀራለች፡፡

ሶስና፡- ወይኔ አምላኬ የውጭው ጉዞዬ ተሳክቶ ፕሮሰስ ስጀምር ይሕ ሁላ ጣጣ ለኔ ሲል ይሄ የሚወራው ሁሉ ሀሰት ይሆን፡፡ ማይክዬ እባክህ ምንም ሳይፈጠር ይህቺን ምድር ለቀን እንውጣ፡፡ ውጭ መውጣት ይሔን ያህል ያስቸግራል እንዴ? ብቻ ናሆሜ ሰላም ሆኖ ወንድምዬም ድኖ ከሆስፒታል ቢወጣ ማይክን አጣድፌ ፕሮሰሱን አስጨርስና ውልቅ ወደ አሜሪካ ቢያንስ ጅቡቲ እንካን መድረስ ለእኔ አንድ ነገር ነው፡፡

/ወደ ውስጥ ትገባለች/ /ተከስተ ተመልሶ ይመጣል/

ተከስተ፡-የባቢሎን ጥርስ አለ ያ ዕብድ፡፡ የባቢሎን ጦር ቢሆን ኖሮ ሳይወጋ ተመለሰ ወጋሁ ይላልና ሰኬትና እቅድ ሰማይና ምድር በሆኑ ነበር፡፡ የባቡሎናውያንን ቋንቋ የደበላለቀ አምላክም እነና ልቤንም አንድ እንድንመክር ቋንቋችንን ባደበላለቀ ነበር፡፡ የባቢሎን ጥርስስ ይታያል በአነንከሱ፡፡ የት አባቷ ሄደች ያቺ የዓርብ ግብር፣ የአባቷ ልጅ! አዝኜ ለግብር ብቀርባት አላርፍ ብላ ብትጭር መታረጃዋን ታወጣ ጀመር፡፡ የአባቷ ዕዳ እንዲህ ባይታሰብባትም በአንጉል ጨዋታ ሞቷን አፋጠነች፡፡ ያው ነው የባቢሎን ጥርስ አነካከሱን የበቀል መቀስ አመቃቀሱ ጨመረ፡፡ በአባቷ ቤት ደሟ ይፈሳል፡፡ የደሟ ትኩሳት የእናቴን ቀዝቃዛ መቃብር ያሞቃል፡፡ ፈረሱም እዚሁ ሜዳውም እዚሁ ሆኗልና ብምርሽ አይማረኝ፡፡

/ወደ ውስጥ ይገባል ተከስተ/ /በአንድ እጁ የሶስናን አንገት ጨምድዶ ይዞ ይወጣል/

ሶስና፡- ተከስተ በእግዚአበሔር ምን አድርጌህ ነው? የምታንገላታኝ፡፡

ተከስተ፡- አየሽ ያ ጨካኝ አባትሽ እናቴ እንዲህ እየተማፀነችው ነበር አስገድዶ የደፈራት ቁጭ በይ /**ትቀመጣለች**/ /**ፋታ**/ አባቴ ከ 13 ዓመት በፊት ነው በመኪና አደጋ የሞተው፡፡ እናቴ አባቴን እጅግ ታፈቅረው ስለነበር እሱ ከሞተ በኃላ ወንድ ሳያምራት ምላ ተገዝታ ጉልበቷን ታቅፋ ኖረች፡፡ አባቴ ቢሞትም ሙሉ ለሙሉ አምሳያ የሆንኩትን እኔን ጥሎላት ስለሞተ በእኔ ትፅናናለች፡፡ ሁሉ ነገራ አድርጋኝ ኖረች፡፡ በኃላ

ግን ያ እርኩስ አባትሽ መስሪያ ቤት ቀይሮ እሷ ከምትሰራበት መስሪያ ቤት ገባ። እናቴ ፀሀፊው ስለነበረች በተደጋጋሚ ሊያማግጣት ቢፈልግም እናቴ የማትሞከር ሆነችበት። ከዚያም ተስፋ የቆረጠ መስሎ በማዘናጋት አንድ ቀን ለስራ ጉዳይ ነው ብሎ ከከተማ ውጭ በመስሪያ ቤታቸው መኪና ይዟት ከወጣ በኃላ አስገድዶ ደፈራት። እናቴ ለሕግ ልታቀርበው ብትፈልግም ሰው ስላልነበራት አስገድልሻለሁ ብሎ አስፈራት። በተፈደረች በ9ኛው ወር አካባቢ እማ ታማ ሆስፓታል ገባች። ደሟን ስታስመረምር HIV positive ተባለች አየሽ የአባትሽን ጭካኔ አየሽ የልክስክስ አባትሽን ጨካኔ።

ሶስና፡- አባባስ?

ተከስተ፡- እሳቸውማ በቀራቸው የዕድሜ ልቃቂት ለእናቴ የእንባ እርጥባን የሚያቀርቡ የሁላችሁም ዕዳ ከፋይ ናቸው። በተረፈ ያ ዕብድ ወንድምሽ እንደ ሁኔታው ይደረጋል። ከዳነ የእናንተን ጽዋ ያነሳል። አብዶ ከቀረ ምህረት ያገኛል።/ አንገቱን ይዞ/ አሁን ከዚህ በላይ ላንቺ እድሜ መጨመረ አያሰፈልግም። በየቱ ጋር መቀላት ይሻልሻል? ምርጫ ልስጥሽ።

ሶስና፡- ተከስተ በምትወዳቸው እናትህ ይገርሃለሁ በአሱ አትውጋኝ

ፖሊስ፡- እጅ ወደላይ **/ፋታ/ /እንዱገቡ ምልክት ያሳያል ለነ ናሆም/**

ተከስተ፡- **/በጣም ይደነግጥና ጩቤውን ወደ ስርቻ ይወረውረውና እጆቹን ወደ ላይ ያነሳል/ /ናሆምን ሲያይ ተንገድግዶ ይንበረከክና ቀስ ብሎ ይነሳል/**

ሶስና፡- ናሆሜ **/በድንጋጤ/**

ናሆም፡- ሶሲ/ያቅፋታል/ እየተገረመ ገሙዱን ከእጇ ላይ ይፈታል።

ማይክ፡- ተከስተ ናሆምን ገድዬዋለሁ ያልከህ ውሸቴን ነበር። እርግጥ በተባባልነው መሠረት አግኝቼው ነበር። እንደምገድለው እርግጠኛ ስለነበርኩ ከመቸኮሌ ብዛት የተነሣ ገድዬዋለሁ ብዬ ላኩብህ። መምጣት ስላልቻልኩ ነበር ምልእክተኛ የላኩት። ነገር ግን ለመግደል አመቺ ቦታና ሁኔታዎችን ስጠባበቅ በፅኑ ክርስትናው ቀድሞ ገደለኝ። ናሆም በአስገራሚ ትህትናው በጥዑም ቃላቱ ለቤን ሰበረው እርሱን ያበቀለች ምድር እኔን ማብቀሏ ገረመኝ። ናሆም መሞት እንደሌለበት አመንኩ። ከዚያ ይልቅ ለክፋት እሽቅድድም የጀመርነው እኔና አንተ ቢያንስ ወይኒ ቤተ ወርደን የእጃችንን ማግኘት እንዳለብን አመንኩ። በወይኒ ቤት የሚደርስብኝን ሁሉ በፀጋ ለመቀበል ወሠንኩ። ከዚያም ፖሊስ ጣቢያ ደወልኩ እናም እየሆነ ያለው ሆነ።

ተከስተ፡- ስለምን እያወራህ ነው

ማይክ፡- ተከስተ ከወደቁ በኃላ መንፈራገጥ ለመላላጥ ነው ይልቅ ቅጣቱን ለመቀበል እራስህን አዘጋጅ።

ፖሊስ፡- ዝም በል ማናችንም ከሕግ በታች ነን። ንፁሐን ነፍሳትን የሚነክሱ የወንጀለኞችን ወንጀለኛ ጥርስ ድንጋይ እንዲነክሱ ታደርጋለች ግዜ

የማይከፍተው የተከደነ ወንጀል የለም። ሁሉም ለፊትህ የቀኝ እጅ በታች ነው። /ወደ ሌላው ፖሊስ ዞሮ/ ከዚያ ስር ጩቤ አንሳ ናሆም ጠዋት 2:30 ፖሊስ ጣቢያ ትገኝልናለህ በተረፈ አመሰግናለሁ። ቀጥሉ እናንተ!

ናሆም፡- /እንደመከተል ሲል ሶስና ትይዘዋለች/

ተፈፀመ

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!
ወለወላዲቱ ድንግል!
ወለመስቀሉ ክቡር!

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን::

የመጨረሻው መጀመሪያ

/መድረኩ ባዶ ነው በቤቱ ሰው ያለ አይመስልም ጭር ብላል:: ከስተውጭ በኩል በሩቅ የሚጣራ ድምፅ ይሰማል:: እየቀረበ ይመጣና በመጨረሻ ይገባል:: ጌታቸው ዕብዱ እየተወራጨ ይለፈልፋል:: ይቁነጠነጣል እናቱን ይጣራል::/

ጌታቸው:- እ...ማ...ዬ! እ...ማ...ዬ...! እ...ማ! ዋይ ዋይ...ዋይ! አለቅን በቃ ጠፋን ወደምን:: እማ ሊጨርሱን ነው:: ጊዜው እኮ ቀረበ:: ሳንዘጋጅ ማለቃችን ነው:: ዋይ ዋይ! የለሽም እንዴ እናቴ? ይህን ምስቅልቅል አንቺም ፈራሽው መሰል፤ ተደብቀሻል እማ! አንቺም ላይ ጦርነት ከፈቱብሽ እንዴ? አሃ...! ለካስ እንደ አማፅያኑ ምሽግሽን አጠንክረሻል ወይኔ እማ! አንቺም እንደ ወንድሜ እንደ ኃይሉ ተልፈሰፈስሽ? ጓዳ ገብተሽ ፊትሽን ከለልሽ ይገርማል:: ብቻ ባንቺ አይፈረድም ቀውሱ እኔ ዕብዱ እንካን ይኸው ተርበድብጄ የለም እንዴ! ወየው...ወየው...! ዓለም ተገለባበጠች፤ተገለባበጠች:: ተራሮቿ ተናወፁ:: የህዝቡ ዋይታ፣ የህቦች እሪታ በረታ...አለቅን...በቃ...ጠፋን ...ወደምን...ኧረ! እንዴ እግዜኦ...! እማ! ኧረ እ...እ...ማ!

/ወደ ጓዳ ዞሮ ሲጣራ ጊዜ እናት ተደናግጠው ነጠላቸውን እየጐተቱ ይገባሉ:: ሊጠጉት ሲሉ ይሸሻቸዋል:: ተደናግጠው ቀጥ ይላሉ::/

እናት:- ምነው? ምን ሆነሃል ልጄ

ጌች :- እንዳትጠጊኝ እዜያው ሁኚ አትቅረብኝ:: ዋይ...ዋይ...ዋይ!

እናት:- ጌትዬ በጡቱ ይሁንብህ...እመቤቴ ምን አልኩሽ? ምነው ከዚህ ስቃይ ብትገላግይኝ መድኃኔዓለም የኔ ጌታ.....አባቴ እባክህን ይቅር በለኝ::

ጌች:- እማ! አልፈልግም፤ እንዳትጠጊኝ:: ፈሪ ነሽ አውቄብሻለሁ እኔን ልጅሽን ለጅብ ጥለሽ አንቺ ጓዳ ተደብቀሻል

እናት:- ስራ ይዤ እኮ ነው የኔ ልጅ

ጌች:- ተይው እማዬ አለቅን በቃ ጠፋን...ወደምን! እንዚያውና እኛውልሽ ተጫረሱ ምድሪቱን በደም አቀላት ባህሩ በፈርሰ ደፈረሱ:: መቃብሮቹ ሞሉ በቃኝ አሉ:: የሬሳ ብዛት አንገፈገፋቸው ወየው...!

እናት:- ምንድን ነው የምታወራው? እስኪ አረፍ በልበት እህል ቢጤም አፍህ አድርግ ወይ! የዛሬው ደግሞ የተለየ ነው ምን ሰምተህ ነው?

ጌች:- ባርነት፣ ጦርነት፣ እልቂት፣ ፍጅት ፣ሞት፣ ረሃብ፣ ጥማት፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ የተራራ መናድ፣ የባህር ሞገድ ዋይ...ዋይ...ዋይ!

እናት፡- ተው ተው! አንተ ታዲያ ምን አስጨነቀህ? ጦርነትም ቢሉ ያው ሲጠግቡ ነው እኔ እናትህ ከነሙሉ ጓዴ ልኑርልህ እንጂ ረሃብ የሚሉት ነገር ጫፍህን አይነካህም::

/ጌታቸው መሬት ላይ ተቀምጦ ዙሪያውን በአዲስ ስሜት ያስተውላል.....እሱ ይተክዛል::/

ጌች ፡- እማዬ ግን የምታመልጭ ይመስልሻል?

እናት፡- ከምኑ ልጄ?

ጌች፡- ቂ.....ቂ.....ቂ.....!አሃ! ለካስ አንቺ ምሽግ ሰርተሻል:: ጓዳ ገብተሽ እንደ ወንድሜ እንደ ኃይሉ መጋረጃ ከልለሻል ግን ሞኝ ነሽ እማ! አታመልጭም ከጣሪያ በታች ወይ በብርድ ልብስ መጓረጃ ኋላ ቀርቶ በልቦና የተመላለሰው ዝብርቅርቅ ጨለማ የሆነ ሐሳብ በግንባርሽ ላይ ይነበባል:: ተታለሻል ቂ....ቂ.....ቂ.....!

እናት፡- **/ግራ ተጋብተው በአይበሉባቸው ግንባራቸውን ይጠርጋሉ::/**

ጌች፡- ወይኔ እማ! ምን እያደረግሽ ነው ያለሽው? ያደፈችው ነፍስሽን፣ በክፋት የበሰበሰውን ሕይወትሽን ነው ከግንባርሽ ላይ ያበሸው ፣ እኔን እናቴ ብቻሽን አይደለሽም ብዙዎች በየስፍራው እነሱነታቸውን መሸገዋል በሰው ሰውኛው ዓይን የጠሩ መስለው ቀርበው ክብር አግኝተዋል:: ቂ...ቂ...ቂ! ይገርማል አየሻቸው እማዬ፤ እኛውልሽ እኮ .....ያውልሽ የድሃይቱን መቀነት ሲያስፈታት ጉቦ ሲበላ:: ወይኔ ሆዲ እኮ እህል ካየ ሁለት ቀኗ ነው! ወይ አበሳዋ! እነሱንስ ትመለከቻቸዋለሽ? ለዕርድ የተዘጋጀ ሰንጋ መስሎ ሲገለጥ ይህንንስ እንም አልለቀውም ዋይ...ዋይ....ዋይ

እናት፡- ጌትዬ ተው ምን አገባህ አንተ...እነሱ እንደ ሆነ ስራቸው ነው ደግሞ እኮ በዘመናትን በእጅ ካልሄድበት ቀላሉን ጉዳይ እንካን የሚፈጽምልህ የለም::

/ለመሄድ ወደፊት መራመድ ሲጀምር...../

እናት፡- እ. ወዴት ልትሄድ ነው?

ጌች፡- ወንድሞቼና እህቶቼ ጋር ታወቂያቸዋለሽ? ብቻ ተይው አታወቂያቸውም የት እንዳሉ ግን ልንገርሽ? ትልቁ አፓርታማ ላይ ኬክ እየበሉና ሻምፖኝ እየጠጡ:: የማትሰልችኝን እናቴን አስቀየምኩህ አይደል ይቅርታ አድርጊልኝ፤ እብድ እኮ ቢያጠፋ አይቀየሙትም አለቅን በቃ ጠፋን ወደምን.....

ዋሽንት

እናት አለም ያኔ ሳላብድ በፊት ዩኒቨርስቲ የሚማር ልጅ አለኝ ብለሽ በኩራት ትናገሪ ነበር እኮ ትዝ ይልሻል:: አይደል? ይኸው ጨርቄን ጣልኩልሽ፤ በመርዝ የዕብደት ድግሪ ጫንኩ..... አበድኩልሽ ፣ አሳበዱኝ በቅናት ተቀምጠው የቅናት መንፈስ ተደባልቋቸው መርዝ አጠጠጡኝ:: መድሃኒት በደም ስሬ ገብቶ ራሳ ላይ ዘፈነብኝ ..... አየሽው ጌች እብዱን፤ ቀውሱ ተማሪ ልጅሽን?!

/አሳዛኝ ክላሲካል/

/እናት ወንበር ላይ ዘፍ ብለው ይቀመጣሉ ምሬታቸው ፊታቸው ላይ እየተነበበ ይተክዛሉ አንገታቸውን ቀና አድርገው እጃቸውን ወደፊት ዘርግተው ይለምናሉ::/

እናት:- እመቤቴ የኔ አለኝታ ምንው ምን አልኩሽ? በኔ በደካማዋ ላይ ይህን ሁሉ መከራ ደራረብሽው ፣ምነው የጫንቃዬን ክብደት አበዛሽው ፣ፀበልሽን እየጠጣሁ ፣ስለቴን በጊዜ እያገባሁ ከደጅሽ ሳልጠፋ.....እዬ.....! አሁንስ በዛብኝ ከአቅሜ በላይ ሆነብኝ ወላዲተ አምላክ እባክሽን አለሁሽ በይኝ:: መግቢያ መውጫው ሲጠፋብኝ፣ ድንብርብሬ ሲወጣ ፣ቀኙን ጠቁሚኝ ኧረ ስንቱን እችላለሁ::

/ትንሽ ፋታ ይሰጡና ይቀጥላሉ/

እናት:- ይኸው ይህን ከይሲ ሀይሉ ተብዬ ወልጄ ልጅ እንዳልወለድኩ የወላድ መካን አሰኘኝ ካለመጠጣት ካለማጨስ ሌላ ስራ የለው:: የታደሉትማ በሱ ዕድሜ ወላጆቻቸውን ቀጥ አድርገው:: አንድ ሰሞን ያስቀመጥካትን ሳንቲም ለቃቅሞ ቢወስድብኝ መቼስ ለማን ይነገራል ብዬ ዝም አልኩኝ አሁንማ ብሎ ብሎ የቤት ዕቃም እያወጣ መሸጥ ጀመረ:: አቤት የኔ ጌታ! ምን ልታሰማኝ ይሆን? ፊጣሪዬ ከቶ ምን ይሻለኛል ወይ አበሳ! .....ለነገሩማ መች በሱስ ይፈረዳል ጊዜው ነው ይህን ሁሉ ጣጣ ያመጣው:: ያው አባቱስ ቢሆን ከእሱ በምን ተሻለ? ቀን ከለሊት እየጠጣ በወጣ በገባ ቁጥር ጥፊና እርግጫው ቢከተለኝ....ጭራሽ ይህ ሳያንሰው ከዚያችም ከዚይችም ሲዛለል ኖሮ ሲብስበት የስንት ጊዜ ታናቹ የምትሆነውን ጠቅልሎ ገባ ድሮስ ከእንክርዳድ መች ስንዴ ይጠበቅና ነው እኔስ የልጁ በሱ እግር መጓዝ ያስገረመኝ:: ወይ ጉድ ብቻ.....የባሰ አታምጣ:: ሲያማርሩህ ደግሞ

/ጌታቸው ብድግ ብሎ እጅን ወደፊት ይቀስራል/

ጌች:- አየሻቸው እማ!

እናት:- ማንን ልጄ?

ጌች:- ዘራፊዎቹን ዋይ! ዋይ ዋ.....ይ! አለቅን በቃ ጠፋን ወደምን ዘረፋት ክብሯን ገፈፋት አኛውና ሮጠው ሄዱ ወ.....ይ.....ኔ! እማዬ .....ንዋያተ ቅዱሳቷን ቀሟት:: ጥንጥላው ፣ መጋረጃው፣ የካህናቱ ልብስ.....ኧረ ምንም አልቀረም ወሰዱት፤ በገንዘብ አምሮት ታውረው የህሊናቸውን ዓይን ንዋይ ጋረደባቸው የአናታችንን ሃብት መዘበሩት የተቀደሰውን ዕቃ ገበያ አወጡት፣ ቸበቸቡት አየሻቸው ፈረንጆቹ ሲሻሙና ሲገዙ ኧ.....ረ.... እንዴ..... .! ምን እያደረጉ ነው? በሩን .....በሩን በጨለማ ሊገነጥሉ እየታገሉ ነው:: ካህኑና ዲያቆኑ የሆነ ሰውም አብሯቸው ይሰረስራል:: ዋይ...ዋይ!.....ተገነጠለ! ተገነጠለ! ተገ..... ገቡ:: እማዬ ቁልፉ ጠፍቶባቸው ይሆን እንዴ! አይደለም፤ አይደለም:: ተመልሰው ወጡ:: የሆነ ነገር አንከብክበዋል:: በስመ አብ.....ታቦቱን ነው ለካስ ይዘው የሚሮጡት ዋይ!! ዋይ! አለቅን በቃ ጠፋን፣ ወደምን:: በብዙ ብር ሊሸጡት እኮ ነው ምን ተሻለ እማ?

እናት፡- ተወው የኔ ጌታ የተለመደ ነገር እኮ ነው ላንተ አዲስ መሰለህ እንጂ ራዲዮኑ በዕየለቱ የሚለፈልፈው ይህንኑ እኮ ነው፡፡ አምላካችን ምን ሊያሳየን እንደሆነ እሱ ይወቀው ብቻ፡፡

ጌች፡- እኔም አውቀዋለሁ ፣ውሸትሽን የልብሽን በር ዘግተሽው እንጂ አንቺም እኮ ታውቂዋለሽ ፣ታላቅ ወንድሜ ኃይሉም አባታችንም ቢሆን ያውቁታል፡፡

እናት፡- ምንድን ነው የምናውቀው?

ጌች፡- የመጨረሻውን መጀመሪያ!

እናት፡- ምን?

ጌች፡- የመጨረሻውን መጀመሪያ!

እናት፡- ስለምን መጨረሻ ስለምን መጀመሪያ ነው የምታወራው የኔ ልጅ?

ጌች፡- ስለ መጨረሻው መጀመሪያ!

እናት፡- ምንድን ነው እሱ?

ጌች፡- ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን እወቁ ይላል ወንጌሉ፡፡ ዓይን አላቸው አያዩም፤ ጆሮ አላቸው አይሰሙም፣ ልብ አላቸው አያስተውሉም ተብሏል እኮ እያወቅን ያለማወቅ ጭንብል ራሻችንን ጋርዶናል፡፡

እናት፡- ጥያቄዬን እኮ አልመለስክልኝም በል እኮ ጮሽ ንገረኝ፡፡

ጌች፡- እማ ኃይሉንና ጓደኞቹን ስታይ ምን እንደምትይ ታስታውሻለሽ? የዘመናችን ወንድ ተብዬዎች በጆሮዋቸው ሎቲ አንጠልጥለው ፀጉራቸውን ተቆጣጥረው ስታይ ምን ይሰማሻል? አድሎሽ ሴት ባትወልጅም በየመንገዱ ሴቷ እንደ ቡጢኛ ደረቷን ገልብጣ በሚኒስካርት ተሽቀርቅራ ወደ ስጋ ገበያ ስትገሰግስ አላስተዋልሽም? ይህም ይቅር «ባስ» ላይ አንቺን የመሳሰሉትን አዛውንቶች አሽንቀንጥረው ለወንበር ሲሻሙ አረጋውያንን «አንተ» ብለው ሲያንጓጥጡ.....አቤት!.....ያኔ በምሬት ምን ነበር የምትሉት?

እናት፡- አዬ! እኔ ደግሞ አዲስ ነገር የምታወራ መስሎኝ ነበር አፈን ከፍቼ ያዳመጥኩህ፡፡ እንዲያው በትንሽ በትልቁ ተጨነቅ ብሎህ ነው እንጂ እኮ ሁሉም እኮ ድሮ ቀረ! ሴቷም በሴትነቷ ራሳን ሸፈን አድርጋ ከአንገቷ ደፋ ብላ ወንዱም በወንድነቱ..... አዬ ምኑን አሳሰብከኝ ጌትዬ፡፡

ጌች፡- እባክሽን ቀጥይ፤ ብስጭት ናላሽን ያዞረው ዕለት እንጂ እኔ እኮ አንቺ ስትናገሪ ማዳመጥ በጣም ነው የማያረካኝ :: በይ እባክሽ!

እናት፡- ኧረ ጨውም የለው ነገሩስ ያው ካነሳኸው ዘንድ መቋጠር አቅቶኝ አንጂ እኛ ማናቸው እቴ.....ወፍራሟ ሴትዮ

ጌች፡- እማማ እጅጓ?

እናት፡- አዎ.....አዎ ያው መቼስ ያችው ጥቁር ቡና ናት የምታሰባስበን እና ይኸውልህ እሳቸው ሪዲዮኑን ፣ ቴሌቪዥኑንም ይከታተላሉ ጨዋታም ይሆንላቸዋል እዚያ ባህር ማዶ ወንዱን ወደ ሴት ሴቷንም ወደ ወንድ ይቀይራሉ አሉ አበስኩ ገበርኩ ጆሮ አይሰማው የለ አንድ ቦታ ደግሞ ህዝቡ ሰለፍ ወጣ አሉ

ጌች፡- ምን ሆነው?

እናት፡- ወንድ ለወንድ ሴት ለሴት መጋባት ይፈቀድልን ብለው ነዋ!

ጌች፡- እግዚኦ ዘረ አዳምና ሄዋን መች ይሆን ከተዘፈቅንበት የጥፋት ባህር የሃጢያት ሀይቅ ውስጥ የምንወጣው፤ ዋ.....ነፍሳችን በበደል ክምር ታፍና በስጋ መሀል ስትንፈራፈር በተቃራንው ደግሞ በስባሹ ስጋ በምኞት ዓለም ሲያሰምጠንና የቁጣ ልጆች የእርጉም እርጉም ሆነን ስንኖር.....መቼ ይሆን ከጨለማነታችን ተላቀን በብርሃኑ ፍሬ በበጐነትና በጽድቅ በዕውነትም በመታዘዝም የምንመላለሰው?

እናት፡- ዘመኑ ነው ምን ይደረግ መፋቀሩ ፣ታላቅ ማክበሩ ሁሉ ድሮ ቀረ ጊዜው ተበላሸ ጉሮሮአችን እንደተከፈተ መቃብር ነው ፣በምላሳችንም ሽንገላና ከከንፈሮቻችን በታች የእባብ መርዝ አለ ፣አፋችን እርግማንና መራርነት ሞልቶበታል ፣እግሮቻችን ደምን ለማፍሰስ ፈጣኖች ናቸው፣ጥፋትና ጉስቁልና በመንገዳችን ይገኛል፤ የሰላምንም መንገድ አናውቅም በዓይኖቻችን ፊት እግዚአብሔርን መፍራት የለም::

ጌች፡- ታዲያ ለምን አንቺ.....

/ጌታቸው አሰብ ያደርግና ወደ ወስጥ በሩጫ ይገባል ከኪሱ ወረቀት ሲወድቅ እናት በፍጥነት ብድግ ያደርጉታል ወዲያው ወንድሙ ኃይሉ የለበሰውን ነገር ገፎት እየሮጠ ይገባል ኃይሉ ይከተለዋል/

ሐይሉ፡- አንተ ቀውስ አምጣ ብዬሃለው አምጣ.....

ጌች፡- ቂ.....ቂ.....ቂ መተኛቱ ይብቃህ ፖሊሶች በር ላይ ይፈልጉሃል

ሐይሉ፡- ለምን?

ጌች፡- ሰሞኑን ከነጓደኞችህ ማጅራቱን ብላችሁ ዘርፋችሁ ወንዝ የጨመራችሁት ወጣት አስክሬን ተገኝቷል::

እናት፡- እግዚኦ ምኑን አሰማሽኝ እመቤቴ እግዚኦ! አቤት ሲያስፈራ የያኔው ጨለማ መበርታቱ

ሐይሉ፡- ምንድን ነው የምታወራው? ለምን ይህን ልጅሽን እዛው አማኑኤል አትጨምሪውም እዚህ ከሚበጠብጠን ለሱም እዛው ይሻለው ነበር

እናት፡- ምን በወጣው ራሴ አስታምሜ አድነዋለሁ?

ሐይሉ፡- ምን እንዳሳበደው አልታወቀም አይደል? **/በጥርጣሬ ዓይን ይመለከታቸዋል/**

እናት፡- በምን አውቁ ያው አባቱ ነበር.....

ሐይሉ፡- አባዬ ግን ያችን ፈላ አሹንጉሊት አገባ አይደል? ግን ስንቱ መሰለሽ እንደ አባዬ መሳይ ሽማግሌዎች በመኪና ፈልሰስ እያሉ ሴት ሲሻሙ የሚያመሹት

እናት፡- የጤና ነው ታዲያ ይኸ ዝሙት የረከሰበት ዘመን የተከበረው ገላ እንደሸቀጥ በየመንገዱ የሚቸረቸርበት ጊዜ ልጄ አንተ እንካ ለምን ሰው አትሆንም?

ሐይሉ፡- ከዚህ በላይ ሰው መሆን አለ እንዴ! በወጣትነቴ ላይፍ ያላየሁ መቼ ላይ ነው፡፡ ቀን ቂማ ላይ ውለን ማታ የጨብሲ ከልሰንበት ..... በቃ ከኛ ሌላ ሰው የሌለ እስኪመስለን እየጨፈርን እየዘፈንን.....

እናት፡- ኤዲያ! በቃህ! የሰው ከንቱ ምነው አንተስ በሆዴ ውሀ ሆነህ በቀረህ?

ጌች፡- የብዙዎች ወላጆች የምሬት ንግግር ነው እኛ እየተራገምን ዘመኑንም የተረገመ አደረግነው ልጅ ለወላጁ፣ ታናሽ ለታላቁ፣ መታዘዝ ቀረ ዋ..... በስጋ የሚዘራ ፍሬ እንበትናለን ከስጋ መበስበስን እናጭዳለን

ሐይሉ፡- ይልቅ ራዲዮኑን ከጓዳ አምጣና ክፈተው

/ጌታቸው ሲገባ ሐይሉ በእናቱ እጅ ያለውን ወረቀት ይመለከታል/

ሐይሉ፡- የምን ወረቀት ነው የያዝሽው? ፊደል መቁጠር ጀመርሽ እንዴ?

እናት፡- የጌትዬ ነው ቅድም ወድቆበት እንካ እስኪ አንብበው

/ከመድረክ ጀርባ ወረቀቱ ይነበባል/

«ማንም እንዳያስታችሁ ተጠበቁ ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፣ ብዙዎችንም ይስታሉ ፣ጦርነትም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠበቁ ፤ አትደንግጡ፤ ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው ህዝብ በህዝብ ላይ መንግስትም በመንግስት ላይ ይነሳልና፤ ረሀብ ፣ቸነፈርም ፣ የምድር መናወጥም ይሆናል»

ጌች፡- ፖሊሶች መጡልህ

ሐይሉ፡- በፊት በር ካለ በጓሮ አጥር ዘልዬ ማምለጥ እችላለሁ አይደል/**በፍርሃት**/

ጌች፡- ቂ.....ቂ.....ቂ! ነፍሰ ገዳይ ልጅሽን አየሽው እማ? ተወው አትበርበድ ፖሊሶችም አልመጡም / **ሐይሉ ሊመታው ሲጋበዝ እናት ይገላግላሉ/**

እናት፡- ተው እንጂ ኧረ ተው በዚህ እድሜያችሁ ወንድማማቾቹ ተደባደቡ ሲባል ሰውስ ምን ይላል?

ሐይሉ፡- ተቧቀሱ ነዋ ሌላ ምን ይመጣል? አንተ ግን ነግሬህአለሁ ይህች ነገር ከአፍህ ብትወጣ ፀጉር ከምላሴ ይነቀል አንተን አያድርገኝ የማደርግህን

ጌች፡- አይዞህ! አንተ ብቻ አይደለደህም ብዙዎች የንፁአንን ደም እያፈሰሱ ነው ነፍሳት ግን ወደ አምላካቸው ዋይታቸውን እየሰሙ ነው አቤት.....! በጓሮ በኩል ልታመልጥ ነበር አይደል? ብልጥ ነህ እባክህ! እዚህም እዚያም በየቦታውና በየጊዜያቱ እንዳለ አላጣኸውም አስተውል ለብዙዎች የሚዘገይ እንደ ሚመስላቸው አይደል

ሐይሉ ፡- ምኑ?

ጌች፡- ፍርዱ!

ሐይሉ፡- የትኛው?

ጌች፡- የመጨረሻው እግዚአብሔር የበቀል አምላክ መሆኑን አታውቅም?

ሐይሉ፡- ሄደህ የምታስቦካውን አስቦካ አሁንስ በጣም አበዛችሁት በየቤተክርስቲያኑ አግዚአታ ጠዋትና ማታ አድነን.....ምንድነው ይህ ሁሉ? መዓት የመጣ ነው የመለሰው **/በመረጋጋት/**

እናት፡- ከዚህ በላይ ምን ይምጣ? ወይ ፊጣሪ .....ብለህ ብለህ ነፍስ ታጠፋ

ሐይሉ፡- የተረሳ ነገር ለምን ትቀሰቅሻለሽ? መቼም የእስር ቤት ቅማልና ትኋን ሲፈተፍተኝ እንዲድር የምትፈልጉ አይመስለኝም

ጌች፡- ይመስልሃል? አዎ በርግጥ አንድ ነፍስ ላንተ ቀላልናት የንፍስ ባለቤት የሆነ ጌታ ግን እንደማይዘነጋት ተገንዘብ ልቦናን የሚመረምር አምላክ ያኔ አንተንና መሰሎችህን የደም ዋጋ ይጠይቃችኋል። ስንቅ የለላት ነፍስም ወደ ሲኦል ትወረወሯለች በምድር ያፈራሽው ፍርድ አስቀድሞ በሰማይ ይጠብቅሃል ቅማልና ትኋን ሳይሆን እሳት ይለበልብሃል አንተ ብቻ ሳትሆን ሁላችንም በምድር በስጋ ስንራመድ ሳለን የነፍስ ስንቅ ያላከማቸነውም ጭምር ይሆናል፤ እነዚህ ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው።» **/ይደናገጣሉ ጌታቸው በእጁ ጋዜጣ ይዟል/**

ሐይሎ፡- ራዲዮኑን የታል ያመጣኸው

ጌች፡- ተውኩት

ሐይሉ፡- ለምን?

ጌች፡- ምን ለመስማት እንደፈለግክ አልገባኝም

እናት፡- እውነት ብላል «ራዲዮኑ ሁሉ የሚያወራው ግራ ግራውን ነው የዚህ ሀገር መንግስት ከዚህ ሀገር መንግስት ጋር ተፋጣል የዚህ አገር ህዝብ በረሃብ አለንጋ ተገረፈ»

ጌች፡- ምን ይህ ብቻ በአራቱም አቅጣጫ የመከራ ነፋስ እየነፈሰ ነው አውሎ ነፋሱ ፣ ሰደድ እሳቱ፣ የምድር መናወጡ ..... እ.....ጦርፉ

ሐይሉ፡- አቦ ተወና! ደግሞ የአለም ሀዝብ በዚህ በዚህ ካልቀነሰ በጥበቷ የተነሳ ወደፊት መታፈናችን አይቀርም ይህ ሁሉ ለመልካም ነው፡፡

እናት፡- ምን አንተ?

ሐይሉ፡- ህዝብ ከህዝብ መጫረሱ መንግስት ከመንገስት መታኮሱ

እናት፡- ድንግል ወላዲተ አምላክ!

ጌች፡- እውነቱን ነው ኧማ! ይህ ሁሉ ለመልካም ነው ነገር ግን መልካምነቱ በርሃናዊው ህይወቱ ለመቀዳጀት የመንፈስ ስራ ለመስራት የተከናወነ ቃሉን ለተከተሉ ነው እንጂ በስጋ ለተመላለስን ግን መጪው ድቅድቅ ጨለማ ነው፡፡

ሐይሉ፡- የምን ጋዜጣ ነው እሱ?

ጌች፡- የሽብር! ላንብብልህ?

ሐይሉ፡- በል እስኪ

ጌች፡- እናት ልጃን በመጥረቢያ ከትፋ ገደለች፡፡ ቃላቸውን ሲሰጡ እንዳመለከቱት መሀረብ እየፈታ የችግር አረንቋ ውስጥ የከተታቸውን የ 5 ዓመት ወጣት ልጃቸውን 6 ቦታ ከቆረጡ በኋላ ሽንት ቤት ጨምረውታል፡፡.....ልቀጥል.....

ሀይሉ፡- አዎ ቀጥል፡፡ **/እንዲቀጥል በእጁ ምልክት እየሰጠው/**

ጌች፡- በወረዳ 10 የነበረውን በራራ ወንድሙን ከሚስቱ ጋር ሲሄድ በማየቱ በጭፍን ቅናት ተነሳስቶ መርዝ ስላጠጣው ከዚህ አለም ተሰናብቷል፡፡ ሪፖርተራችን እንደገለፀው ከሆነ.....

እናት፡- በቃህ! እመቤቱ አድራሽን ከዚህስ ሰውሪኝ፡፡ አይ ስምንተኛው ሺ! ለመከራ የተፈጠረ ህዝብ ምነው እንዲህ አበሳችን በዛሳ! ፈጣሪዬ ኧረ አንድ በለን፡፡.....

ጌች፡- እማዬ! አይዞሽ ይህ ሊሆን ግድ ነው የማያስጨንቅ ዘመን ይመጣል ተብሏል እኮ

ሐይሉ፡- ተው እባክህ ያለው ባለው ይደሰት እስከ መቼ ተፈርቶ ይዘለቃል፡፡

እናት፡- ሀይሉ ኧረ እግዚኦ በል ምኑን ደንዳናውን ልብ ሰጠህ ልጄ? ወንድም በወንድሙ ላይ ሲነሳ ፣ በግራ በቀኝ መከራው ሲበረታ.....አሉታው ሲያይል.....አቤት!

ጌች፡- ወንድም በወንድሙ ቀንቶ መርዝ ሲያጠጣው!

ሐይሉ፡- ምን? **/ሀይሉ ከመጠን በላይ ተደናግጦ የሚይዝ የሚጨብጠው አጥቶ አይኑን ያፈጣል/**

ጌች፡- እማ! ያኔ አባባ በየቦታው መንዘላዘል ስጀምር በመጨረሻም ቤሳቤስቲን ሳይተውልን ሲከዳን ተስፋሽ ምን እንደነበር ትዝ ይልሻል?

እናት፡- አዬ ጌትዬ! አንተው ነበርክ ተስፋዬ የአባታችሁ ስራ አንገቴን ቢያስደፋኝ ባንተ ነበር የተፅናናሁት ይህ ሀይሉ ተብዬማ.....

ሐይሉ፡- አቦ ምንድን ነው አበዛሽው አሁንስ .....ምን.....

እናት፡- አይ የኔ ጌታ ለወለዱት የማይታዘዝ፣ ፍቅር የሌለው ፣እርቅን የማይሰማ ምኑን አመፀኛ ሰጠሽኝ?! እመቤቴ ምነው ቸል አልሽኝ ርህራሄሽ ራቀኝ

/ሐይሉ ሊሄድ ራመድ ይላል/

እናት፡- ደግሞ አሁን ወዴት ልትሄድ ነው

ሐይሉ፡- የሚበላ በማቅረብ ፈንታ ወሬያችሁ ሁሉ መከራ ነው፡፡ ወይ ሳንቲም ምናምን ቢጤ .....መቀባጠር ብቻ

ጌች፡- ሐይሉ! ወላጅ እናትህ መሆኗን እረሳኸው?

ሐይሉ፡- እና

ጌች፡- አክብራት

ሐይሉ፡- እብድ

ጌች፡- አንተው አሳብደህ አንተው እብድ አልከኝ **/ሐይሉ ይደናገጣል አናቱም ይፈዛሉ/**

ሐይሉ፡- ምን ለማለት ፈልገህ ነው?

ጌች፡- ታስታውሳለህ አይደል ያኔ ታናሽህ ቀድሜህ ዩኒቨርስቲ ስገባ ትዝ ይለኛል አይንህ ደም ነው የለበሰው ሰንበት ት/ቤት በመከታተሌ እግዚአብሔር ልቦናዬን ወደ እሱ ቢያደርገው አንተን ከፋህ፣ የእናታችን የጧት ማታ ምርቃት በውስጥህ የማይጠፋ የቅናት ክበሪት ጫረ ፣ተንኮል ማውጠንጠን ጀመርክ፣ ልብህን የሞላው መጥፎ ሀሳብ አንገትህ ደረሰ፣ አፍነህ አወራጨህ፡፡ እማዬ .....ገንዘብ ስታጪ ያባረርሻትን ሠራተኛ አትዘነጊያትም አይደል.....ዘነጋሻት እንዴ?

እናት፡- በል እስኪ ቀጥል ልጄ

ሐይሉ፡- አንተ ጌታቸው ቢቀርብህ ይሻላል፡፡ እኔ.....

ጌች፡-አሥ አንተ! ሠራተኛችን ከቤት ስትወጣ እርጉዝ ነበረች

ሐይሉ፡- ከማን? ከአባባ ነዋ?

ጌች፡- አይደለም

እናት፡- ከማን ነው ታዲያ? አንተስ ከወዴት ሰማኸው?

ጌች፡- እዛው ነገረችኝ እስከ ትላንት ድረስ ታች ያለው ቤተክርስቲያን ደጃፍ ላይ ፍርፋሪ ትለምን ነበር.....ከተወለደው ህፃን ጋር እማ ህፃኑ ቁርጥ ማንን ይመስላል መሰለሽ?

እናት፡- እ.....

ጌች፡- ወንድማችን ሀይሉን /**ሀይሉ ሊመታው ሲጋበዝ እናት ያገላግሉታል**/

ጌች፡- እናም ነገረችኝ ሁሉን ዘርዝራ ዛሬ ግን በህይወት አብረን ተቀምጠን ጓደኞቹ ስላዩን ነግረውት ማታላይ ጠብቀው ከሀይሉ ጋራ አንገቷን ጠምዝዘው አንቀው ገደው ወንዝ ጨመሯት አቅም አጣው እንጂ ሁሉንም አይቼ ነበር።

እናት፡- እግዚኦ ስምንተኛው ሺ!

ሐይሉ፡- እና ምን ይጠበስ ነው የምትለው?

ጌች፡- ምንም ዋይ.....ዋይ.....ዋይ! አለቅን በቃ ጠፋን ወደምን ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ፣ትምክህተኞች፣ ሐሜተኞች፣ ጨካኞች፣ ከዳተኞች፣ ችኩሎች፣ ሰካራሞች፣በትዕቢት.... የሆኑበት የመከራ ዘመን ይህ ሁሉ ግን ገና መጀመሪያ ነው።

ሐይሉ፡- የምኑ?

ጌች፡- የመጨረሻው

እናት፡- በል እንጂ ልጅ ምን ምን ነገረችህ?

ሐይል፡- አንቺ ደግሞ ከዕብድ ምን ቁም ነገረ ትጠብቂያለሽ

ጌች፡- ዓይነ ህሊናዋ ታውሮ ባለበት ሰዓት ቅመም ሰጣት ሻይ ውስጥ የሚገባ በጀ አትይም?

እናት፡- በጀ

ጌች፡- በእጅ በእግር ገብቶ ካሳመናት በኋላ «ቀኑ ትዝ ይለኛል ሰኞ ጠዋት ነበር እዚህ አድራ ጠዋት ዩንቨርስቲ ለመሄድ ቁርስ ስጠይቃት ሻዩ ቃናውን ቀይሮብኝ ነበር። ቅመሙ ነው ብላ ዝም አሰኘችኝ፤ እዛ ስደርስ ይጫጫነኝ ጀመረ። ራስን መቆጣጠር አቃተኝ ያዝ መለስ ያደርገኝ ጀመር.....ይኸውልሽ ታሪኩ ይሄው ነው ያቺም መከረኛ ሚስጥር እንዳታወጣ በግፍ ተገደለች። ባላት ጊዜ ተጠቅማ ለንስሐ ስትዘጋጅ በመጀመሪያ የበደለችውን ሰው ይቅርታ ጠይቃ ወደ ፈጣሪዋ መማፀን ስትጀምር ከሀጢአቷ ሳትጠራ ሞት በአሳቻ መንገድ ቀደማት።»

እናት፡-ሀይሉ! አንተ አረመኔ ነፍሰ ገዳይ፣ አንዱን ተስፋ ይሆነኛል ብዬ የተመካሁበትን የዋሁን ልጄን በመርዝ አስበድከው የህይወቱን ሚዛን አዛባኸው እስከመጨረሻው አውላላ ላይ አስቀረኸው ምነው አንተ ታናሽ

ወንድምህም አይደል እንዴ የአንድ አብራክ ክፋይ ሆናችሁ እንዲህ ያለ ጭካኔ ትሠራለህ? የሰው ከንቱ ..... እግዚኦ/

ሐይሉ፡- **/በሀፍረት ወደ መሬት አቀርቅሯል/**

ጌች፡- ተይው ቃሉ ይፈፀም ዘንድ የግድ ነው፡፡ ወንድም በወንድሙ ላይ ይነሳል ተብሏል እኮ አትገረሚ ይህን የሚሰሩ ብዙዎች ናቸው፡፡ ረሀብ፣ የምድር መናወጥ፣ ቸነፈር፣ እሳተጎሞራ፣ ጉርፍ መጥለቅለቅ.....እማ! ዋይ.....ዋይ.....ዋ! በየዕለቱ ሲነገር ሲሰበክ እንሰማለን ነገር ግን ዓይን አለን አናይም ፣ ጆሮ አለን አንሰማም፡፡ ከአመጽም ብዛት የተነሳ የሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች፡፡ እስከ መጨረሻ የሚፀና ግን እርሱ ይድናል ለአህዛብም ሁሉ ምስክር እንድሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በአለም ሁሉ ይሰበካል፡፡

ተፈፀመ

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!
ወለወላዲቱ ድንግል!
ወለመስቀሉ ክቡር!